ጅዳ ነኝ

ከፀጋ ዮሐንስ

የደራሲዉ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

በ1991 ዓ·ም· በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

የሽፋን ዲዛይን
ከትዕግስት ፍቃዱ

መግቢያ

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የተቀረፁት ገፀ ባህሪያት በገሀዱ ዓለም የሌሉ ፍፁም ልቦለዶች ናቸው። የራሴንም ጨምሮ የማውቃቸው የስደት ጓደኞቼን ህይወት ምንም ያልነካ ሙሉ በሙሉ ልቦለድ ታሪክ ነው።

ታሪኩ የቆመበት ቦታ እና ባለታሪኮቹ የተንቀሳቀሱበት አካባቢ ግን ጅዳ እራሷ ናት።

ፀጋ ዮሐንስ

መታሰቢያነቱ የስደት ጓደኛዬ ለነበረችው ህይወቷን ጅዳ ውስጥ ላጣችው አስቴር _____ ይሁንልኝ።

ምስጋናዬ

ይህን መጽሐፌን አሁን የሚገኝበትን የመጨረሻ ቅርጹን ይዞ እንዲወጣ ለረዱኝ ለእህቴ ወ/ሮ ምንያ ዮሃንስና ለአቶ ጌድዮን ተክላ ከፍተኛ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ጅዳ ነኝ

ምዕራፍ አንድ

ለመጨረሻ ጊዜ ጥቁር ሻሽ አጠማጠም ተለማመድኩ። ሻሹን አሟዙሬ መጠምጠሙ በቻልኩ ቁጥር በአጭር ጊዜ አራሴን የቻልኩ እየመሰለኝ በተስፋ ተሞላሁ። ከአረብ አገር መጥታ የነበረችው የአጐቴ ልጅ በእጇ የሞላችው የወርቅ አንባርና የሰውነት ልስላሴ በአዕምሮዬ ብቅ እያለብኝ ጥቁር ቆዳዬን ጠላሁት። በምትኩ ጅዳ ሄጀ ጠየም ያለ ቆዳ ያማረ ሰውነት ቅርፅና ቁመናን እንኳን ለግሶኝ በውበት ስምነሽነሽ ታየኝ። እና ያኔ አዲስ አበባ ብቅ ብዬ ውበቴን በአገሬ እያበራሁ እንዴት እንደምስብ ቃኘሁ። ይልቁንም የሻከረ ጥቁር ቆዳዬን ከአጐቴ ልጅ ቡናማ ለስላሳ ቆዳ ከርዳዳ ፀጉሬን በለስላሳው ዘመናዊ ቡናማ ፀጉሯ ባወዳደርኩ ቁጥር «እንዴ! በጣም ቀላች አማረባት። መልኳም ተቀይሮ ውብ ሆናለች። በፊት ከዚህ ስትሄድ አመዳም አልነበረችም እንዴ?! ሆሆ! አያቴ ሲተርቱ «ሰው ኑሮውን ይመስላል» ያሉት ልክ ነው ሆሆ!» እያለች በአድናቆት ትናገር የነበረችውን የእናቴ ድምፅ በጆሮዬ ያስተጋባና በውበት

ከእርሷ እንደምበልጥ እራሴን አሳመንኩ. . . ብቻ እዛ ልድረስ ብዬ ፀለይኩኝ::

ወር ሙሉ ያጐቴ ልጅ ያወራችልኝን የነዋይ ብዛት ገና ካሁኑ ምን እንደማደርግበት ሀሳቤን ሰረቅ እያደረገ የራሱ አድርጐታል:: በውነት ገንዘብ ምን ያህል እንደምወድ እስካሁን አላወኩም ነበር:: ያች ዘመዴ ላደረገችው የወርቅ ድርድር ክው ማለቴንም አልክድም::

በነጭ እምነበረድ የታነፁ ነጫጭ ህንፃዎች ከበዙበት ደስ የሚል ከተማ እራሴን ሳገኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: አይኖቼ ከወዲህ ወዲያ እያማተሩ መንገዱን መብራቱን ህንፃዎቹን አልጠግብ አሉ:: በሰፊው የተዘረጋውን መንገድ መሀል ለመሀል የሚከፍል ብርሃን ነገር ከውስጥ ተቀብሮበታል:: ብቻ መንገዱ ከስፋቱ ከጥራቱ አይን የሚሞላ የሚለው ቃል ያንሰዋል::

አየሩ ግን ከበድ ያለ ነበር:: በሀይል እየተነፈስኩ ትንፋሽ እጥር ይለኛል:: ሁለቱን አገሮች ኢትዮጵያንና ሳውዲ አረቢያን በፍልስፍናዬ ሳስቀምጣቸው እንዲህ አድርጌ ነው:: ኢትዮጵያ በአየር በተፈጥሮ ስትበልጥ ይህችኛዋ ደግሞ በብርቅርቅናዋ ትበልጣታለች:: አዎ! ይህች ልክ እንደተኳለች በዕንቁ እንደተንቆጠቆጠች የራሷ ያልሆነ ውበት ያደመቃት ስትሆን:: . . . የኔዋ ደግሞ ምስኪን ውበቷን መደበቅ ይቀናታል:: ውበቷን ለማየት አየሯን መተንፈስ ያስፈልጋል:: ብቻ ለአሁኑ

ቁልጥልጩን መርጫለሁ:: ደግሞም የኔዋን ማን ይከለክለኛል?!

የጫኑኝ አረቦች በመጠየፍ እየተመለከቱኝ በአረብኛ ይንጣጣሉ:: እኔ ግን ያንድ ቃል ትርጉም ለማወቅ ችጉቼአለሁ:: ገና ጅዳ እንደደረስኩ ሻንጣዬን ጐተት እያደረግኩ ፈዝዤ እያለሁ የአውሮፕላኑ ማረፊያ ፖሊስ «ያ ሁማራ» ብሎ ያለኝ በህይወቴ ለኔ ተብሎ የተወረወረውን የመጀመሪያ የአረብኛ ቃል . . . «ያ ሁማራ» «ያ ሁማራ»

ሰዎቹ ቤት እንደደረስን ፈረንጅ መላዩ ሹፌር ሻንጣዬን ይዞ ተከተለን:: ፈረንጁን ሲሸከም ማየቱ አዲስ ነገር ቢሆንብኝም ወንዶችን ብዙ ማየት እንደማይፈቀድ ስለሰማሁ እርሱ ላይ ማፍጠጡን እየፈለግኩ ፈርቼ ተውኩት:: የአሰሪዎቼ ቤት እጅግ ያማረ ቤት ሆኖ አገኘሁት በፊልም ላይ ካየኋቸው ቤቶች ጋር ይማሰላል:: የዕቃዎቹ አቀማመጥ ለአይን ይመቻል::

ከአየር ማሪፊያ ፓስፖርቴን ይዛ ያመጣችኝ ሴት ፊቷን ስትገልጠው እንደድምፅዋ አሮጊት አልነበረችም:: ይህችው ሴት በምልክት ጫማዬን እንዳወልቅ ነገረችኝ:: በቤቱ የነበሩት ሰዎች ሁላ እኔ ወዳለሁበት አቅጣጫ የተለየ ነገር እንዳዩ አይነት በጣም አፈጠጡ:: ከሰዎቹ አስተያየት በጣም መንከርፈፌን አወኩ:: ሁኔታዬን ለመሸፈን ፈጠን ብዬ ፈገግታ ሰጠኋቸው:: ሴትየዋ ፈጥና ተቆጣችና በተሰባበረ እንግሊዘኛ «ኖ ስማይል ውመን»

/ፈገግ የማትለዋ ሴት/ በእጇ ደግሞ ወደ ወንዱ እያሳየች የአጐቴ ልጅ ያለችኝን ረስቼው ኖሯል። ደነገጥኩ። ካሁን አሁን ወደመታረጃው ቦታ የሚወስዱኝ መስሎኝ ሰውነቴ ሊኮማተር ተሰማኝ። ከደረጃው በኩል ብቅ ያለችው አሮጊት ሴት ልቤን አረጋጋችው። «ያ ሚስኪና» እያለች በመራራት አየችኝ። አረብኛ ከመቼው ተማርኩ። ያለችው ገብቶኛል። . . . ከአማርኛው ጋር አንድ የሆነ ቃል መሆን አለበት።

ቀጥሎም ሙሉ እቃዬን የያዘ ሻንጣዬን አይኔ እያየ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በርሜል ውስጥ እንዲከተት ተደረገ። አዳዲስ ቅያሪ ልብሶችና ጫማ ሳሙና ፎጣ ማበጠሪያ የጥርስ ብሩሽ አምጥተው ታጥቤ ለብሼው የነበረው ልብስም ሻንጣዬን እንዲከተል ሴትየዋ አስታወቀችኝ። ብቻ ከሁለም የቀጨኔ እናቴ ደፋ ቀና ብላ ያዘጋጀችው ሽሮና በርበሬ እንደቆሻሻ ሲጣል ነው። ገና እንደገባሁ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ አዲስ ስሜት ተሰማኝ። . . . ባይተዋርነት . . . ቦታው ያንቺ አይደለም የሚል አይነት . . . እናም ጠላኋቸው። ትንሽ እንኳን እንግዳ ናት የለም። በእንደዚህ አይነት አቀባበል . . . አስደንጋጭ አቀባበል . . . ተቀበሉኝ አሰሪዎቼ።

አስተማሪያችን የነበረችውን ሕንድ የምትመስል ባንግላዲሻዊት ሴት የፅዳቱን ስራ ረጋ ብላ አስተማረችኝ። ትንሽ ያስቸገረኝ ሥራ ቢኖር የቆጥራ /የወንዶች ሻሽ/ አተኳኮስ ነበር። ይህ ቆጥራ ሁለት ዓይነት ብቻ ነው። አንዱ ሙሉ ነጭ ሌላው እንደፊሊስጤሙ መሪ የቀይና

ነጭ ዥንጉርጉር። ታዲያ ይህን ስስ ሻሽ ከአራት ማዕዘን ወደ ሦስት ማዕዘን ቀይሮ መተኮሱ ልዩ ዘዴ ያስፈልገዋል። አለበለዚያ እየተዛነፈ /እየተዘናበለ/ ያደክማል። በሰውዬው ጭንቅላት መሀል ላይ የሚውለውን መስመር ለማስመርም ካውያውን መጫኑ ቀላል አይደለም።

መጥረግ ማጠብ እቃዎችን ማፅዳት ከባድ አይነት ሥራ አይደለም። በርግጥ አድካሚ ነው። ግን የሰው ልጅ በቀላሉ የሚለምደው ብቸኛ ሥራ ይህ መሆኑ ነው። እኔም በቀላሉ ተለማምጄ ከባንግላዲሻዊቷ ሰራተኛ ባላነሰ ፍጥነት ተፍ ተፍ ማለት ጀመርኩ።

ያበሻ ጆሮዬ በማይችለው ሁኔታ የሴትየዋ ጩኸት ያማርረኝ የጀመረው ገና በገባሁ ከጥቂት ሰዓቶች ጀምሮ ነበር። ያበሻ ጆሮ ከሌሎች ጆሮ በምን እንደሚለይ ታውቂያለሽ? ቁጡ ነው። ቶሎ ተቆጥቶ በንዴት ታ ይላል። ይህ ስለታማ ምላሷና ትዕቢተኛ አስተያየቷ እግሯ ስር ሆኜ ስትረግጠኝ የሚሰማኝ ስሜትን ይወልድብኛል። ብቻ . . . ሙሉ ትዕግስቴን ለአካባቢዬ ሰጥቼ ነገሮችን ረጋ ብዬ ማየት ስጀምር አዲሱ እርምጃዬ ቀለል ብሎ ታየኝ።

የመጀመሪያ ደሞዜን ሳገኝ ከደስታ ብዛት እንቅልፍ አልወሰደኝም። በጣም በጣም ተስፋ የሰጠኝ ደግሞ ሪያላቸው ወደኛ ብር ሲለወጥ እጥፍ የመሆኑ ነገር ነው።

ፐ . . . አልኩኝ። ፐ ድህነት ባይ! ባይ! ቻው ደህና ሁን ድህነት።

እ! ለእናቴ ወርቅ ልብስ በያይነቱ . . . እ! ለራሴ መኪናና ቪላ ቤት ብቻ . . . ወንድሜስ አም ለሱ ሚኒ ባስ ውይ እህቴስ? አም ለሷ ደግሞ የፀጉር መሥሪያ ሙሉ እቃዎችን ገዝቼላት ፀጉር ቤት ሳይሻላት አይቀርም. . . አክስቴስ ምን ትሰኛለች! ለሷ በቃ የሆነ ነገር . . . እ! አጐቴስ ይቀየመኛል. . .

አምን ሰንት ዓመት መሥራት አለብኝ? ሦስት ዓመት እንደምንም አብቃቅቼ በቂ ጊዜ ነው። ከዚያ እመለሳለሁ በጣም ናፍቄአለሁ። ያኔ ተዲያ ሌላ ሰው ነኝ።

ደግሞም አለምኩ። ቁምሳጥን ውስጥ ካየኋቸው የእመቤቴ የሀር ቢጃማዎች አንዱን አድርጌ . . . አገሬ ይመስለኛል ትልቅ ቪላ ቤት ውስጥ በሚደላ መቀመጫ ሆኜ ቴሌቪዥኔን እያየሁ . . . ከፊት ለፊቴ የተደረደረውን ነጭ ቸኮሌት እየበላሁ በፊልም . . . ስመሰጥ ክር የለሽ ዘመናዊ ስልኬን ይዤ ሥራ እንደበዛበት ሰው ወዲህ ወዲያ እያልኩ በሥራ ከማስተዳድራቸው የፋብሪካዬ ሠራተኞች ጋር በትህትና ሳወራ . . . በቃ ምን ልበልሽ ህልሜ ድሎት አጥግቦኝ ያድራል። ስነቃ ህልሜን እውን ለማድረግ ጠንካራ እግሮቼን በፍጥነት ከወዲህ ወዲያ አወራጫለሁ። ብቻ ጨኸታማ አሰሪዬን ድንገት በጥዋት ነቅታ ካየኋት ለቀኑ ሙሉ መጥፎ እድሌ ምልክት ሰለምትመስለኝ ደስ አይለኝም።

በሦስት ወሬ የዚያ ትልቅ ቤት ብቸኛ ሠራተኛ ሆንኩ። ምክንያቱ የእመቤቴ ስስታማነት ነው። ለኔ ትንሽ ገንዘብ ጨመረችልኝና ሙሉ ጉልበቴን ልሰጣት አስማማችኝ። ባንግላዴሻዊቷ የሥራ ጓደኛዬ የእኔ መምጣት እንዳስደሰታት ሁሉ በጣም ተከፍታ ወደአገሯ ተጠረዘች /ተላከች/።

ለሞኑን በለበቤ ለተሰበረው የልብስ ማድረቂያ ማሽን ማሠሪያ የሁለት ወር ደሞዜ ተቆረጠ። ሰርቶም እያለ ለመቀጫ ተብሎ ልብስ ለማስጣት በየቀኑ ሦስት አራቴ ፎቅ «ስጡህ» /የፎቅ መጨረሻ/ ስወጣ ፀሐይዋ ለማዩን ከትክታ ሰባብራ አናቴ ላይ ጂ ብላ የምትፈነዳ እስኪመስለኝ ድረስ ትጠቀጥቀኛለች። አንድ ልብስ ለማስጣት አንገቴን ባንጠራራሁ ቁጥር ውስጧ የምላወስ ይመስለኛል። የዚያን ያህል ጠራራ ፀሐይ መቼም ቢሆን አገሬ ላይ ሰፍሮ አያውቅም። ሁሉም ተክል እርርር. . . ርር ብሎ ድርቅ ብሏል። አረንጓዴ የሚባል ነገር የለም። ላለመዋሸት አልፎ አልፎ ከተተከሉት አመዳም ቅጠላ ቅጠሎች በቀር . . እነርሱም ቢሆን በየቀኑ እንደጉድ የሚጠጡትን ውሃ ፀሐይቱ እየነጠቀች እንዳይሞቱም እንዳይኖሩም ሆነው መሀል የተንጠለጠሉ ቅጠሎች ናቸው። ለአንድ ቀን ውሃ ቢቋረጥባቸው ምን ይሆኑ? ደግሞስ ውሃው ይጥማቸው ይሆን። ያገሬን ውሃ ሳስታውስ ምራቁ አፌን ይሞላዋል። ምራቄን በዋጥኩ ቁጥር ይበልጥ ይጠማኛል። ውሃ የሚጠጣው እየተገዛ በመሆኑ አንድ ፕላስቲክ ውሃ ጠጣሽ ማለት አንድ

ጠርሙስ ክካክላ ጠጣሽ ማለት ነው። ዋጋቸው አንድ በመሆኑ እንደልቤ ውሃ አልጠጣም። የምጠጣው በስስት ነው። እስክጠግብ ውሃ ጠጥቼ ከዛም ፊቴ ላይ ጨብ ጨብ ለማድረግ ምን ያህል እንደናፈቅኩ አትጠይቂኝ። እናም ስዑዲ በረሃ ናት በበረሃ ውስጥ ህዝቦቿ ይንፈላሰሳሉ። ባማረ መኪናቸው ባማረ መልካቸው ባማረ ቤታቸው። እመኚኝ ምቾት ልብሱን ጠቅልሎ የገባው አረቦች ጋ ነው።

የጉደላቸውን ቀዘቃዛ አየር የሚያሟላ ማሽን አላቸው። የአየር ማቀዝቀዣው ከባዱንና ሞቃቱን አየር ቀይሮ ቀዝቃዛ አየር እቤት ውስጥ እንዲሰፍን ያደርጋል። መኪና ውስጥም እንዲሁ። የፀሐይዋ ብርታት የሚሰማው እንደኔ ልብስ ለምታሰጣዋና ለምስኪኖቹ ወዛደሮች ነው። ልብስ ሳሰጣ በተለያየ አቅጣጫ ሰፎቅ ሥራ የሚሆን ድንጋይ ተሸክመው ገላቸው በላባቸው እየታጠበ ሲዋትቱ በየቀኑ አስተውላለሁ። ለሸክም ሥራ የሚሆን ግዙፍ አካል ያላቸውና መራራውን ፀሐይ የሚደፍሩት ሁለቱ ዜጎች ፓኪስታኖችና ግብፆች ብቻ ናቸው። አበሻማ በምን አቅሙ። ሚጢጢ ገላውን እንኳን ማወራጨት አይችልም እንደ ፀሐይዋ አቋቋም። ምን ያህል አጭርና ደቃቃ ህዝቦች እንደሆንን ታውቂለሽ? በርግጥ ከሕንዶች ብዙ አንተናነስም። ፊሊፒኖችንና ባግላዲሾችንም እንበልጣለን። ከነዚህ ከሚሸከሙት ህዝቦች እና ከአረቦች ጋር ግን የጉላ ልዩነት አለን።

ታዲያ ወዛደሮቹን ፓኪስታኖችና ግብፆችን የምታቀልጠውን ፀሐይ በድፍረት የተጋተሩትን ሳይ ኃይልና ጥንካሬን ይሰጡኝና ፀሐይዋ እንዳላቃጠለችኝ ሁላ አትት. . . ትት ሲበርድ እያልኩ እወርዳለሁ።

ደሞዜ ተቆራርጦ እንዳያልቅ በየቀኑ ጥብቅ ጥንቃቄ በቤቱ እቃዎች ላይ አደርጋለሁ። እመቤቴ ብዙ ሀብት ቢኖራትም ለሰበርኳት ስኒ እንኳን ምህረት አታደርግልኝም። በተለይ በቀደም እለት ገዝተዋቸው የመጡትን የበረንዳ አበባ ማስቀመጫ ባዞች ስወለውል እጅና እግሬ መንቀጥቀጥ ጀምረዋል። ሲገዙ አብሬአቸው ነበር። ከባዞቹ ውስጥ አንዷን ብሰብር እድሜ ልኬን ብሰራ እንኳን ለመክፈሌ እርግጠኛ አይደለሁም።

እመቤቴ አብዛኛው ጊዜዋን የምታጠፋው በየሱቆች እየዞረች በመግዛት በመግዛት በመግዛት ነው። በዚህ ልምዷ እኔም ብዙ ብዙ ሱቆች እያየሁ ክርፍፍ አስክል ተደንቄአለሁ። በሱቆቹ ጥራት። ከንደራ በሚባለው ቦታ ያለውንም የጌጣጌጥ ሱቅ አየሁት። በወርቁ ብዛት ተደንቄ ከሚገባው በላይ አይኔን ስለተከልኩ እራሴን አመመኝ። ወርቆቹን ለማድመቅ የበሩት ፓውዛዎች ሀይለኛ በመሆናቸው ልቤን ወደላይ አለኝ። እንደቋንጣ በወፍራሙ የተንጠለጠሉት ወርቆችና የአልማዝ ፈርጦች ብልጭልጭነታቸው ውስጤ ሰርጐ እየገባ መቆም አልቻልኩም። አልማዞቹም ብርጭቆአማ ስቦታቸው የሴት ልብን ይፈታተናል። እመቤቴን ጨምሮ ብዙ ሴቶች

በአካባቢው የሚርመሰመሱትም ምክንያቱ ይሽው መሆኑ ነው።

ለምግብ ገበያ ስንወጣም በአገራችን የሌሉ ምግቦች ይበዛሉ። ስማቸውን እንኳን ለምቼ የማላውቀው ፍራፍሬዎችም ብዙ አይቼለሁ። የቅጠላ ቅጠሎቹም ብዛት ለቁጥር ያዳግታል። አረቦቹ አመጋገባቸው ሰፊ ነው። ባለፈው ጊዜ የምበላው ደረቅ ዳቦ ብቻ ስለነበር በጣም ከስቼ ነበር። የወተቱም ጣዕም የተለየ ስለሆነ የግድ አፍንጫዬን አፍኜ እንደኾሰ በግድ ከጉሮሮዬ ሳወርደው ከርሜ ቀስ በቀስ ለመድኩት። «በወረቃ አይነበ» /በወይን ቅጠል/ የሚሰራው «ማህሺ» ተብሎ የሚጠራው ምግባቸው እጅ እንደሚያስቆረጥም ለማወቁ ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር። በኋላ ግን በጣም ጣፈጠኝ። በወይን ቅጠሉ ውስጥ በቅመምና በሌሎች አጣፋጭ ነገሮች ያበደ ሩዝ ይጠቀለልና በልዩ ዘይታማ ውሃ እንዲበስል ይደረጋል። ይህን ዘዴ በጥቅል ጎመንና ዝኩኒ ውስጡን ቦርቡረው ሩዙን በመጠቅጠቅም ይጠቀሙበታል። እኔ ታዲያ ቦርቡረው የከተቱትን ሩዝ ቦርቡሬ እበላና የወይን ቅጠሉንም ሆነ ዝኩኒውን ንክች አላደርገውም። የጅብ ጥላው ሾርባና «ሞለኪያ» የሚባለውን ምግብ «ባሚያን» ጨምሮ ዝልግልጋማ ውሃቸውን በማየት ብቻ ብጠላቸውም ብዙም ሳልቆይ ቀስ በቀስ ለምጀአቸዋለሁ። እንደውም አጣጥማቸው ጀምሮአል።

ልለምደው ያልቻልኩት የእመቤቴን ቁጣ ነው። ተሳስታ እንኳን እንደሰው አይታኝ አታውቅም። ሲሰራ

እንደማይደክመው ብረታማ አካል አድርጋኝ እንደጉድ እያሠራችኝ ምላሷን አትሰበስብም።

ለቁጣ ምክንያት ፍለጋ ሁሌ ስትጥር ለሞኑን ጥሩ ምክንያት አገኘች። ወጥ ቤት ሳህን ፍለጋ ስትንጐዳጉድ በሥራዬ የምታግዘኝን ቀይ የሸክላ ድስት ሰበረች። በነጋው የሚጠብቀኝን ንዝነዛ ልክ ኳ ብሎ ሲሰበር አውቄዋለሁ።

ይህች ሸክላ ለተዋጣ የኮፍያ አተኳኮስ የዘየድኳት አጋዥ ድስቴ ነበረች። የዚች ድስት ስፋትና ቁመት ከጌታዬ ጭንቅላት ጋር እኩል ስለሆነ የጌታዬን ጨርቃማ ኮፍያ ስተኩስ ድስቷን አለብሳትና ያለምንም መስመር ቀጥ አድርጋ ትወጥርልኝና ባጭር ጊዜ ተኩሼ እጨርስ ነበር።

«ዛሬ የኮፍያ አተኳኮስሽን ባሌ አልወደደውም እንደገና ተኩሺው» የጨኸት ትዕዛዝ ተከተለኝ። የተኩሱና የድስቷ ጉዳይ አላስፈላጊ ንግግሮችን እየጨመረብኝ መጣ። ተመሳሳይ ድስት ለመግዛት ምንም ዕድል አላገኘሁም።

«ሰሞኑን ሥራሽ ሁሉ የይምሰል ነው። መለገም ጀምረሻል። ከዳማዎች መለገም ከጀመራችሁ አትቻሉም። ስለዚህ ኮፍያ አጨማዶ በመተኮስ ጥጋብሽን ጀምረሻል ሥራሽ ሁሉ አልጥም ብሎኛል ሳሎኑን በትክክል አላፀዳሽውም። የሽቶ መደርደሪያዬን ካፀዳሽ በኋላ ሽቶዎቹን እንደነበሩ አልደረደርሽም . . . ትሠሪ እንደሆነ

እንደበፊትሽ ሥሪ አለበለዚያ . . . » የስድብ ጋጋታም አወረደች።

ወጥ ቤት እያለን አጠገቤ ቆማ አከታተፈን ስታይ ስለነበር ስርበተበት የያዝኩትን ቢላዋ ጣቴ ላይ አሳረፍኩት። ደሜ ቡልቅ ሲል የምታዝንልኝ መስሎኝ እንባዬን አቀረርኩ። ያ ደደብ የአውሮፕላን ማረፊያ ፖሊስ መጀመሪያ ቀን ሲነጅሰኝ ያለኝን ቃል ደጋግማ አለችው።

«ያ ሁማራ» /አህዮ/ ደምሽን መሬት ላይ አንጠባጥቢና ወየውልሽ ነገርኩሽ ብላ ተንጣጣች። ኧረ የሰው ያለህ . . . ደሜን እንደዚያ ሳዘራ . . . ጨካኝ። በእልህ ያቀረረ እንባዬን ዋጥ አደረግኩት።

ሁለተኛ ጨዋታ እንደሚረብሸኝ ፈሩ ላይ ማየት የለባትም። ሰትሰድበኝ የመከፋት የማዘን ሁኔታ ሳላሳይ እንደውም ኮራ ማለት እንዳለብኝ ወሰንኩ። ደግሞ ያ ፖሊስ ተብዬው አይቶኝ አያውቅ የት አውቆኝ አህያ ብሎ ሰደበኝ?! ይህቺስ መቼም ገረዲ እንደሆንኩ እና እንደዚህ አይነት ቃላቶች ለኔው እንደተፈጠሩ አድርጋ አንዴ አዕምሮዋን መርዛለች።

የልምምጫው ነገር አላዋጣም። እንደማያስብ እንሰሳ ስለሚያዩኝ እኔም እንደማስብ እንስሳ ሆንኩላቸው።

እንግዳ ሲመጣ የሚያቀርቡት የክብር የሻይ ዕቃ ስብስብ አለ። ትሪ በትሪው ላይ ያማረ የሀገር ጨርቅ ዳር ዳሩ የተጠለፈ . . . በጨርቁ ላይ የሲኒ ማስቀመጫ። በያንዳንዱ የሲኒ ማስቀመጫ ላይ በትንንሹ ተቆራርጠው

የተጠለፉ ትናንሽ የሀገር ቁራጭ ጨርቆች ይደረጋሉ። ለስኳር ማስቀመጪያውም የራሱ የሆነ ማዳመቂያ ጨርቅ ተጠልፎለታል። ትናንሽ ማንኪያዎችም በቦታቸው በቁንጥ ማስቀመጥም ይጠበቅብኛል። የሻይ ጀበናውን የሚጀቡንና በዚያውም የሻሂውን ሙቀት እንዳይወጣና ሻይው በቶሎ እንዳበርድ የሚያደርገው ጀቢኝ ጨርቅ ከስኒ ማስቀመጪያው ጋር ተመሳሳይ ከለርና አጠላለፍ አለው። ታዲያ ይህን ሁሉ ድርድር ለመማር ሶስት ቀን ፈጅቶብኝ ነበር። በሙከራዬ ሰዓትም ወይ የጀበናውን ልብስ ወይ የትሪውን እረሳለሁ። እኔ ይሽው ነኝ ቀልቤ ካልወደደው ቁም ነገር ብዬ ካልቆጠርኩ እረሳለሁ። ይህ ለኔ ምንም ያልመሰለኝ የሻይ ሽንሽናሽንሽን ወሳኝ የእንግዳ አቀባበል ነው. . . ለነርሱ።

የሚያከብሩት እንግዳ ፊት የእንግዳ መቀበያ ሽርጣም ዩኒፎርሜን ለብሼ ኩስ ኩስ ስል ብዙ ነገር ረሳሁ። ጉድ የሚያሰኝ ስህተት ሰራሁ። . . . የሻይውን ጨርቅ ረሳሁ። አዳር አላደርኩም። ሴትየዋ እንግዶቿን ጠርታ ኩሽና አስገብታ ምን ያህል የተሟላ የሻይ ዕቃ እንዳላት ልታሳያቸው ምንም አልቀራትም። አልገባኝም አንጂ ለዚያ ምሽት ብላ በልዩ ሁኔታ ያሰፋችው የሻይ ጀቢኝ ነበር። ኡ. . . ሳያዩት በመሄዳቸው ብግን ብላለች። ንዴቷን ልትወጣ እንደጥፊ ግፍተራ ማመናጨቅን በሚገባ ተጠቀመች።

ይህን ቂም አድርጋ ስትተነኳኩሰኝ መረረችኝ። እንደለመደችው ባሏ በሌለበት ጥፊ ሰነዘረች። ልስልስ

እጇን ያዝ አደረግኩና አጠፍ ሳደርጋት ትል አከለች። አሳዘነችኝና ተውኳት. . . አበሻ አይደለሁ። ባሷ እንዳይመጣብኝ ተቻኩዬ ጥቁር ልብሳቸውን /አባያ/ ለበስኩ። አንዴ ስለተሳሳትኩ የእመቤቴን እጅ ስለጨመደድኩ የሚደርስብኝን እግዜር ይወቀው ቶሎ ከዚህ ቤት መውጣት እንዳለብኝ ወሰንኩ።

የታክሲ ብር አምጪ ብዬ አፈጠጥኩባት። ስትርበተበት ተመልክቼ ለመቆራረጥ እንዲመቻት እኔው ጋር ይሁንልሽ ብላ ያልሰጠችኝን የአራት ወር ደሞዜንም ጠየኳት። ምንም እንቢታ ፊቷ ላይ ሳይታይ ሳንቲም ሳይቀር ቆጥራ ሰጥታኝ ለእኔ ምላሷ ፈፅሞ አውጥቶት የማያውቀውን ውድ ቃል «ሹክረን» /አመሰግናለሁ/ አለችኝ።

ከቤቷ ከመውጣቴ በፊት «ፖሊስ ብትጠሪ ኤንባሲ ሄጀ እጅን በቢላ ቆረጠችኝ እላለሁ። ዝም ብትይ ይሻልሻል። ለእልህ ለእልህ ከኔ አትብሽም . . . እኔ ጥቁር ነኝ እ! ያንን አትርሺ» አልኳት። እንግሊዘኛዬ እንደገባት ቶሎ ቶሎ ራሷን ነቀነቀች። ልሰድባት አፌን ከፈትኩ።

«ያ ሁማራ እ የማታስቢ ጨካኝ» ብዬ ትንሽ እንደተራመድኩ «ያ ከልባ» /ውሻ/ አልኳት። «ደግሞ እኔ ላይ በሠራሽው ግፍ ልክ መካ ሄደሽ ጠጠር ብትወረውሪ በፅኑ እንዲቀጣሽ ስለምፀልይ ምህረት አያደርግልሽም» አልኳት። በመሀል በመሀል አማርኛ ቃል ሳላስበው እያመለጠኝ በንዴት ሁሉ ነገሬ ተወራጨ። ስለአስልምና

ሀይማኖትና ስለመካ ይህን ያህል ባላውቅም አገሬ እያለሁ ጉረቤቴ የነበሩት ሀጂ ሙስጠፋ ወደ መካ የሀጅ ጊዜ የመሄዳቸውንና የጠጠሩን ነገር እናቴ በአድናቆት ስታወራ ሰምቻለሁ።

ኤንባሲ ድረስ ባለታክሲው አደረሰኝ። የኤንባሲው ጠባቂ ፊቴን ብቻ አይቶ ያለምንም ጥያቄ አስገባኝ። በማዘን ስላየኝ ብሶቴን አገነፈለብኝ።

«አባክሞ ይርዱኝ» አለቀስኩ

«እኔ ምንም ልረዳሽ አልችልም ግን ሊረዱሽ የሚችሉ የሚጠባበቁ ብዙ ሰዎችን በዚህ ህንፃ ውስጥ ታገኚአለሽ ግቢ!»

ከጉኔ በእርምጃዬ ልክ እየተራመደች ንግግሬን ቀስ እያለች የሰማች ልጅ በፈገግታ ቀረበችኝ።

«እንዴት ነሽ? ቅድስት እባላለሁ።» ለዚህች ልጅ ብዙ የምላት እንዳለ ተሰማኝ። ያች ጠባብ ጊቢም ያገሬ ንፋስ ይነፍስባታል። ከመጣሁ ለመጀመሪያ ጊዜ አማርኛ ሰማሁ።

«ደህና አይደለሁም። በየቀኑ እየሞትኩ ነው። ወደቤቴ መሄድ እፈልጋለሁ። በዚህ ኤንባሲው እንዲተባበረኝ ነው የመጣሁት»

ቅድስት ዞር ዞር ብላ አካባቢዋን አየችና «ከኔ ሌላ ወደአገርሽ መመለስ እንደፈለግሽ እዚህ ግቢ ለሌሎች ተናግረሻል?»

«ገና መምጣቴ ነው። አንቺም እንደኔ በችግር ነው የመጣሽው አዲስ አበባ ልትመለሺ?!» ፊቷ እዘን አለ።

«እኔ እንኳን አባቴ ስለሞተ ለእናቴ የአባቴን ወራሽነት አልቃወምም የሚል ሀጋዊ ወረቀት ላስፅፍ ነው የመጣሁት።»

«አዝናለሁ አባትሽ እዚህ እያለሽ ነው የሞቱት?»

«አምን ከሁለት ወር በፊት . . . እኔ እዚህ ዓመት ከምናምን ሆኖኛል።»

ለቅፅበት ታየኝ በዚህ በስደት ችግር ላይ የአባት ሞት። ዘገነነኝ ደግሜ ማዘኔን ነገርኳት።

«አሁን የረጋሽ ትመስያለሽ። ይህ ሁላ እንባ ለምንድን ነበር። በዓለም ላይ ያለ ምንም ችግር ያን የሚያክል እንባ አይገባውም ገባሽ! ደግሞ ይህን ንፁህ ጉንጭ ለምን በእንባሽ ታበልዝዋለሽ? እንባሽን ማድረቅ ነበረብሽ እዚህ አገር ከመምጣትሽ በፊት። ምክንያቱም ያንቺ ያልሆነ ቦታ ላይ ብዙ የሚያስለቅሱ ነገሮች ይገጥሙሻል።»

ቅድስት ማፅናናት ትችልበታለች። በመጠኑም ቢሆን ጥንካሬን ሰጠችኝ።

«ጭራቅ ከሆነች ሴት ጋር ሥራ ልሠራ በኮንትራት መጣሁ» ሌትዮዋ በጣም ክፉ ነች። እንደሰው ሳይሆን እንደዕቃ ነው የምታየኝ። በቃ በድሮ ጊዜ እንደተሸጠች ባሪያ አድርጌ እራሴን እንድቆጥር

አደረገችኝ። ይህንን መቋቋም አልቻልኩም። ታውቂያለሽ በጥፊ ሳይቀር ትመታኛለች።»

ቅድስት ነገሩ ያስደነቃት አትመስልም። ከዚህ በፊት ከሌሎች ወይም እራሷ የጥፊውን ጉዳይ ሳታውቀው አትቀርም። አይኗን ወደ መሬት ተክላ

«አንዳንዶቹ እኛን እንደዛ ነው የሚያስቡን። ግን ሁሉም አይደሉም። ጥሩዎችም አሉ። እኔ ለምሳሌ ካንቺ የከፋ ሥራ ነበረኝ አሁን ደግሞ በጣም ጥሩ ሰዎች ጋ እየሠራሁ ነው። እኛ በአገራችን ብቻ ነው ክብር ሊኖረን የሚችለው። በሌሎች አገሮች የተሰደዱ ጓደኞቼ እንደዚህ እንደኛ በጣም አይገዙ እንጂ ሁሌ ያነሰ ቦታ ነው ያላቸው። አሁን አንቺ ስለመብትሽ እርሺ. . . ማሰብ ያለብሽ እንዴት ቶሎ አገርሽ የምትገቢበትን ሁኔታ ነው። እዚህ የመጣሺው ገንዘብ ለማግኘት ነው። መሥራት አለብሽ ጠንካራ ሁኚ ተሽቀዳድመሽ ባዶ እጅሽን አገሬ ልግባ ብለሽ አትወስኚ የተሻለ ነገር ይዘሽ ሂጂ ትንሽ ከሠራሽ ቤተሰብሽን ልትረጅበት የምትችይበትን ገንዘብ ልታገኚ ትችያለሽ። እኛ ሁላችንም ጓደኞቼን ጨምሮ የመኖሪያ ፈቃድ የለንም። ፖሊስ እስኪይዘን ተደብቀን እንሠራለን። ያች የምታሠራሽ ሴትም ልታገኝሽ አትችልም። ሥራ ለማግኘቱ ሁላችንም እንረዳሻለን። ለጊዜው ከኔ ጋር እቤቴ ልውሰድሽ የቡና እቃዎች አሉኝ። ቡና እያፈላሁልሽ ስለነገሩ ትወስኛለሽ እመኚኝ ሀሳቤ ደስ ካላለሽ መልሼ እኔው እራሴ አመጣሻለሁ . . .» አመንካት…

ምዕራፍ ሁለት

የረዳችኝ ልጅ ቅድስት ከሌሎች እኩዮቼ አበሾች ሴቶች ጋር አስተዋወቀችኝ። ገና ሳያቸው አዲስ አበባ የመመለስ ሀሳቤን ቀየርኩ። ሁሉም በሀዘኔታና በፈገግታ ተቀበሉኝ። ሁለት ሁለት ስም አላቸው። በቀልድ የእስልምና ስማቸውንና እውነተኛውን አስተዋወቁኝ። ሳባ /ስባህ/፣ አበባ /ሳልዋ/፣ ዘመናይ /አይሻ/፣ ጽጌረዳ /ጀሚላ/።

ጀሚላና ስባህ ከቅርብ ቦታ እንጀራ ለኔ ሲሉ ሊገዙ፣ ሳልዋ ሽሮ ልታበስል ኩሽና አይሻ ደግሞ ቡና ልታቀራርብ ተበታተኑ።

አራት በሶስት እርምጃ የምትገመተዋ ጠባብ ክፍል ብዙ ፍቅር ያለባት ትመስላለች። ተመኘኋት። ጐኔን የማሳርፍበት ትንሽ ቦታ ቢሰጡኝ ብዬ ፀለይኩ።

አዲሱ ሕይወቴ ከአበሾች ጓደኞቼ ጋር እንደቀልድ ተጀመረ። የክፍሉ ዋና ተከራዮች ቅድስት ሰባህና ጀሚላ ናቸው። አይሻና ሳራዋ የጀሚላ ጓደኞች ናቸው። እዚህ የመጡትም አዲስ ቤት ለመከራየት እያፈላለጉ እስኪያገኙ ድረስ ብቻ ነው። ቅድስት እንደክፍሏ አባል ወስዳኖለች። እኔም ጥገኝነት እንዳይለማኝ የሚከፈለውን ከፈልኩ። እነ አይሻ እስኪሄዱና ክፍሏ ቀለል እስክትል እኔንም ጨምሮ

ትልቁን ቤት በአጋማው /የመኖሪያ ፍቃዱ/ ከተከራየው ሰውዬ መደበቅ ነበረብን። ሰውዬውና ሚስቱ ካንድ ልጃቸው ጋር ሲመጡ . . . የሚመጡበት ጊዜ የታወቀ ስለሆነ . . . ሲመጡ ጠባቧ ክፍላችን ትዘጋለች። ጮክ ብሎ ለመሳቅም ሆነ ለማውራት የሚችሉት ቅድስት ሰባህ እና ጀሚላ ብቻ ነበሩ። ሌሎቻችን እንታፈናለን።

ጀሚላ አይሻና ሳልዋ የሆነ የሚያመሳስላቸው የሚያጣምራቸው ነገር አላቸው። ሰባህ ወደ ቅድስትም ወደነአይሻም ታወላውላለች። ይህች ቅድስት ግን የተለየች ናት።

እድለኛ ሆንኩና ገና ሳምንት ሳይሞላኝ የቅድስት ዘመድ የሆነች ሴት ትወልድና በሥራ እንድረዳት በፊት የሚከፈለኝን ደሞዝ እንደምትከፍለኝ ተዋውላኝ ሥራ ጀመርኩ። ለዚያውም ሀሙስ ለአረፍት ወጥቼ አርብ እገባለሁ። እረፍቱ ብርቅ ሆነብኝ። እውነቱን ለመናገር ሥራ የምሠራ መስሎ አልታየኝም። የምታዘዘው በአማርኛ ነው። ልክ ቤተሰቤ መሀል እንዳለሁ ዓይነት ተሰማኝ።

ለአረፍት ስወጣ እነ አይሻ ቅድስት ወጣ ስትልላቸው ቁጭ አድርገው ይመክሩኝ ነበር። እዚህ አገር አበሻ ሆኖ አበሻ ቤት መሥራት እንደውርደት መቆጠሩን ሊያስረዱኝ ይሞክራሉ።

«ደሞዙ ዝቅ ያለ ነው። በዚያ ላይ እንዴት አበሻ ቤት ትሠሪያለሽ? ወደ አገርሽ ስትሄጂ ይቆጭሻል። አንድ

ቀን መንገድ ላይ ትገናኙና 'ይሀችኝ እኮ ሳሠራት ነበር' ብላ ትጮርርብሻለች። አረብ ቢገዛሽ ይሻላል» እያሉ። አበሻዋ ሴት ከአራስ ቤቷ ስትወጣ በሰላም አሰናበተችኝ። እነ ቅድስት ለዕረፍት ሲመጡ በጣም ደስ የሚል ጊዜ እናሳልፋለን። እነ አይሻ ሳልዋና ጀሚላ ግን አንዳንዴ ማታ ላይ ብቻ ይወጡና ይመለሳሉ። የተሻለ ሥራ እንደሚያፈላልጉ ይነግሩኛል። ምሽዋር /የሆነ የሚደረስ ቦታ/ አለን ብለውም ሲወጡ ተቆነጃጅተው ነው።

ጀሚላ በቅድስት ታሾፋለች።

«የቅድስት ሀልም "ረኢስ ከዳማ" /የገረዶች አለቃ/ ለመሆን ነው። ለዚህ ነው በእንድ ቤት የሙጥኝ ብላ የተቀመጠችው።» በቀልዷ እንስቃለን።

«እንደናንተ የማይመስል ሀልም ከማለም መሆን የሚችለውን ማለም ይሻላል። እንደ እመቤቴ ልጅ ከማለም ደግሞ ይሰውረኝ!»

ባንድ ድምፅ ጠየቅን «ደግሞ እሷ ምን አጥታ ታልማለች?»

«ያላትን እንዲያሳጣት!»

«ምን!» የሆሆታ ሳቅ ሳቅን

«አልነገርኳችሁም! የምትገርም ልጅ ናት። በቀደም አዝና አገኘኋትና ምን እንደሆነች ጠየቅኳት። ምክንያቷ አስቂኝ ነበር። 'አላህ ድሆችን ይወዳል' ሲሉ አልሰማሽም?

ታዲያ ሀብታሞች አያላዝኑም?» ብላ ነበር ያዘነችው። እኔ በሆዴ «አቤት እናንተ ሀብታሞች ሁሉን ነገር የራሳችሁ ማድረግ ትወዳላችሁ። እኛ ድሆች ባንድ አምላክ ፍቅር ብንበልጣችሁ እናንተ በምድር የምታሳልፉትን ደስታ ማካካሻ አንድ የተሰፋ ቃል ቢኖረን . . . አምላክ እናንተኑ ወዶ እያለም . . . ትመቀኙብኛላችሁ» እያልኩ አጉተመተምኩ። እንደገና ንግግሯን ቀጥላ ምን ትል መሰላችሁ . . . . «ኤዳ መርፊ የሚሰራበትን የአሜሪካ ፊልም አላየሽም?! ወጣቱ የንጉስ ልጅ ከንጉሳዊ ኑሮው ጠፍቶ የድህነት ጣዕምን ማየቱ እንዴት እንዳስደሰተው!!! . . . . እኔ ሁሉ ነገር አለኝ። በልጅነቴ እንደሌሎች ሕፃናቶች በመጫወቻ ከማለሜ በፊት ቤተሰቦቼ ያመጡልኛል። አያናድድም!» አለችኝ ብላ ቅድስት ስቃ ሳትጨርስ፦

አይሻ አፏን አጣመመችና «ለምን እንዲህ ስትቀብጥብሽ በጥፊ አትያት? ወላጆቿ ሰጥተዋት የማያውቁት ነገር ቢኖር ጥፊው ብቻ ነው። ሞልታታ!»

«እንዴ ታዲያ ምን አናደደሽ?» አይሻን አበሸቅናት

«የማይመስል ነገር ስትል ነዋ! ያች ሚጢጢ አረብ።»

«እኔ ግን ምን አልኳት መሰላችሁ?!» ቀጠለች ቅድስት «ማለምሽን ሳታውቂ በድህነት እያለምሽ ነው። አላህ ደግሞ ምኞትን እውን ያደርጋል። አንድ ቀን ሁሉን ነገር አጥተሽ በደስታ እፎይ ትያለሽ። ከዚያ የተመኘሽውን

የኛን የድሆችን ስሜት ህልም ታገኚና ታመሰግኛለሽ። ግን ላስጠንቅቅሽ ድህነት የሚጥመው ባየሽው የአሜሪካ ፊልም ላይ ብቻ ነው»

ሁላችንም ባንድ ድምፅ፡-

«ሀራም! /ግፍ ነው/ ሀራም!» ብለን ያለቻትን ነገር አወገዝን። የድሀ ቁጥር ቢጨምር ምን ልንጠቀም?!።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ያለሁበት ሰፈር "መርካቶ" የሚል ቅጥያ አለው። ጅዳ ያለ አበሻ አብዛኛው የሚኖረው በዚህ አካባቢ ነው። ቡዋዲ ይባላል። መቼም አበሻ በአንድ አካባቢ መሰባሰብ ይወዳል። የአበሻ ወንዶችም ተሰባስበው የሚያወሩበት «አፍሪካ ሻይ ቤት» የሚባል ሻይ ቤት አለ። እዚያው ምግብ የዶሮ ወጥ እና እንጀራ ይሸጥበታል። አጠገቡ ደግሞ ሌላ አነስተኛ መደብር አለች። ውስጧ ቡና ዕጣን ምናምን ይሸጥባታል። ለዚያውም ቡናው ደረጃ አለው። የሀረር ቡና የከፋ ቡና እየተባለ። የጤፍ እንጀራም እዚህ ሱቅ ይገኛል። ግን ስለሚወደድ ለበግል ጊዜ ብቻ ነው እኛ የምንገዛው። ሌላ እንደእንጀራ ብዙ አይኖች ያሉበት እንጀራ መሳይ ነገር ይሸጣል። እኛ የምናዘወትረው ይኼንኑ እንጀራ ነው። የሚገበየው ሁሉ አበሻ ስለሆነ አገር ቤት ያለሁ ይመስለኛል። እዚህ ሠፈር ስመጣ ትንሽ

ሳይርቅም የሀረር ስጋ የሚል ስም ያለው ስጋ ቤት አለ። መርካቶ ኢትዮጵያ የሚለው ሱቅም ውስጥ ጀበና ምናምን የባህል ዕቃዎች የሚገኙበት ነው።

አንዳንዴ ምንም ሳልገዛ እዛ አካባቢ እንደሞኝ አንገራብቤ እመለስ ነበር። በታ ደስ ይለኛል።

አለፍ ብሎ ሱቅ አልበዋዲ /የቡዋዲ ገበያ/ ይገኛል። ብዙ ነገሮች በረከሰ ዋጋ የሚገኙበት ሱቅ ነው። በጣም ሰፊ ነው። ትልቅ የገበያ ቦታ ነው። ታዲያ አበሾችና ሕንዶች፣ ባንግላዴሾች ፊሊፒኖች ሱዳኖች . . . የመሳሰሉት ድሀ ስደተኛ ሕዝቦች የሚገበያዩበት ቦታ ይኸው የቡዋዲ ገበያ ነው። አረቦቹ ታዲያ በዚህ የገበያ ቦታ ሲያሾፉ "ቦምቤ" ብለው የሕንዱን ከተማ ይወክሉበታል። የሦስተኛው ዓለም ግብይትም ብለው ይጠሩታል። በገበያው ቦታ ያሉት ሻጮች አብዛኞቹ የመኖች ናቸው። እዚህ ሱቅ ስንሄድ ፊታችንን አንሸፈንም። ለነገሩ ፀጉርና እንገት በደንብ ከተሸፈነ የሱዑዲያ ተወላጆች ላልሆኑት ምንም አይደለም። አይንና አፍንጫን ማሳየት ይፈቀዳል። ከአበሻ ወንዶች ጋር ስንተያይ ታዲያ መፋጠጥ ነው። ሰላምታ ንግግር የለም። አልፎ አልፎ በየሱቁ በራፍ ላይ «በአሻራ በአሻራ ሪያል ኩሉ አሻራ በስ» /የሁሉም ዋጋ አስር አስር ሪያል ብቻ/ እያሉ በመጮህ ገዢ የሚጣሩ አበሾች ቢኖሩም ሥራው ስለሚያሳፍራቸው ሦስት ቀን እንኳን ሳይሰሩ ሥራውን ለሕንዶች ይሰጣሉ። ወይ ደግሞ በዑምራ አካባቢ የመጡ አዲሶች ይሆኑና እዚያው መንገድ ላይ ፖሊሶች

ይጠርሟቸዋል። ምን ፖሊስ ቢኖር ግድ የማይሰጣቸው ደፋሮቹ አበሾች ደግሞ በድብቅ ያጣሩትን ካቲካላ በውሃ ፕላስቲክ እያደረጉ በጀርባቸውና በሆዳቸው ሸጉጠው መንገድ ላይ ይንቀዋለላሉ። መጠጥ ክልክል ስለሆነ አረቦች ይህ ካቲካላ ብርቃቸው ነው። በውድ ይገዙታል። ታዲያ የሚገርመኝና መልስ ያጣሁለት ጉዳይ የመጠጡ ሻጭና ገዢ እንዴት እንደሚገናኙ ነው። የተገኙ ጊዜ ጀርባቸውን አርባ ጅራፍ ይላጡና ወደ አገራቸው ይላካሉ። ጅራፉን ያልቻለ በሰላም አገሩ አይገባም።

በዚህ በቢዋዲ ሱቅ ፖሊሶች የብዙ ምስኪን ስደተኞች መሰባሰቢያ እንደሆነ ያውቃሉ። አብዛኞቹ የመኖሪያ ፍቃድ የሌለን ነን። በዑምራ አካባቢ የገባ ብዙ ስደተኛን ለማስወጣት "ሀ" ብለው የሚጀምሩት ከዚህችው የቡዋ ሱቅ ነው። እኔ ጥሎብኝ ፖሊሶቹን ሳይ ገሀነብ ይመስሉኛል። ገና በሩቁ እንቀጠቀጣለሁ። ሌላው ቢቀር ከምሠራባቸው ሰዎች ጋርም እያለሁ እንደማይዙኝ እርግጠኛም ሆኜ ቀልቤ አይወዳቸውም።

አይሻ ጓደኛዬ ግን አትፈራቸውም። በተለይ መጠውአች /የሀይማኖት ተከራካሪዎች/ በየመንገዱ እየተዘዋወሩ «ተገጢ ተገጢ ወሽክ» /ፊትሽን ሸፍኚ/ እያሉ የሚጮሁ ሲያለኛቸው የመኖሪያ ፍቃድ የሚጠይቁ ሳያገባቸው ደርሰው ላገራችን ፖሊስ ነን የሚሉ ደረቆች ናቸው። እነርሱ ከያዙ ጣጣቸው ብዙ ነው። መልካቸውና አለባበሳቸው የተለየ ነው። ከአፍንጫቸው በታች ያለ ዒማቸውን ሙልጭ አድርገው ይላጩና የጉንና ጉን

ዒማቸውንና የአገጫቸውን በጣም ራ-ጅም ያደርጉታል። በጣም አስቂኝ መልክ ይሰጣቸዋል። ጀለቢያቸው ከቁርጭምጫሚታቸው ከፍ ይላል። «ቆጥራ» የሚባለውን ነጭ ሻሽ ያለ ኢገል ያደርጉታል። አይሻ እነዚኞቹን በተለይ በነፍሳቸው ትጫወትባቸዋለች።

አንዴ ስታወራልን መጠውሉ ይመጣና ኢጋማ /የመኖሪያ ፍቃድ/ ይጠይቃታል። ከየት የመጣሉት ሀሳብ እንደሆነ እኔ እንጃ እቅፍ ታደርገውና ልትስመው ስታሞጠሙጥ «እስታፍሩላ» ብሎ ልቡ እስኪወልቅ ሮጠ። ሌላ ቀንም እንዲሁ ፖሊሶች ይይዟትና ኢጋማ ይጠይቋታል። የለኝም ትላቸዋለች ወደ መኪናቸው እንድትገባ ይጠይቋታል። አይሻ «አባያዋን» ታወልቅና በለበሰችው አጭር ጉርድ ቀሚስ ሆና «አገሬ ስለምፈድ ይህንን ድሪቶአችሁን እንኩ» ትልና ትወረውርላቸዋለች። ፖሊሱ ሁኔታዋ አስፈርቶት ለጓደኛው «ይህቺ እብድ ናት ከየት አመጣናት እንላለን ለዚች ሀላፊነት አልወስድም» ይልና አውርዳት አባያዋን ወርውሮላት መጭ ይላል። በሰላም እቤቷ ትመለሳለች . . .።

* * * * * *

ላሚ የሚባለው ልጅ የሰባህ ዘመድ ከኛ ጋር ላይፈራ በኛው በሌቶቹ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ያወራል። እነቅድስትን የሚጠይቁ አንዳንድ የአበሻ ወንዶች

ግን ብዙም ሳይቀመጡ በቁማቸው ይመለሳሉ። ቅድስት እንደነገረችኝ ከሆነ በዚህ አገር ህግ ሴትና ወንድ አንድ ላይ ከተገኙ ጥሩ አይደለም። መኪና ውስጥም ቢሆን አብሮሽ የሚሆነው ወንድ ወይ ባልሽ ወይ ደግሞ ወንድምሽ መሆን አለበት።

ሳሚ ግን ልክ እንደሴት ጓደኞቹን አዘውትሮ እየመጣ ያጫውታል። ቀጭን ሞጣጣ ቢጤ ነው። በክሬም የተለጠለጠ ፊቱ ከውሰጥ አመዳም እንደሆነ ያስታውቃል። የሰለለች አንገቱን እንደልማድ ያቅለሰልሳታል። ከፊት ለብቻዋ የተንጠለጠለች ፈጂም ፀጉር አለችው። ደማቅ የሆኑ ሱሪዎችን ሁልጊዜ ያደርጋል። አንገቱ ላይ ጉልቶ የሚታየው እንቅርት ሲናገርና ሲውጥ ወዲያ ወዲህ እያለ ያስቀይማል። ግን ድምፅ አልሰጠውም። ድምጹ እንደሴት ቀጭን ነው። ደጋግሞ አፉ ውስጥ የሚከታት ረጅም የትንሿ ጣት ጥፍሩን ከሌላው አካሉ አስበልጦ ሳይወዳት አይቀርም። በጣም የተለየ ሰው ነው። ሴታ ሴት ስለሆነ አብሮን ሲሆን ፖሊስ አንፈራም። እሱ ሄድ ሲልላቸው እነ አይሻ «ሙናዬ» ብለው በሴት ስም ያቀማጥሉታል።

አንድ ቀን ማንም በሌለበት ብቻዬን ሆኜ መጣ። እነቅድስትም እያሉ እኔ ሳወራ ፈዞ ስለሚያዳምጠኝ ለኔ የሆነ ስሜት እንዳለው ጥርጣሬ ነበረኝ። አብሬው መቀመጡን ስላልወደድኩት ሻይ ላፈላለት ወደ ወጥ ቤት ገባሁ። ስመለስ የኔኑ አረማመድ ሲለማመድ ያዝኩት። ማሾፍህ ነው ወይ? ስለው አይ አካሄድሽን ብለምድበት በጣም ደስ ይለኛል ብሎኝ እርፍ አለ። ሻይውን ሳመጣለት

ድምፁን ይበልጥ አለሳልሶ አይኑን ስልምልም እያደረገ ከሻይ ጋር የማቀርበው ጥሩ ቁርስ እንዳለ ጠየቀኝ። እርቦት ይሆን እንዴ? ብዬ ሳስብ አንድ ቀን ሳልዋ ያለችኝን አስታወስኩ። «ይሄ ቀጫጫ ቀላል ሰው እንዳይመስልሽ በጣም ሀብታም ሰው ነው» ያለችኝን። ታዲያ የቢት ምግብ ናፍቆት ይሆናል ብዬ ቁርስ አዘጋጀሁለት። አይኖቹን ያለማፈር ተክሎብኝ እንዳፈጠጠ እነ አይሻ በመሀል መጡልኝ።

እኔና ሳልዋ ብቻችንን ስንሆን

«ሳሚ እናንተ ሳትኖሩ ሲመጣ እፈራዋለሁ።» ሰላት ሳልዋ ጮሽ ብላ ሳቀችና «ብቻ ጡቱን ጉነተለኝ እንዳትሉ?»

«አያ እንደሱ ሳያሆን አስተያየቱ . . .» አልኳት

«አነጋገሩ እና አረማመዱን እወደዋለሁ ይላል ለዚያ ይሆናል።» ሳቋን ተጠለችና

«ግን አትፍረው ምኑ ያስፈራሻል እ . . . » ብላ የሳሚን ሚስጥር አወራችልኝ።

«ሳሚ እንዲህ የተበላሸው ለገንዘብ ሲል ነው። እርሱን በእድገ የሚያፈቅሩ የአረብ ባሎች አሉት። አንድ ጊዜ እህቱ ሞታበት ከሰባህ ጋር አብሬ ሄጀ መርዶ ተቀምጠን እያለ የሱዳን ሴት ጥምጣም አድርጎ በስሱ ሊጎስቁክ ተቀብቶ ተደብቆ ሊወጣ ሲል አጋጠመኝ። ደንግጬ አየሁት። ለማንም እንዳትነግሪ ብሎኝ ወጣ።

በማቀጥለው ጊዜ ስላየሁት ነገር አከርፊ ስጠይቀው አልቅሶ ነገረኝ ችግሩን። ሴት ሳይሆን ሴት የመምሰሉን ሚስጥር . . . ለገንዘብ ሲል ወንድነቱን ማጣቱን እና እነዚያ የአረብ ባሎቹ ብዙ ብር ይከፍሉታል ለሴትነቱ።» ብላ ለጀሮዬ ግራ የሆነብኝን የሳሚን ታሪክ አጫወተችኝ። አዘንኩለት።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

እነሳልዋ ቅድስት ሳትኖር ብዙ ውሸት ይነግሩኛል። ቅድስት ካለች ግን ውሸታቸውን የቆጥባሉ። መጀመሪያ ጊዜ ስለወንድ ሲያወሩ አልጋ አናውቅም አሉኝ። እኔም አምኜአቸው እኔም እኮ አላውቅም አልኳቸው። ቅድስት ባለችበት ግን እውነታቸውን አወጡ። የኔን አልጋ አለማወቅ ግን ደጋግሚ ምዬ ነው ያሳመንኳቸው . . . . በግድ። ድሮ ድሮ እንደነውር የሚታየው የወንድ ግንኙነት አሁን ደግሞ ተሟዙሮ . . . ጭራሽ ምን ይላሉ . . . «ቆንጆ ነሽ ቁመናሽም ያምራል ታዲያ ምን ሆነሽ ነው ይዘሽው የምትዞሪ» ብለው አሾፉብኝ። በዚያ ላምንት ብዙ ነገር ሲያወሩ አላዋቂ አድርገው አዩኝ። እንደባላገር . . . ማለቱ ባለባበሴ ያለኝን ችሎታ እስካዛባ ድረስ አስተያየታቸው ልዩ ሆነ። ከጓደኝነቱ ትንሽ ወጣ አደረጉኝ። ሲያወሩ ከቆዩ እኔ ስመጣ ጭጭ ይላሉ። ሁሌ ስለእኔ ወንድ አለማወቅ የሚያወሩ እየመሰለኝ መጣ። ጅዳ

ሆነ እንጂ አዲስ አበባ ቢሆን ይህ እነሱ የፈጠሩብኝ ስሜት ከአንዱ እጅ ነድቶ ይወትፈኝ ነበር። እናቴ «ጓደኛ ይቀይራል» ትል የነበረው እውነቷን ነው። እነርሱን መስዬ ተደባልቄ የሚያወሩትን እንዳወራ ወንድ ማወቅ ፈለግኩ።

በዚያን ሰሞን የተሰየ ሴራ እንደሚያሴሩ ሁሉ በጣም ተቀራርበው አፍ ለአፍ ሲያንሾካሹኩ ቅድስት ታዝባቸው «ስለነሱ አልነገርኩሽም በሚቀጥለው ጊዜ በደንብ አወራልሻለሁ ግን ተጠንቀቂ አብረሻቸው የትም እንዳትወጪ» ብላ አስጠነቀቀችኝ ሥራ ከመግባቷ በፊት።

እኔ ቅድስት ያለችውን ሳልሰማ ከነሳልዋ ጋር የሳልዋ አዲስ ቦይፍሬንድ እራት እቤቱ ይጋብዘናል ብሎው ሲያሽሞነሙኑኝ ምንም ሳልጠረጥር የሄዱበት ተከተልኳቸው።

እነ አይሻ መኪናው ውስጥ ሲቀሩ እኔና ሳልዋ መምጣታችንን ልናስታውቀው ቀድመን ገባን። የሳልዋ የወንድ ጓደኛ በነጭ ሰስ ካኔቴራ በጀልጃላ ሙታንቲ ወገቡን ይዞ እያቃሰተ መጣ። በረጅም ቁመቱ ላይ አገር የሚያክል ቦርጩን ቆንዝሮ በየደቂቃው እያገሳ «አላህምዲሊላ» /ቱመስገን/ ይላል። የተባለውን እራት ብቻውን በልቶ መጨረሱን ገመትኩ ከአገሳው። ሰውዬው አተኩሮ ማየት የሚገባው ሳልዋን ቢሆንም አይኑን ከእኔ ላይ አልነቅል አለ። ሲናገር ሆዱ እየተነቃነቀ ሰላምታ

ሰጠን። አስተያየቱን አፍሬ አቀርቅሬ እያለሁ ደስ የማይሉትን ዝብርቅርቅ የእግር ጣቶቹን አየሁ።

«አሚን ይባላል» አለች ሳልዋ የሰውየውን ስም ስትነግረኝ። ሲጨብጠኝ አይኖቹን አየሁ። ርሁሩሆች ይመስላሉ። ሳልዋ ከገንዘቡ ሌላ የሳባት ነገር አይኖቹ መሆን አለባቸው አልኩ በሀሳቤ።

ሳልዋ እንደመደናገጥ ብላ «እነ አይሻን ልጥራቸው አስክዚያ አሚንን አዋሪው። የሚያጫውትሽ ብዙ ነገር ይኖራል። ጥሩ ሰው ነው» አለችኝና በአረብኛ የኔን መልስ ሳትጠብቅ ጥላኝ ወጣች። ፈገግ አለልኝ። ፈገግታውም ሩሀሩህ ነው የሚያስፈራ ሰው አይደለም። ስለዚህ ሳልዋ እንደማትመለስ እኔ ከእርሱ ጋር እንደምቆይ ሲነግረኝ በሳልዋ ብናደድም አልሰጋሁም።

ረጋ ብሎ ልስልስ አደቹን ሰጠኝና ወደ አንድ ክፍል ወሰደኝ። ግማሽ አረብኛ ግማሽ እንግሊዘኛ ያወራል። ሙሉ ለሙሉ እንግሊዘኛ ላውራ ቢል በደንብ እንደሚናገር ያስታውቃል ብቻ አረቦች እንደዚያ ናቸው አረብነታቸውን ያመልኩታል። ሺ ጊዜ ናላቸው እስኪዞር ቢማሩ ጀለቢያ /ቀሚሳቸውን/ አያወልቁም። ባህላቸውን አይረግጡም። ቋንቋቸውንም መራቅ አይፈቅዱም። ሩዛቸውን በእጅአቸው አፈስ እያደረጉ እግራቸውን አነባብረው መሬት በመቀመጥ የመመገብ መለያቸውን አይተውም። የምግብ ጠረጴዛ ሹካና ማንኪያ ሞልቶ

ቢተርፋቸውም። ባህላቸውን የሙጥኝ ብለው በሌሎች ባህል ያለመጠመዳቸውን ጥንክሬአቸውን አደንቅላቸዋለሁ።

ክፍሉ ውስጥ እንደገባሁ ነጭና ሰፊው አልጋ አስደነገጠኝ። የፊቴን መቅላት በመስተዋት ማየቴ ይበልጥ ፍርሃቴን አባባሰው አልጋው ላይ ከስምንት በላይ ትራሶች አሉ። በነእሱ አፍኖ የሚገድለኝ መሰለኝ። ከወደ እጁ ቀጭን ማሰሪያ ያለው ገላን በደንብ የሚያሳይ በፊልም ያየሁት አይነት ስስ የሌት የሌሊት ልብስ እና ተመሳሳይ ከለር ያለው ገመድ መሳይ ነገር አልጋው ላይ ተደርገዋል። ገመድ መሳዩ ነገር ከብዙ አትኩሮት በኋላ ሙታንቲ መሆኑን ማወቄ ፈገግ አስደረገኝ። ከላይ አበባ ተደርጓል. . . ቀይ፣ ሽቶም።

ከመኝታ ክፍሉ ወደውስጥ ያለው በር ሲከፈት የመታጠቢያ ክፍል ይገኛል። በፍርሃት ተንደርድሬ የመታጠቢያ ክፍል ገባሁና በሩን ዘጋሁ። አሚን በቀልድ አነጋገር ያን የብልግና ስሰ ቢጃማ መውደዴን ጠየቀኝ። አሁን ገባኝ ምን ማረግ እንዳለብኝ ላሰላስል በር ስር ተቀመጥኩ። ጊዜ ለማግኘት የባኞውን ውሃ ከፈትኩ። የውሃው ጀቲታ አስጨነቀኝና ዘጋሁት። ወዲያውኑ ፎጣ የያዘ እጁን ዘረጋልኝ። ቀስ ብዬ ሳየው ፊቱን ወደውጪው አድርጓል። እንደሀሳቡ እራቁቴን እንዳያየኝ መሆኑ ነው። ፎጣውን አሸርጬ እስክወጣ ጠበቀኝ። እራቁቴን እንዳያየኝ ማድረጉ ቢያስመሰግነውም ሊያለብሰኝ ያዘጋጀው ቀውጢውን ቀሚስ ምን ይሉታል? እኔ ገላዬን አልታጠብኩም። ልብሴንም አላወለቅሁም። እያነባሁ ብቅ

አልኩዋት። እግሩ ስር ተንበረክኩና «ነገሩ አልገባኝም አንተ የሳልዋ ጓደኛ መሆንህን ብቻ አውቄ ነው የመጣሁት እንደዚህ ያለ ቀሚስም በህይወቴ ተመኝቼውም ለብሼም አላውቅም እጠላዋለሁ» አልኩት።

ከጉልበቴ ብድግ አድርጉ እንባዬን እየጠረገ

«ኢሽ ሙሽክላ /ምንድን ነው ችግሩ/» ብሎ ረጋ አለ። ከውስጥ የሚፈታተነውን ወንድነቱን ሲቆጣጠር ታየኝ።

ነገሩን በዝርዝር ሲያስረዳኝ ሁለታችንም ጉን ለጉን አልጋ ላይ ተቀምጠን ነበር።

አሚን ጓደኛው ቤት መደወል ፈልጉ ሲደውል ይሳሳትና የሳልዋ የወንድ ጓደኛ ቤት ይደውላል። ሳልዋ ድምፅ ደስ ሲል ብላ ታጠምደዋለች። «ደስ ካለሽ ማታ ደውይልኝ» ብሎ ስልክ ቁጥሩን ይሰጣታል። ብቻዋን ስትሆን ትደውልለታለች። የስልኩ ወሬ ይደራና «እኔ ቢንት /ልጃገረድ/ ነኝ» ትለዋለች። አሚን ሳይደነቅ «እዚህ አገር ያላገቡ ሴቶች ሁላ ልጃገረዶች ናቸው። ያለልጃገረድነታቸው ከተገኙ የሚጠብቃቸውን ስለሚያውቁ ቢሞቱ አይሳሳቱም» ይለታል። ቀልጠፍ ትልና «ታዲያ ልጃገረድ ለማየት ጋብቻ ያስፈልግሀል እኔ ያለጋብቻ ባሳይህ ምን ታደርግልኛለህ» ትለዋለች። ይቋምጥና «የፈለግሺውን» ይላታል። «ውሸቴን ነው» ስትለው «ልጃገረድ ካልሆንሽማ አልፈልግሽም እንደውም ሁለተኛ አትደውይ ለዚህ ለዚህማ የአውሮፓና የአሜሪካ ሴቶች ምን አሉኝ?» ሳልዋ

ስልኩን እንዳይዘጋ ተለማምጣ የእኔን ሁኔታ ትነግረውና አግባብታ እንድታመጣለት ክፍያ ይዋዋላሉ። ለእኔም የሆነ ክፍያ እንደሚኖረኝ እርሱ እራሱ ይነግራታል። በዚህ ምክንያት እኔ አሁን ከማላውቀው ሰው ጋር እገኛለሁ።

የሳልዋ ሥራ ከኔ ይበልጥ ለእርሱ አናደደው። ላልስማማ አታለው ስላመጡኝ አዘነልኝ። ከማዘኑ የተነሳ ብቻ አንዴ ላመኝ። ከንፈሮቹ በጣም ይሞቃሉ። ሰውነቱም በጣም ሲሞቅ ይሰማኛል። እኔም በጣም ስላመንኩት አስተቃቀፉን አልጠረጠርኩም። እንደውም በደንብ እንዳምነው እራሳቸውን ለወንድ በገንዘብ መልክ ለሚሰጡ ሴቶች ያለውን አመለካከት አወራልኝ።

«እንደዛ ዓይነት ሴቶች ያስጠሉኛል። ሴት እዚህ አገር በድብቅ የሆነበት ምክንያት ስለሚያስቀጣ ነው ያ ማለት የኛ ሴቶች ነፃነት አልተሰጣቸውም ሴቶች ነፃነት ሲሰጣቸው በጣም ባለጌዎች ናቸው። የሀገሬን ሕግ እወደዋለሁ። ሴት ነፃነት ማግኘት የለባትም። ነፃነት ቢያገኙ ኖሮ . . . ያ አላህ አሆ! እንደአውሮፓ ሴቶች የገዛ እህቴን እንደዛ ቂጧን ጥላ ስትደንስ! ወንድ ለመሳብ መላ አካሏን ስታቁነጠንጥ . . . አሉዝቢላ!» አይኑን ጨፈን ገለጥ እያደረገ ቀጠለልኝ በአገሩ ሴቶች በጣም እንደሚመካ የአረብ ሴት ቆሽሻ አታውቅም በሕጋችን ከሚያቆሽሻት ነገር እንከላከልላታለን እያለ።

ጥሩ ሰው ነው። እራሱን እየተቆጣጠረ ምንም ሳይነካኝ እቅፍ አድርጉ እንደ አገሩ ሴቶች ውስጡ ከሚያሰቃየው ሙቀት ሲከላከልልኝ አደረ።

ጠዋት ላይ «ይህን የመሰለ ውብ ሌሊት አላልፌ አላውቅም። እንዲህ እራሴን መግታት የምችል ጀግና ነኝ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ሴት በጣም ስለምወድ እንኳን አጠገቤ ተኝታ ይቅርና ገና ላስባት ውስጤ ያተኩሳል። ዛሬ ወንድ ሆኜ ከወንድነቴ ፊት በቆራጥነት ተጋተርኩ። ይታይሽ ለዚያውም ከምታምር ምንም ከማታውቅ ንፁህ ልጅ ጋር አድሬ ቡናማ ገላዋ ልቤን እያቀለጠው. . .»

በነጋታው ላልዋ ትንሽ እንኳን አፈር ሳትለ ክፍያዋን ልትወስድ መጣች፡ ገና ሲያያት እነዚያ ርህሩህ አይኖች ተቀይረው በንዴት ቀሉ። በጥፊ ጭው አደረጋት። ላልዋ በምፀት እነጋገር «ዋሽሽኝ ልጃገረድ አልነበርሽም» አለችኝ። እኔ የምላት አልነበረም። አሚን ምላሹን እየጮኸ አስረዳት። ሽቶውንና አበባውን እንዲሁም ጠቅለል ያሉ ብሮች ሰጥቶኝ እቤት ሲያደርሰኝ፡

«ለሁለተኛ ጊዜ እየላምኩ ባቅፍሽ ደስ ይለኛል። ግን የመጀመሪያው ፈተናዬ በጣም ከብዶኝ ጥርሴን ነክሼ ነው ያለፍኩት። ሁለተኛውን ግን የምችለው አይመስለኝም ስለዚህ እራስሽን ጠብቂ ከነእዚህ ደም ከሌላቸው ጓደኞችሽ» ብሎ ከንፈሬ ላይ የክብረት አሳላም ሳመኝ።

ለቅድስት የነላልዋን ሥራ ነገርኳት። ወዲያውኑ የነላልዋ ጓደኛ ጀሚላ ላይ እርምጃ ወሰደች። እነ አይሻ

እዚህ የሚመጡት እርሷን ፍለጋ ስለሆነ እርሷ መውጣት አለባት ብላ ሻንጣዋን እየገፋች ኮሪደር አደረሰችው።

የዚያን ላምንት ከልቤ ወድጀአቸው ሲሸጡኝ ስላሰቡት ጓደኞቼ ሳስብ ሥራዬን በትክክል መሥራት አልቻልኩም። ይህን አስታኮ የተፈጠረብኝም ፍርሀት ያለሁበትን ሁኔታ በጥርጣሬ እንዳይ አደረገኝ። ገንዘብ አካባቢዬን ሁሉንም ገዝቶ ከሥሩ አድርጉአል።

ምዕራፍ ሦስት

ከዚህ በፊት በዚህ አመሌ አሪፍ ሥራ እንዳጣሁ ባውቅም አመል አመል ነውና ስደጋግመው ያስደስተኛል። ታውቂዋለሽ ቀስ ብሎ ሌሎች የሚሉትን የመስማት ልምድ። ይህ ድርጊቴ ያኔ ትምህርት ቤት ሆኜ ጓደኞቼ ሲያሙኝ እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ያለኝ ፅኑ ፍላጐቴ ያሳደረብኝ ሱስ ነው። ሰዎች እኔ ሳልኖር ስለእኔ የሚሉትን እንደመስማት የሚያጓጓኝ ንግግር የለም። ትዝ ይልሽ እንደሆነ አንቺና የክፍል አለቃችን የነበረው ዳንኤል ስለኔ ስታወሩ ፊታችሁ ከች ብዬ ቀልባችሁን የገፈፍኳችሁ . . . በፊቴ ስለኔ ጥሩ ታወሩ ነበር ከኋላዬ ግን . . . ያን አስታውሺ ቂም ይዤብሻለሁ ለማለት አይደለም። ልነግርሽ የፈለግኩት ያንን ፀባዬን አልቀየርኩም።

ልክ ፊልም እንደምትቀረፅ የሴት ሰላይ እጀን ወደኋላ አድርጌ ጆሮዬን ከጉን ወዳለው ሳሎን ወረወርኩ።

ትልቋ እመቤቴ ከነባሏ እና ሰሞኑን ምክንያቱን በማላውቀው ጉዳይ ከእኛ ጋር መኖር የጀመረችው ልጃቸው ትንሿ እመቤቴ አረብኛ ፊልም ያያሉ። አልፎ አልፎ ስለፊልሙ አስተያየት ይሰማል።

የቤቱ ጌታ አፉ ላይ የሚሎጉመው የሺሻ ድምፅ «ቡም ቡም ቡም» ይላል . . . በሳበው ቁጥር። ሺሻ

አረቦች በተለምዶ እንደሲጋራ የሚያጨሱት ባህላዊ ነገር ነው። ረዘም ብሎ እንደተሠራ የሳሎን ጌጥ ይመስላል። አናቱ ላይ ትንሽ ገል መሳይ ነገር አለች። በገሏ ውስጥ የሚጠቀጠቅ መአሰል የሚባል ነገር ከፍራፍሬዎች የሚሠራ ትንባሆ ሲኖር ከበላይ የሚደረገው የከሰል ፍም መአሰሉን እንዲጨስ ያደርገዋል። ከአቃው ጉን ያለ ቱቦ የሚጨሰውን ጭስ ወደ አጫሹ አፍ ያደርሳል። ከዕቃው መሀል ያለው ውሃ ነው ጠቀሜታው ያልገባኝ። አናም ጌታዬ ጭሱን በሳበ ቁጥር እንደሚንተከተክ ውሃ እየተገላበጠ «ቡም ቡም» ሲል ጆሮዬ እየገባ የሰዎቹን ድምፅ እየዋጠ ረበሸኝ።

ለነገሩ ስለኔ አያወሩ! ለምኑ ነው ልፋቱ አያሙኝ ቢያሙኝማ በምን አድሌ።

«አሉዝቢላህ! ይህን ፊልም ያዘጋጀው መሲህ /ክርስቲያን/ መሆን አለበት» ሲል ተሰማኝ ጌታዬ።

«ሙሽሙታለደቢን /አደብ የሌላቸው/» ሚስት ደገፈች። ምን ዓይነት ፊልም ይሆን? ለማየት ጓጓሁ። መቼም የብልግና ፊልም መሆን አለበት።

ወደ ክፍሌ እየሮጥኩ ሄድኩና የቴሌቪዥን ጣቢያ እየቀያየርኩ አየሁ። ምንም ስነ ስርዓት የጣሰ ፊልም አልነበረም። ሳሎን ያለው ቴሌቪዥን የየትኛውን ጣቢያ እንደሚያስተላልፍ መላ ፈጠርኩ። ትንፋሼን ዋጥ አደረግኩኝና በቀጥታ ሳሎን ገባሁ።

«ሺሻ ልቀይር አሚ /ጌታዬ/»

የአልፈልግም ምልክት በእጁ ሰጠኝ። ሙሉ ለሙሉ ክንፉን ዘርግቶ ወደ ቀኝ ፊቱን ያዞረ ቁራ መሳይ ወፍ ያለው ምልክትን ላይ የንስር /ግብፅ/ ጣቢያ መሆኑን አወቅሁ።

«እንደዚህ መሆን የለበትም። እንዴት የንስር መንግሥት ይህን ይፈቅዳል?» የሰውዬው ድምፅ

«አሉዝዚላህ! ሴት ረዳል /ወንድን/ እንዴት አትፍታኝ ብላ ትፋረዳለች። አስር ዘመን /የመጨረሻ ዘመን/ ጮ! ጮ!» ሴትየዋ ትልቋ።

«ክፍያ! የክፈ! /ይብቃ/» ብላ ጮኸችና ትንሿ እመቤቱ ወደ ክፍሏ እየሮጠች ገባች። ልታለቅስ ወደ ክፍሏ እንደገባች ገባች። ሁሉም የአረብ ሴቶች የሚያደርጉት ነው። የአረብ ሴት እንድታለቅስ ያደረጋት ነገር የተከሰተው ከቤቷ አስር ኪሎ ሜትር ቢርቅ እንኳን ልታለቅስ እየሮጠች ከክፍሏ መግባት አለባት። ከዛ ወንበር ላይ ወይም ቶሣ አታለቅስም። አልጋ ላይ ዘፍ ብላ በመውደቅ ታለቅሳለች። ባህል ይሁን ልምድ እኔ እንጃ ወይስ ሲሞላቀቁ. . . ብቻ ሲታዘንም መሞላቀቅ ያምራል እንዴ? እንዚህ ነው የገባች። ክፍሏ ብዬድ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ስትንሰቀሰቅ እንደማገኛት እርግጠኛ ነበርኩ። እንደዚህ ስሜቷን ሊነካ የቻለውን ፊልም ለማየት ቸኩዬ ቴሌቢዥን ከፈትኩ።

ፊልሙ ያተኮረው በፍቺ ጉዳይ ላይ ነበር። አንድ ሴት ሌሕግ ባለሙያ ጓደኛዋ ስለበፊት ባሏ እያወራችላት

ወሬዋ እንደትዝታ ሆኖ በፊልሙ ይታያል። ባልና ሚስቱ እጅግ ይዋደዳሉ። ባልየው ትንሽ ነገር የሚያናድደው አይነት ነው። ሚስቴን በጣም እየወደዳት በአንዳንድ ጥቃቅን ጉዳይ ይጨቃጨቃሉ። ይጮሀባታል። ሚስትየው ረጋ ያለች ነች። ተው አባክህ ቀዝቀዝ በል እያለች ልታረጋጋው ስትጥር ይታያል። እናም እንደተለመደው በትንሽ ነገር ሲጨቃጨቁ አራሱን መቆጣጠር ያቅተውና ተሳስቶ ሶስት ጊዜ የፍች ቃሉን ይለዋል።

«ኢንተ ጣልግ! ጣልግ! ጣልግ!

/አንቺ ተፈትተሻል! ተፈተሻል! ተፈተሻል!» እናም በነዚህ ቃላቶች ባልና ሚስቶቹ ይፋታሉ።

ሚስት ቀላል ሴት አይደለችም። በሕግ ባለሙያ ጓደኛዋ አመካኝነት ከዚህ በፊት ማንም ሴት ከፍቶት የማያውቀውን ክስ ትከፍታለች።

«ባሌ የፈጣሪ በበቂ ምክንያት ስላልሆነ ይመለስልኝ» የሚል

በእስልምና ሀይማኖትና በአረብ ባህል ይህን የሚያክል ነውር የለም። እናም ይህች ሴት እናት አባቷ ያፍሩባታል። ሰው ይስቃባታል።

ክሱም በህዝብ ዘንድ የተደገፈ ስላልሆነ ብዙ ሆሆታ አስነሳ። ሁሉም ወንዶች አልደገፉትም። ሴቶችም ያልተለመደ ክስ ስለሆነ ፈርተው ስሜታቸውን ደበቁ።

እናም ለኔ ግራ የገባ ፊልም ነበር። ግን ትንሿን እመቤቴን ለምን ነካት?

«ተፋታ ይሆን እንዴ የመጣችው?» ብዬ አሰብኩኝ።

የቀዘቀዘ የሎሚ ጭማቂ ይዤ ያለትዕዛዝ የትንሿ እመቤቴ መኝታ ቤት ገባሁ። እመቤቴ አዝና ፊቷን በመሀረብ ታብሳለች። በርከክ አልኩና «የሎሚ ጭማቂ አመጣሁልሽ ቀዝቃዛ ነው እንዲያቀዘቅዝሽ!»

«እኔ እኮ አልተናደድኩም ብቻ ልቤ ተሰብሯል።» ለቅሶ ቀጠለች። ከእርሷ ጋር እንዳወራ የፈቀደችልኝ ዛሬ ብቻ በመሆኑ የልቧ መሰበር ደስ አለኝ። ልባቸው ሲሰበር የሚያዋሩት ሰው ይፈልጋሉ። ያኔ ብቻ ከፊታቸው እንደሰው ይቆጥሩናል . . . እመቤቶቹ።

«ከባሌ ጋር ተፋትቼ እንደመጣሁ ታውቂያለሽ?»

የጠረጠርኩት ነገር አልኩና ራሴን በአሉታ ነቀነቅኩ።

«ባሌ ይወደኛል በዚህ እርግጠኛ ነኝ። እኔም በጣም እወደዋለሁ። እርሱ ህይወቱ ነው። ይገባሻል! አንዳንዴ ሰይጣን በሚዋደዱ ሰዎች መሀል ይገባል አይደል? ሰው ፍፁም አይደለም እናም ፈታኝ»

«ምክንያቱን ልንገርሽ ዝም ብለሽ አዳምጪ። እርሱ እንደራሳችን እንጉር ሲለኝ እኔ ግን የአክስት ልጆቼን ጉሮ እያየሁ እንዲህ እናድርግ እንዲህ እንሥራ እላለሁ።

አይኑን አፍጦ «አይሆንም» ካለ ባሌ አይሆንም ነው። ስለዚህ ወዲያው ነገሩን ረስተን ተቃቅፈን እናድራለን። የፈታኝ እለት የአንዷ አክስቴ ቤት እራት ተጠርተን ልብስ እየቀያየርኩ ነበር። ባሉኝ ልብሶች ሁላ በያንዳንዱ ቀሚሴ አክስቴ ቤት ታይቼአለሁ እና አዲስ መግዛት እንደነበረብኝ ስነግረው እንደ አብድ ሠራው። እኔም ስሜቱን ሳልረዳ ሌሎች ባሉት ለሚስቶቻቸው እንዴት እንደሚጠነቀቁ የሚገዙላቸውን ስጦታዎች ቀሚሶች ገልጬለት እኔ ግን ባሌ ለኔ ግድ እንደሌለው እራሴ እንኳን ግላልኝ ብዬ ስለው እንደሚጮህ በምሬት ተናገርኩ። ምን እንደነካኝ ሳላውቅ እንደዛ አልኩ እንጂ እንደኔ ባል ለሚስቱ የሚጨነቅ የሚንሰፈሰፍ ባል ጥቂት ነው። በቆምኩበት ጥሎኝ ሄደ። ተከትዬው ሄጄ ነተረክኩት። እንደውም ከጥሪው እንደምንቀር ነግሬው ልብሴን ለማውለቅ ስሞክር ገና ብዙ ቁልፎች መፍታት ይኖርብኝ ነበር። በእርሱ ምርጫ ገዝቶልኝ የነበረ ቀሚሴን ከላይ ጀምሬ ተረተርኩት። ከኋላዬ ፊቱ ደም ለብሶ ተቀያይሮ ሳየው ደነገጥኩ። በእንደዚህ ሁኔታ ፈፅሞ አይቼው አላውቅም።

ትንፋሹን በሀይል ሰበሰበና «አንቲ ጣልግ! ጣልግ! ጣልግ!» አለና በደቂቃ ፈታኝ። ስነቃ እራሴን ስቼ ሆስፒታል እንደገባሁ ነገሩኝ። ከጉኔ ቆሞ አይቼው ግን እንደባዕድ ተያየን። ተፋተናላ። አይኑ እንባ እንዳዘለ ይህን እንዲያደርግ የገፋፋሁት እራሴው እንደሆንኩ ነገረኝ።

አንዱ በአላህ ፊት ስለፈታኝ ነገሩ ጊዜ ያለፈበት ሆነ። ለቤተሰቦቼ እንደፈታኝ ሲነግራቸው ክብራቸውን ስለነካ በጣም ጠሉት።

«ይታይሽ ይህ ለፍቺ በቂ ምክንያት ነውን? እንደሌሎች አገሮች ፍቺ በሕግ ቢሆን ጊዜ ይወስድና ባልና ሚስቶቹም ረጋ ብሎ የማሰቢያ በቂ ጊዜ ይኖራቸው ነበር። ፍቺ በአፍ ባይሆን በህግ ቢሆን ባሌ ከንዴቱ መለስ ሲል እንኳን ሊፈታኝ በክፉ አይኑም አያየኝም ነበር። ይመለስልኝ ነበር። በነጋታው ያቅፈኝ ነበር» አለቀሰች።

«የሚወድሽ ከሆነ ለምን እንደገና አያገባሽም?»

«ሊያገባኝ መጥቶ ነበር። ቤተሰቦቼ አልፈቀዱም! እርሱ እንደሚወደኝ በድብቅ ደውሎ ነግሮኛል። አንድ ቀን እንጋባ ይሆናል። ገላዬን ሌላ ሰው እንዲነካ አልፈቅድለትም። እኔ ለእርሱ ተብዬ እንደተፈጠርኩ አውቀዋለሁ። የእርሱ ነኝ።»

«አንቺ ከወደድሺው እርሱም ከወደደሽ ለምን ከቤተሰብ ውጪ አትጋቡም። ቤተሰቦችሽ በኋላ ይቅርታ ያደርጉልሻል። በእኛ አገር ሁለቱ ፍቅረኛሞች ከተዋደዱ የቤተሰብ ውሳኔ እንብዛም አይጠብቁም። ቤተሰብ ቤተሰብ ነው የት ይሄድብሻል ብለሽ ነው!»

«ኦው! የኛ ሌላ አይነት ሕብረተሰብ ነው። ከቤተሰብ ውጪ ሆነሽ ስታገቢ ቤተሰብሽን ብቻ አይደለም የምትረግጪው። ህብረተሰቡን ረግጠሽ . . . ባሀሉን ረግጠሽ እናም ከዚህ ሁሉ ለመውጣት በጣም ጥንካሬ

ያስፈልጋል። እርሱም ቤተሰቦቹን ያጣል እኔም ቤተሰቦቼን አጣለሁ። ይህም ለሁለተኛው ፍቺአችን ምክንያት እንዳይሆን በጣም ስለምፈራ አልደፍርም። በዚያ ላይ እናቴ የልብ በሽተኛ ናት። እኔ እራሴን መዳሬን ስትሰማ ትሞታለች። የማይሞከር ነገር ነው። ይህን ሁኔታ በፊልም አይ እንደሆነ ነው እንጂ ደፍራ ያደረገች አንድ ሱውዲያዊት አትገኝም። አንዳንዱ እናንተን የውጪ ሰዎችን መሆንን እመኛለሁ።»

ባሀሉ በትንሿ እመቤቴ የፈጠረባት ትልቅ ችግር ዓይነት ስንቱ በየቤቱ ይኖራል። እንዲያ ከሆነ ታዲያ የአረብ ወንድ ያገባና አፉ እንዳመጣለት «ኢንቲ ጣልግ!» ካለ ሦስት ጊዜ ይህን ሊያስር የቻለ የጋብቻ መስፈርታቸው ጥሩ ሰንሰለት ነው ማለት ነው። ሴቷ ከመጋባቷ በፊት የምትጠይቀው የነዋይ ብዛት . . . ታዲያ ያን ያህል ከፍሎ በቀላሉ ትዳሩን የሚያፈርስ እንብዛም ነው። ለነገሩ ሀይማኖታቸውም ጋብቻ ላይ ያለው ተፅእኖ ጥሩ ነው። ችግሩ ሴቷ መፋታት ከፈለገች ነው። ወንዱ ካልፈቀደ እጅግ አስቸጋሪ ነው። ይህ አገር ለወንዶች ያደላል። በጣም ያደላል። ለነገሩ ለተፋታች ሴት ያለው የህብረተሰቡ አመለካከት በጣም ስለሚጫናት መፋታትን እንደሞት እየፈራች ትኖራለች።

«ወይ ጉድ ይህ ሁላ ድሎት ከውስጥ ባዶ ነውን?» ብዬ ገረመኝ። እመቤቴ ላይ የቀናሁባትን ያህል አሳዘነችኝ። ጥሩ ትዝታዋን ቀስቅሼ እመቤቴን ላዘናጋት አሰብኩና

«የአጐትሽ ልጅ ነበር ባልሽ?»

«አይ አልነበረም! አይገርምም?» እውነቱን ለመናገር እኔ የሚገርመኝ ከአጐት ልጃቸው ጋር ጋብቻ የመፈፀሙ ጉዳይ እንጂ ከባዕድ ጋር የመጋባቱ ጉዳይ ምኑ ላይ ሊገርመኝ።

ቀጠለች ንግግሯን «ትንሽ እያለሁ ሁሌ አብሮኝ የሚጫወት የአጐት ልጅ ነበረኝ። ሁለታችንም ስናድግ እንደምንጋባ ከቤተሰቦቻ ን እንሰማ ስለነበር ስለጋብቻ ያለዕድሜአችን እናወራ ነበር። «ሳገባሽ እደበድብሽና ደም ብቻ አደርግሻለሁ» ይለኝ ነበር አያስቅም! ታዲያ ስንጫወት የሌሎች ዘመድ ልጆች ከነኩኝ ከቻለ ያግዘልኛል ካልቻለ አብሮኝ ያለቅሳል። እንዲህ እንዲህ እያለኝ አብረን አድገን እኔ የስምንት ዓመት ልጅ ስሆን እርሱ ደግሞ የአስራ ሁለት ሲሆን መተያየት ተከለከልን። ከዛ ጀምሮ አባያና ጠረሀ /ረጅም ጥቁር ቀሚስና ሻርፕ/ ለበስኩ። እርሱንም አይቼው አላውቅም። እቤት አንዳንዴ ከመጣ እኔ ወደ ክፍሌ እንድገባ እታዘዛለሁ።»

አቋረጥኳትና «እንዴት ከርሱ ጋር ሳትጋቡ ቀራችሁ?»

«ኦ ታሪኩ ረጅም ነው።»

«ረጅም ታሪክ እወዳለሁ። ብዙ ጊዜ መጨረሻው አስደሳች ነው» ፊቷን በፈገግታ አበራችልኝ። ቆንጆ ናት። ፈገግ ስትል አይኗ እንደመከደን ይልና ቅልብስ ረጃጅም ሽፋሽፍቶቿ ይበልጥ የሚስቡ ይሆናሉ።

«ደግሞ እንደልብ ወለድ ታሪክ አይነት ነው። የሮሚዮና የጁሌት ታሪክን አንብበሻል. . . ሙች ሙች የኔ ታሪክ ከነርሱ አይተናነስም. . . ደህና ደራሲ ቢያቀናብረው . . . ከየት ልጀምርልሽ አም . . . . ታውቂያለሽ አብረውኝ ይማሩ የነበሩ አምስት ጓደኞቼ እንደኔ ሁሉም ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ለአጐታቸው ልጅ እንደሚዳሩ ያውቁት ነበር። ነገሩ የተለመደ ስለሆነ ወንዱም የአጐቱን ልጅ አላህ ለአዳም ሀዋን እንደፈጠረለት ሁሉ እርሷን ለእርሱ የፈጠረለት መሆኗን ስለሚያምን እርሷን ሌላ ሰው ካገባ እራሱን እንደ ደካማ ሰነፍ የራሱ የሆነ ነገር ሲነጠቅ ዝም ብሎ የሚያይ ፈዛዛ ተደርጐ የተቆጠረ ስለሚመስለው የአጐት ልጁን ቢወዳት ባይወዳት አይለቅም። ታዲያ ከእነዚያ ጓደኞቼ ጋር ስለወደፊት ባሌ ላወራ የሚታየኝ እነዚያ በትንሽነቱ ያየኋቸው ሞኖሞኝ አይኖቹ ስለሆኑ እበሽቅና ንግግሬን አቆማለሁ። ጓደኞቼ ግን ልቤን እንድከፍትለት ይመክሩኝ ነበር። ምክንያቱም ሁኔታዬ እየገፋ ልጁን እንዳልጠላና ኑሮዬን እንዳላማርር ያስቡ ስለነበር ነው። ከኔ በቀር ሁሉም ስለአጐታቸው ልጅ ቀናነት መልክ ሁሌ እያወሩ ራሳቸውን በፍቅር ለማሰር ይሞክራሉ። እኔ ግን አላህ ሲያማክረኝ እንደማላገባው የነገረኝ ይመስል እንደነሱ አልሞከርኩም። በተለይ አንዷ ከአጐታ ልጅ ፍቅር ስለያዛት እራሷን እድለኛ ታደርግ ነበር። ይህች ልጅ አባቷና አጐታ ሲጨቃጨቁ ካሁን አሁን ቃላቸውን ያጥፉና የወደፊት ባሌን አጣለሁ እያለች ጭንቀቷን ስትነግረን በሳቅ እንፈነዳ ነበር።»

ባህሏ ከባህሌ ህብረተሰቧ ከእኔ ህብረተሰብ በጣም የተራራቀ ስለሆነ ወሬዋ አዲስና የሚስብ ሆነብኝ። ሳላስበው የእመቤቴ አልጋ ጫፍ ላይ ተቀመጥኩ። በጣም ስሠተት ነበር ብቻ በወቅቱ የአልጋ ጫፍ መሆኑ እንጂ የማን አልጋ ለሚለው ቁብ ስላልነበረኝ ተደላደልኩ።

«ባሌ ሙስጠፋን ስተዋወቅ ሊያገባኝ ከነበረው የአጐቴ ልጅ ጋር አባቴ የጋብቻችን ቀን ከአንድ ዓመት በኋላ እንደሚሆን ተስማምተው ለትምህርት ውጪ አገር ሄዶ ነበር።

እኔ ከታናሽ ወንድሜ ትንሿ እህቴ እና ከዳዳ /ሞግዚታቸውን የሚጠሩበት የተለምዶ ስም/ ጋር ሆኜ የገበያ አዳራሽ ውስጥ የሚገኝ የመጫወቻ ቦታ ነበርኩ። ድንገት ሁለት ጉረምሶች ሲሯሯጡ ሙስጠፋን ገፋትና የአይን መነፅሩ ሲፈናጠር እንዴት እንደሆነ ሳላውቀው ራመድ ብዬ ቅልብ አደረግኩት። በፈገግታ አየኝ። አስተያየቱንና አይኖቹን አረሳቸውም። ያለመነፅር በጣም የተዋቡ ናቸው።» ስታወራልኝ የበፊት ባሏን ፊት ለፊት የምታይ ይመስል አይኗን እያባበለች ፈገግ ትላለች አይኗን መልሳ ቡዝዝ ታደርግና ፈካ . . . እዝን እዝን. . . እኔን አታየኝም።

«ከዛ የትም ሳይሄድ እዛው የጫወታ ቦታ ቆም በዓይኑ ሲከተለኝ አየሁ። እኔን ከሌሎች ሴቶች ለመለየት አስቸጋሪ ሲሆንበት በዓይኖቼ እዚህ ጋ ነኝ አለዋለሁ። ብዙ ተያየን። መጨረሻ ላይ ጥቅልል ወረቀት ሲወረውር

ዳዳ ሻሮፕ ላይ ወደቀ። እየተጣደፈ ወጣ። ወረቀቱን ሲወረውር ያየው እንደሌለ ቃኘት አደረግኩኝና ቶሎ ብዬ ከሞግዚታችን ሻሮፕ አነሳሁና ዳዳ ላይ ጮህኩባት። ለእህት ወንድሜ ወረቀቱ የሚለውን ዋሽቼ «አንቺ እንደናቸሪያ ነሽ ወይ?» የሚል እንደሆነ ስገልፅላቸው ከፈታችን ሕሳናት ያጫወተት የነበረ አንድ ኢንደኖዢያዊ ወሳት ላይ ጮሀብት። ነገሩን መሀል ገብቼ አባረድኩ። ትነሻ እህቱ «እንደ'ት ቢደፋራት ወረቀት ይፅፍላታል» ብላ ለሞግዚታችን ተቆረቆረችና «ሚስኪኗ ዳዳ ያሚስኪኗ ዳዳ» ስትል አመሸች።

እየሮጥኩ ባኖ ቤት ገባሁና እየተንቀጠቀጥኩ የወረወረልኝን ወረቀት ስገልጠው የስልክ ቁጥሩንና የምደውልበትን ሰዓት ፅሮ ስሙን ግን አልፃፈም። የዛን እለት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለወንድ ያሰብኩበት ቀን ስለነበር ሌሊቱን እንቅልፍ አንዘ አለኝ። ልደውል አልደውል እያልኩ ሳትሚሚ ብዙ ቆየሁና ልክ ባለኝ ሰዓት ደወልኩ። ገና ባንድ የስልክ ጥሪ ብቻ ቸኩሎ ማንሳቱ እየጠበቀኝ እንደነበር አረጋጠኖ አደረገኝ። ሁለታችንም የምናወራው ጠፍቶን ሰንተባተብ ከቆየን በኋላ እንድደውልለት ተቀባብየረን ስልኩን ዘጋሁ።

ሁሉ ሌሊት የሁሉንም ስልኮች ገመድ እንድትነቀልልኝ ከዳዳ ጋር በገንዘብ ተዋዋልኩ። ሁሉም ሊተኙ እኔ መኝታ ቤቱን ዘግቼ መብራት አጥፍቼ እደውልለትና ቢያንስ ለሁለት ሰዓታት እናወራለን። ብዙ

ባወራን ጊዜም እኔም ስለቤተሰቦቼ ስለራሴ እርሱም ስለሁሉም ነገር በግልፅ ስለተነጋገርን በደንብ ተዋወቅን::»

አቋርጣ የሆነ ነገር ያስታወሰች መሰለችና ፊቷ ቲማቲም መሰለ:: የአፍረት ሳቅ ሳቀች «እ . . . » አለችና ልታወራ ያሰበችውን ከአፏ መለሰችው:: ይበልጥ አጓጓችኝ:: መጓጓቴን ላሳያት አልፈለግኩም:: ሀሳቧን ቀየረችና ያላፈራትን ጉዳይ ነገረችኝ::

«በስልክ ውስጥ ፍቅር ሰራን ታምኚኖለሽ? ፍቅር እንደ አልጋ በስልክ ይሠራል የሚል ሰው ከእኔ በቀር አጋጥሞሽ ያውቃል?»

«እ! እውነቱን ለመናገር አም!» እራሴን ነቀነቅኩ:: እመቤቴ ከሰው የተለየ ያለችው የግል አጋጣሚዋን የነጠቅኳት ይመስል አይኗን በቁጣ አፈጠጠችና «ውሸታም! ማ?»

«ዜና ላይ አላዳመጥሽም የአሜሪካኑ ፕሬዚዳንት ከክሰሰችው ሴት ጋር ነዋ በስልክ ፍቅር ሰራኝ ብላ የለም!» አልኩ በእርግጠኝነት::

«ኦ! ያ ሌላ ነገር ነው የኛ ደግሞ ሌላ:: ደግሞም ፕሬዚዳንቱ በስልክ የጠለፉበት ሪኮርድ ላይ የተገኘው ቃላት ተራ የፍቅር ቃል ነው:: አንድ ሰው ደስ ለምትለው ሴት የሚናገረው ዓይነት ለዚያውም በፍራቻ ቁርጥ ቁርጥ የሚሉ አጫጭር ቃላቶች:: ታዲያ ይህችን ቃላት ለፕሬዝዳንቱ ማግኘታቸው በስልክ ፍቅር ሠራ ለሚለው

ቃል በቂ አይደለም:: እኔ የምልሽ ሌላውን ዓይነት የፍቅር መሠራራት ነው::»

አሁን እኔ በተራዬ በአግርሞት አይኔን አፈጠጥኩ:: እንደሞኝ አፌን ከፍቼ «እ! እንዴት?» አልኩ

«መጀመሪያ የለበስነውን ልብስ በደንብ እንነጋገራለን:: ከዛ ዓይናችንን ጨፍነን አንዱ ያንዱን እንደሚያወልቅ ዓይነት የየራሳችንን ልብስ በቀስታ እናወልቃለን. . . እየተንሾካሾክን:: እራቁቴን ስሆን ከፊቴ አገኘዋለሁ:: በጨለማ ሲዳብሰኝ ይሰማኛል:: በለስለስ ድምፅ የቱጋ ልንካሽ ይለኛል ሳላፍር ወደሚዳብሰኝ ቦታ እመራዋለሁ:: ነካሁሽ ይለኛል ይነካኛል:: ሁለታችንም የእውነት በስሜት እንዋጣለን. . . እንጨነቃለን. . . እንሙሀለን:: ሰውነቴ በሙሉ ሀይሉ ሲፈልገው ይሰማኛል:: ናልኝ ብዬ አለቅሳለሁ:: እሙሃለሁ በፊት የማላውቃቸውን ዓይነት ደስ የሚሉ የሲቃ ድምፆችን ከራሴው አፍ እሰማለሁ:: ሌላ እሆናለሁ:: የምር እረካለሁ:: ሰውነቴ ሊያገኝ የፈለገውን ሁላ ያገኝ ይመስለኛል:: እደሰታለሁ:: ከዛም ከመተኛቴ በፊት ዛሬ ሌሊት ውብ ነበርሽ ይለኛል:: እንዳየኝ. . . እንደነካኝ ሁሉ ግን ግን እንዲነካኝ እንዲያየኝ እረዳዋለሁ:: የሰውነት ክፍሌን ሳልዋሽ በምችለው ቋንቋ ነግሬዋለሁ:: እርሱም እርቃኑን ምን እንደሚመስል ሊነግረኝ ሞክሯል:: ንገሪኝ እብዶች አይደለን? ንገሪኝ በየትኛው የፍቅር መዝገብ ይህን የመሰለ ተመዝግቦአል . . . ኡፍ እወደዋለሁ::» በእጇ ልቧን ተጫነች::

«ይህ ልዩ ግንኙነታችንን በሳምንት ሁለቴ ሦስቴ እያዳበርነው ሄድንና ሁሉም ነገር ቀላል ሆነልን።

አንድ ቀን ፊቴን ሲያይ እንደሚፈልግ ነገረኝ። እኔም ላየው እፈልግ ስለነበር ለመተያየት ዘዴ ቀየስን። ኩዳ ጋር የገበያ ቦታ ለመሄድ አስፈቅጄ በተቃጠርነው ሰዓትና ቦታ ተገኘሁ። እርሱም ከሩቅ ሲከተለኝ አየሁ። እንዲያውቀኝ ከአባያዬ በላይ እንደባላገር ነጭ ቦርሳ እንጠልጥዬ ነበር። እንደተነጋገርነው ሰው ወደማይበዛበት ቦታ ሄድንና እንዳቀድነው እርሱ ከፊት ለፊቴ ሲመጣ ሻርፔን የማስተካክል መስዬ ፊቴን ሙሉ ለሙሉ ገለጥኩለት። አየኝ። ሄደ።

ስደውልለት ምን ያህል ቆንጆ እንደሆንኩ ደጋግሞ እየነገረኝ የተለየ ፍቅር ሰራን።

ቶሎ ቶሎ ለመተያየቱ የግድ ዘዴ መቀየስ ነበረብን። ወፍራሟ እህቱ መሰላል ሆነችን።

ውፍረቷን ለመቀነስ በየቀኑ የስፖርት ቤት ትሄድ ነበር። እኔም ለቤተሰቤ ሰውነቴን ለማጠንከር ስፖርት መሥራት እንዳለብኝ አሳመንኩና እህቱ የምትሄድበት ስፖርት ቤት አባል ሆንኩ።

በተፈጥሮዬ ስፖርት በጣም ብጠላም የሰውነት አቋሜ ስፖርት ከሚሠሩት ያማረ ነው . . እንደምታይው ግን ለእርሱ ስል ትንፋሼ እስኪያጥር ስፖርት ሠራሁ።

ወፍራሟ እህቱ ዝጋታምና ከሰው የማይገጥም የተለየ ፀባይ ስላላት እርሷን ጓደኛ ለማድረግ ወር ሙሉ ፈጀብኝ። ለዚያውም በጣም ስለተለማመጥኳት እንደገረዷ 'ያን ስጪኝ ይሄን ግፊ ይሀን ሳቢ' እያለች አሰለቸችኝ።

ጓደኛ ከሆንን በኋላም ጓደኝነታችን እስከ ስፖርት ቤቱ ደጃፍ ድረስ ብቻ ሆነ። በር ላይ ወንድሟ ቆሞ ይጠብቃታል።

እኔም ለማየት ለዚያች አጭር የዓይን ንግግር ስል ሰውነቴ የማይፈልገውን ስፖርት በግድ አሠራዋለሁ። ማታ ስደውልለት ስለእብደታችን እያወራን ለሊቱን እንስቃለን።

ሁኔታው ቀጥሎ ሊነካኝ ተመኘ። ይህ እንዴት ይሆናል አልኩት ለዚህም መንገድ አላጣንም። አብረን ሌሊቱን ዘየድን።

እኔም ስፖርት ቤት ከመሄዴ በፊት ጣቶቼን በሚያለሰልስ ክሬም ዘፍዝፌ ጥፍሮቼን በሚያምር የጥፍር ቀለም አስዋብኳቸው። ሹፌሬን ዘግይቶ እንዲመጣ ገንዘብ ስለሰጠሁት ከጓደኛዬ ጋር ከስፖርት ቤቱ ስንወጣ በር ላይ አላገኘሁትም።

ጓደኛዬን ሹፌሬ እስኪመጣ አብራኝ እንድትቆም ጠይቄአት እኛ የገመትነውን ጥያቄ ጠየቀችኝ። 'እናድርስሽ?' ለደግነቷ እያመሰገንኳት በደስታ የፍቅሬ መኪና ውስጥ ገባሁ። እንደተነጋገርነው እጆቼን የፊት ወንበር ላይ እንደቃልድ ሳስቀምጥ የኋላ ማርሽ አስገብቶ

ወደ ኋላ ሊያይ እንደመዞር አለና የወንበር ድጋፍ ላይ የነበሩትን ጣቶቼን ጫን ሲላቸው መላ አካላቴ ሲነድ ተሰማኝ።

ንገሪኝ እስቲ ሮሚዮ ጁሊየትን ሲሰማት እንደኔ የተሰማት ይመስልሻል?! በጭራሽ! የአለም አላሳሞች ያህል ሊመስጡ አይችሉም። ነፍሴ ጥላኝ ሄዳ ነፍሱን ያመጣችልኝ መሰለኝ። በትንፋሹ ተነፈስኩ።

እህቱ ደንግጣ ወንድሟ ሳያስብ እንደነካኝ ስላሰበች ይቅርታ ጠየቀችኝ። የምትለው ጠፍቷት እየተንተባተበች እጅሽን የፊት ወንበር ላይ ማስቀመጥሽን አላየም። ይህንን ጉዳይ ለማንም አትናገሪ። ወንድሜ ስነ ስርዓት ያለው ሰው ነው።' አለችኝ።

የተሸፈነ ፊቴ በደስታ እንደፈነደቀ ጥፋተኛዋ እኔ እንደሆንኩና ነገሩን አንድትረሳ ነግሬአት እቤት አደረሱኝ። ሹፌሬ ላይ በእናቴ ፊት ለይምሰል ጮኽኩበትና እናቴም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጠችው። ነገሩ ሳይታወቅብኝ የምወደውን ወንድ አካል ነካሁ።

በዓመቱ መጨረሻ በሙቀቱ ጊዜ ሁልጊዜ ወደ ውጭ አገር ከቤተሰቤ ጋር መሄዱ የተለመደ ስለሆነ ይህን ጊዜ ጠብቄ ለንደን እንደምንሄድ ነገርኩት። እዛ በሄድን በሳምንቱ ለእኔ ሲል እዛ ድረስ መጣ።

ለንደን እያለን ከእናቴና እህቴ ተለይቼ ለመውጣት ብሞክርም የማይሆን ሆነ። በስልክም እንደበፊቱ ፍቅር መሥራት አልቻልንም። ላብድ ደረስኩ። ደውዬ እዚያው

ለንደን ከእርሱ ጋር ለመቅረት እንደምፈልግ ነገርኩት። ይህ የማይሞከር ነገር ነው ረጋ በይ አገባሻለሁ' አለኝ። ስለጋብቻ ሳስብ ፈራሁ። አባቴ ቃሉን የማያጥፍ ክባድ ሰው ስለሆነና ያጨኝን የወንድሙን ልጅ በጣም ስለሚወድ ጋብቻችንን እንደማይቀበል እርግጠኛ ነበርኩ።

እንደምንም አንድ ቀን ካለንበት ሳንርቅ ተደብቆ እንዲያየኝ በደንብ ተነጋግሬን እየፈራሁ ከዳዳ ጋር ተደብቄ ወጥቼ እንደተባባልነው አባያና ሻርፔን አወለቅኩና ቆምኩ። ካንድ በኩል የካሜራ ብልጭታ አየሁ። ፎቶ እንዳነሳኝ ሳረጋግጥ አባያዬን ልለብስ ስል ድንገት እናቴ እራሷን ይዛ አየሮጠች መጣች። ፀጉሬን ጨምድዳ አስለበሰችኝ። እናቴን እንደዛ ስትሆን አይቼአት አላውቅም። የዛን እለት 'ልጅሽ ሽረሞጠች' እንደተባለች እናት ታማ ተኛች። ደጋግሜ እንድሰግድ አስገደደችኝ። ለአባቴ 'ልጃችን አበደች እንደ አውሮፓዎቹ ስድ ሴቶች እራቁቷን ሄደችልህ። ፀጉሯን ከፈተች። ደግነቱ ማንም ሳያያት አንቂ መለስኳት። ልጅህ በገዛ እግሯ ገሀነብ ስትገባ ማየት አልፈልግም። የወንድምህን ልጅ የጋብቻውን ጉዳይ እንዲያፋጥን አስታውቀው። ቶሎ ታግባና እኔም ልረፍ። አልፈርድባትም።' ስትለው ሰማሁ።

እረፍታችንን ሳንጨርስ አባያዬን ባወለቅሁ በነጋታው ወደአገራችን መጣን።

ሙስጠፋ የጋብቻችንን ሁኔታ ለቤተሰቦቹ ተናገረ። የእርሱ አጐት ልጆች በሙሉ ወንዶች ስለሆኑ ቤተሰቦቹ

ክፉዕድ ጋር ለሚያደርገው ጋብቻ አልተቃወሙም። ስለቤተሰቦቼ በደንብ አጥንተው ለጋብቻ አባቴን ጠየቁት።

አባቴ ለአጐቴ ልጅ ቃል መግባቱን ገልፆ ጋብቻውን ሳይቀበል ቀረ። በአባቴ ውሳኔ ህይወቴ ወደ አሳት የሚጣል መሰለኝ። ከሙስጠፋ በቀር ማንም ቢሆን ከልቤ በር እንደማይደርስ አውቀው ነበር። የአጐቴ ልጅ ነገሩን እንደሰማ ትምህርቱን ትቶ ሊያገባኝ በፍጥነት መጣ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሙስጠፋ ከእርሱ በቀር የማንም እንደማልሆን እየማለ ያሳምነኝ ነበር።

ካጐቴ ልጅ ጋር የተደረገው የሰርግ ቀጠሮ እየቀረበ ሲመጣ እየደወልኩ ማልቀስ ብቻ ሆነ ሥራዬ።

የሰርጌን መቃረብ እንደሞቴ መቅረብ ቆጥሬ ተሰቃየሁ። ሙስጠፋ የአጐቴን አድራሻ ጠይቆ ከወሰደ በኋላ ትንሽም ቢሆን ተስፋ አደረግኩ።

አጅሬ በቀጥታ ሄዶ እንደሚወደኝ ነገረው። የአጐቴ ልጅ እንደእብድ ሠራው። ነገውኑ እንደሚያገባኝ ዛተ። ሙስጠፋ ግን ንግግሩን ቀጥሎ በደንብ እንደሚያውቀኝ ነገረው። ፀጉሬና ፊቴ እየታየ ለንደን ያነሳኝን ፎቶ አሳየው።

እጮኛዬ «ለሌላ ወንድ የታየችን ርካሽ ሴት አላገባም» ብሎ ወደ ትምህርቱ ተመለሰ። ቤተሰቦቼ ላደርስኩባቸው እፍረት ወዲያው ላየኝ ወንድ መዳር ግድ ሆነባቸው። ብዙም ሳይወዱ እኔና ሙስጠፋ ተጋባን።»

ንግግሯን እንደጨረሰች አፈጠጠችብኝ። «አንቺ ምን ላይ ነው የተቀመጥሺው!! ባዋራሽ ገረድነትሽን ረሳሽው ወይ? አልጋዬ ላይ! ከአልጋዬ አውጭ! ውጪ! የአልጋ ልብሱን አንሺና ሌላ ቀይሪ!» ብላ በመጠየፍ አልጋዋንና እኔን አየች። ያን ሁሉ ታሪክ አዳምጬ አብሬአት ባስተሳዝናትም ያው ከዳማ /ገረድ/ ነኝ።

ምዕራፍ አራት

ቤቱ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ሳላየው አንድ ቤት ሊኖረው የሚችለውን ስፋት በህልምሽ አልሚ ቢሉኝ እንኳን ላልመው አልችልም። በምንኖርባት አለም ውስጥ ጉረቤታችን የነበሩት የነባንቺ ቤትና የነዚህ ሰዎች ቤትን ያህል ልዩነት ከየት ሊመጣ?! ማማቴ ላይቀር እላይ ቤት እሰማይ ሄጀ አንድዬን እንዳማ ቢፈቀድልኝ መቼም ለሰው ልጆች ልዩነት ከዚህ ሌላ ምን ማስረጃ ሊገኝ!

ከስተማ ከተማ ይጠራሩ ይመስል እናትና ልጅ ባንድ ቤት ሆነው ካንዱ ክፍል ወደሌላኛው በስልክ ያወሩና አንዱ ክፍል ላይ እንዲገናኙ ይቃጠራሉ።

እኔም የተሰጠኝን ጊዜ ጠብቄ ሥራዬን የምጀምረው ባሎቻቸው ሥራ ከሄዱ በኋላ አበቦችን ከነጨዛቸው ቆርጦ አስተካክሎ ለእመቤቴና እናቷ ከእንቅልፍ የመንቂያቸው ሰዓት ሲደርስ አበባ ይዤ በመግባት በደመቀ ፈገግታ «ሰብሀ አልኬር /እንደምን አደሩ/» ብዬ መስኮት በመክፈት ንፁህ አየር አስገብቼ እመቤቶቼን እቀሰቅስና «ጣዛጅ አሲር» /ትኩስ ጭማቂ/ በማቅረብ ነው።

እመቤቴ ለያሙ ዝግጅት ገና አስራ አምስት ቀን ሲቀረው እናት አባቷ ቤት ገባች. . . እኔም አብሬአት። ይህ የያም ወቅት ቤተሰብ ለመሰባሰቢያ የመረጠው ወቅት

በመሆኑ ብዙዎቹ ይህን ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ለመቀራረቢያ ከያሉበት ለመሰባሰቢያ ይጠቀሙበታል።

ያሙ እስኪያበቃ ብቻ የምንቆይ መሆኑ በጅኝ እንጂ የዚህ ቤት ሥራ ሙትት ያደርጋል።

ታዲያ ከጠዋት እስከማታ በዚህ ባህር በሚያክል ቤት ስዋኩብ እውልና ወደ ማታ እግሮቼ ይዝላሉ። ለመኝታ ወደተሰጠኝ ክፍል ማምራት እራሱ ትልቅ ሥራ ነው። ብዙ ደረጃዎችን አልፎ የቤቱ አናት ላይ ከተወጣ በኋላ እንደ ቀልድ የተገነቡት ክፍሎች ከወጥ ቤት ሠራተኛ እንስቶ እስከ የፅዳት ሠራተኞች መኝታዎች ናቸው። ሁሉም ሲለፋ ስለሚውል ድንገት ሊገጣጠም ብቻ የቸልታ ሰላምታ ተለዋውጦ ክፍሉ ገብቶ ቶሎ አልጋ ላይ ለመውደቅ ይቸኩላል።

እንደዛ ደክሟቸው ቶሎ የማይተኙ ሲያስካኩ የሚያመሹት አዲሶቹ የሥራ ጓደኞቼ ሜሪና ክሬስ ከኔ ቀጥሎ ባለው ክፍል እስክለምዳቸው ድረስ መኝታ ነስተውኝ ነበር።

ሜሪ በጣም ወጣት መስላኝ ነበር። ዕድሜዋን እስከነገረችኝ ጊዜ ድረስ። አጠር ያለች ልጅ እግር ናት። መጀመሪያ ሜሪንና ክሬስን ሳያቸው ክሬስ አሮጊት ከመምሰሏ በቀር ሌላ ምንም የመልክ መለያ የሌላቸው እህትማማቾች መስለውኝ ነበር። በኋላ ግን ክሬስ በሁለታቸው መካከል ስላለው የመልክ ልዩነት አስረዳችኝ።

ስኔ ግን ሁለቱም ፊሊፒኖች ትናንሽ ቅድ አይኖችና ድፍጥጥ አፍንጫ ያላቸው ተመሳሳይ ፍጡሮች ናቸው።

በሥራ በጣም ይተጋገዛሉ። ቋንቋቸውን መስማት በጣም ቢያስጠላኝም የውሸት ለመውደዴ ማስረጃ ብዙ ጊዜ በፈገግታ አያቸዋለሁ። በዕድሜ አነስ ያለችዋ ሜሪ በፍቅር ዓይን ታየኛለች። ክሬስ ግን አይኖቿን በጥላቻ ታሰፋቸዋለች። ለዚሁ መፍትሔ እንዲሆነኝ ከሥራዬ ውጪ ክሬስን ልረዳ ብሞክርም ሙከራዬ ሳይሳካ ቀረ። ይልቁንም ይበልጥ እንድርቃት በሁኔታዋ አስረዳችኝ። ችግሩ እርሷን ብቻ እንድርቃት ብቻ ሳይሆን ሜሪንም እንዳናግር አለመፈለጓ ነው።

ሜሪ ከመተኛቷ በፊት እኔ መኝታ ቤት መጥታ ልታሳስቀኝ ስትሞክር ክሬስ ከስነስርዓት ውጪ በሬን በርግዳ ሜሪን ጮትታ መውሰዷን ልማድ አደረገች። ሜሪም እየሳቀች «ምን ያህል ተፈላጊ እንደሆንኩ አየሽ?!» ትልና ተጮትታ ለመወሰዷ ምንም ቅሬታ አይታይባትም። ብቻ በነጋታው ከሥራ መልስ እንደገና ብቅ ብላ ታዋራኛለች። እየቆየን ስንሄድ የሜሪ ወሬ የሚናፍቀኝ አይነት እየሆነ መጣ። ብቻ ብቻ የሜሪ ከልክ ያለፈ ፍቅርና የክሬስ ከልክ ያለፈ ጥላቻ ምክንያቱ አልገባኝ አለ።

ሜሪ ስለህዝቦቿ ብዙ አወራችልኝ። ስለአረብኛ ሙዚቃ ያላትን አስተሳሰብ ግን ተቃወምኩ . . . ስለወንድ ደግሞ የተለየ አገላለፅ አላት።

ቴፕ የሚጫወተውን ዘፈን ፀጥ ብላ ስትሰማ ቆየችና

«ታውቂያለሽ! ይህን ዘፈን ብዙ ጊዜ ሰምቼዋለሁ ከሌሎች አረብኛ ሙዚቃዎች ይህ ደስ ይለኛል። የኛ ሙዚቃ ቅንብር ቢበዛ የሰባት ሰዎች ሥራ ነው። አረቦቹ ግን ድርድራቸው ለቁጥር ያስቸግራል። ቫዩሊናቸውን እንቀው የሚወዘውዙ ብዙዎች ናቸው። ይህ ሁላ አንድ ድንዙዝ ሙዚቃ ለመፍጠር ነው።» ሳቀች።

« ኡ. . . ኡ. . . አትሳሳቺ! የአረቦቹ የሙዚቃ ቅምር ጥልቅ ነው። ጥልቀቱን ለማየት ቃናውን ለማጣጣም ትዕግስት ያስፈልግሻል . . . ፀጥ ጭለሽ ማዳመጥ። ከአመት በፊት እኔም አረብኛ ዘፈን ከመስማት ይልቅ ቶሎ ደሜ ገብቶ የሚወዘውዘኝን የአሜሪካኖቹን ወይንም የእንግሊዞችን ሙዚቃ እመርጥ ነበር። ግን አረብኛ ሙዚቃ ጋ ስመጣ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነብኝ። ብዙ ሰዎች ተደርድረው ቫዮሊንን ሲያናግሩ ዘመናዊ ያለመሆናቸው እንዳይመስልሽ . . . ለሙዚቃ ያላቸው ክብር ነው። በዚያ ላይ እንደኔና እንዳንቺ አገር ቋንቋ እየተከፋፈለ የሚነገር ቋንቋ ስለሌላቸው አንድ መሰረት ባለው ጠንካራ ቋንቋቸው በሙዚቃ ውስጥ ማለት የፈለጉትን በሰፊ ስልት ይጠቀማሉ። ስለፍቅር ማለት ቢፈልጉ ብዙ ብዙ የቋንቋ መንገድ አላቸው። ሰምና ወርቀ የፍቅር ቃላቶቻቸው ከሙዚቃ ቀመራቸው ጋር ተስማሚ ነው። እስቲ አረብኛ ሙዚቃን ለሳምንት ያህል ስሚ ሙች

ፍቅር ይይዝሻል። የሆነ የተሸፈነ ነገርን በስሜት ለመክፈት እስክትዋትቺ ድረስ ይዞሽ ጭልጥ ይላል።»

የሙዚቃ ገለፃዬን በልዩ መንፈስ ከንፈሯን አፏ ውስጥ ከትታ ስታዳምጥ ቆየችና «ልስልስና ስሜታም እንደሆንሽ አሁን ገና አረጋገጥኩ» አለችኝ።

ባሰኜ አገላለፅዋ አዲስ አልሆነብኝም። የሜሪ ቃላቶች ግማሻቸው ከብልግና መዝገበ ቃላት የተወሰዱ ናቸው።

«ገረብ ናር ለጊራ ገረብ ናር ለጊራ /የቅናትን እሳት ሞክር/ ኢሊ ኡሊ ኤ ራይክ አል ሳብሪ /ንገረኝ ንገረኝ አስተያየትህን ለትዕግስቴ/» ትላለች ዘፋኝዋ የቅድሙ ዘፈን ቀጥሏል። ሜሪ አስተያየቷን ለዘፈኑ ትርጉም ሰጠች።

«ሴትዮዋ ባሏ ያስቀናት ነበር። ልታስቀናው ሞክረች። የቅናትን እሳት አስሞክረች። እናም እርሱ ሲያስቀናት ለታገሰችው ትዕግስት ከቀና በኋላ አስተያየቱን ጠየቀች። ግን የዚህ አገር ሴት ይህን ልታደርግ ትችል ይመስልሻል? የት ዕታ? ተከፍታ ፊቷን አሳይታ የቱን ወንድ አስቀንታ ልታስከትል?! የማይሆን ነገር ነው። ዘፈን ብቻ ሆኖ መቅረቱ ያሳዝናል።»

ድንገት ፊቷ ተለውጦ በቁጭት እራሷ ነቀነቀችና ንግግሯን በከረሩ ቃላት ቀጠለች።

«አንዳንዴ ሴቶችን በወንድ ላይ አስነሺና መኪና ባደባባይ ንጅና በሰይፉቸው ተቀጪ ተቀጪ ይለኛል። የወንድ ግዞት አያበቃም . . . በሁሉም አገር። የዚህ አገሩ ግን የተለየ ነው። ማን ነውና ወንድ በተፈላጊነቱና በበላይነቱ በህይወታችን የሚጫወተው?! ወንዶች በጣም እራሳቸውን ይወዳሉ። በጫንቃችን ላይ ሆነው ሁሉ ያለእነርሱ መኖር የማንችል ደካማ ፍጡሮች አድርገው በኃይለኝነታቸው ይመካሉ። ቢሆንም የፊሊፒን ሴቶች ይሻላሉ።»

«የፊሊፒን ሴቶች እራሳቸውን ለወንድ አሳልፈው ካልሰጡ በቀር ለግዞት ግዴታ የለባቸውም። እንደኔ ነፃነታቸውን አውጀው ወንድን ከህይወታቸው ካገለሉ ተገላገሉ ማለት ነው። የዚህ አገር ሴቶች ግን ያሳዝናሉ። እዚህ አገር ገና ስገባ ያስደነገጠኝ ወሬ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ . . . ሴቶች አይሾፍሩም። መቼም ሴት ሆና መልኳን በማሳየት ፀጉሯን በትና በመኪናዋ መሽከርከሩ የመጀመሪያ ህልሟ ነው። እናም በጥቂቱ መኪና እንኳን መንዳት ተከለከሉ . . . በየትኛው ህግ . . . በወንዶቹ ህግ። ወንዶችን እጠላቸዋለሁ። እኔ ለመፈጠሬ ዋና ምክንያት ወንድ ነው። ለመኖሬ ምክንያት እንዲሆን ግን በፍፁም አልፈቅድም።»

ስለወንድ አዕምሮዋን የመረዘ የህይወት አጋጣሚ እንዳላት ባውቅም እንድትነግረኝ ልጫናት አልፈለግኩም።

«ሜሪ ወንድም እንዳለሽ ባላውቅም አባት እንዳለሽ ግን እርግጠኛ ነኝ ታዲያ አባትሽ ወንድ መሆኑን አትርሺ!»

«ወንድ ስጠላ ቁጥር አንድ ብዬ የጀመርኩት ከአባቴ ነው::»

«አባትሽን?» ፈራቷት:: «አዝናለሁ አባትሽ ሳያስከፋሽ አይቀርም::»

«እኔን አይደለም እናቴን ነው:: ስለዚህ ማንም ወንድ ወድጄው እራሴን እንደናቴ ልሰጠው አልፈልግም::»

«ወደሽ አታውቂም?»

«አውቃለሁ ግን ሸሽሁት»

«የወንድ ግንኙነት አልነበረሽማ?»

«ነበረኝ ብዙ . . . ግን የሚወዱኝ እነርሱ ነበሩ መጨረሻ ላይ እንድወድህ ልታደርግ አልቻልክም ብዬ ስሜታቸውን ጉድቼ እለያቸዋለሁ::»

«ህይወትሽን ለምን እንዲህ ታሰቃያለሽ? ከምትጐጂ አቸው ይልቅ ያን የወደድሺውን ባትሸሺ ትልቅ ደስታን ታገኚ ነበር»

«ለወንድ የምትከራከርን ደካማ ሴት እጠላለሁ::»

«ጥይኝ እንጂ ህይወቴን የከበቧት ወንዶች ናቸው:: ከአባት ፍቅር ጀምሮ የወንድም ፍቅር ለእኔ በህይወቴ እጅግ ጠቃሚ ነው:: በዚያ ላይ ብዙ አልሞከርኩም እንጂ

ወንድ ልቤን ስንጥቅ ያደርጋታል:: ደግሞም ወንድ ሁሉ አንድ አይደለም::»

«አምን ወንዶች ይለያያሉ ግን ባንድ ነገር ብቻ አንድ ናቸው. . . ለኛ ለሴቶች ያላቸው አስተያየት አንድ ነው::»

ሜሪ ለወንድ ያላት ጥላቻ አሁን የደረሰችበት ቦታ ያደርሳታል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር:: የአባቷንና የእናቷን ታሪክ በዝርዝር ባትነግረኝም የጥላቻዋ መንስኤ አባቷ መሆኑ ነው:: ይኸው ያስተዳደጓ ሚስጥር በህይወቷ ገንፍሎ ወጣ::

* * * * * *

የአለባበሷ ጉዳይ ሙቀቱን በተመለከተ እንደሆነ ገመትኩ:: አልያም ፊሊፒኖች ሴት ለሴት አይተፋፈሩ ይሆናል . . . እኔ እንጃ:: ብቻ ሁኔታዋ ልክ አንድ ለዓመታት የናፈቀችው ፍቅረኛዋ የሚመጣና ልብስ በማወላለቅ እንዳይደክምባት ያሰበች ያስመስላታል. . . እራቁቷን ነች እንዳይባል ብቻ ለይምሰል ቅንጥብጣቦ ጨርቆች ጣል አድርጋለች::

«ሃይ ሜሪ ኬፊክ» አልኳት በጣም ገርሟኛለች:: «ሙዚቃችንን ወደድሺው ባኛ ቤት እያለሽ እንድትሰሚው

ፊልጌ ነው ጮኽ ያደረግኩት። በእርግጥ የባኛ ቤት ሙዚቃ ነው።»

«ደስ ይላል ትርጉሙ ባይገባኝም»

ትርጉሙ ከጨረቃ ስትወለጂ አየሁሽ . . . ምናምን . . . የፍቅር ዘፈን ነው። ባኛ ቤትማ ከሰማሽው የውሀው ሙቀት ይበልጥ ይሰማሻል» ከትናንሽ አይኖቿ አንዱን ረገጥ አደረገች።

ሜሪ ብልግና ማውራት ትወዳለች። ወሬዋን እኔም አልጠላሁትም። ብቻ ባለጌ ናት። ደስ ትላለች።

«ኢትሽ ናይሽ» ሁሉም ፊሊፒኖች መሆናቸው ነው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በዝ' ድምፅ 'ሰ' ወይንም 'ሽ'ን ይጠቀማሉ። የሜሪ እንግሊዘኛም ቅምጥል ያለ ይመስላል። ትናንሽ አይኖቿ ይበልጥ አናንሰዋል. . . ልጅቷ ምን ነካት?

«ምን ትጠጪያለሽ?» ወደ ፍሪጅ አመራሁ። ከተጋደመችበት አልጋዬ ላይ ተንጠራርታ ያገለደምኩትን ፎጣ ሳበችብኝ። አፈርኳት። ፎጣውን እንድትሰጠኝ ባንድ እጇ እየለመንኩ ስታገላት በሌላው እጇ አንዴ ጡቶቼን አንዴ ጭኔን ለመሸፈን እየጣርኩ ነበር።

አፍረቴ ወደ ንዴት ሲለወጥ ግን እንዲህ አልኳት «ምንድን ነው? አንቺ የሌለሽን የአካል ክፍል ብቻዬን አልያዝኩ። ደግሞም የሚያሳፍር ገላ የለኝም። እይኝ ጠንብሽ በደንብ እይኝ!» ጮሁኩባት።

በጣም እየሳቀች «እስኪ ዙሪ። ከኋ. . ላሽ አሳይኝ ኦ ኦ. . .» ተንከተከተች።

«ይኸው» ከፊት ለፊቷ ይበልጥ ቀርቤ ተሽከረከርኩ። ካደግሁ በኋላ ገላዬን እናቴ እንኳን እንዳታይብኝ እጠነቀቅ ነበር። ከወንዶች መሀል አንድ ሴት ሆኜ ስላደግኩ ነው መሰለኝ እራቁት ከሰው ፊት መቅረቡ እጅግ ከባድ አጋጣሚ ነው ለኔ።

ሳቋ ቀዝቀዝ ሲል ተመለከትኳት። ላመሉ ጣል ያደረገችውን ጨርቅ ከላይዋ ላይ ሳብ ሳብ አድርጋ መሬት ጣለችው. . . እርሷም እራቁቷን።

እንደ መዳህ እያለች ነጭ ገላዋን ወደኔ አስጠጋች

«አ! በፍቅርሽ ወድቄአለሁ። ሳታውቂው የቀረሽ አይመስለኝም። ካየሁሽ ጀምሮ በፍላጐት ነደድኩ። ተጠጊኝ። ነይልኝ።» የማየው ነገር ግራ ገባኝ። እንዲህ አይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። ሁኔታዋ አስፈራኝ። ሸሸኋት ተጠጋችኝ ምላሷን ዘርጋ ክትት ስታደርግ ምላሷ አሰው ዘር ምላሶች ረዝሞ ታየኝ። ዘገነነኝ።

ሜሪ ፍፁም ተቀይራ እየዳኸች ትጠጋኛለች። እኔ እሸሻታለሁ. . . ትጠጋለች. . . እሸሻታለሁ። በጠባቧ መኝታ ቤት ተሽከረከርን። ግራ ገባኝ። ከንፈሯ ላይ ማር ያለ ይመስል አስሬ ምጥጥ እያደረገች በአገጯ ልክ የተቆረጠ ፀጉሯን ምስቅልቅል ስታደርገው በፍርሀት

ተርበተበትኩ። ምን ዓይነት ዓለም ውስጥ ልትከተኝ አሰበች? ሰይጣን!::»

«እ! ተቃጠልኩ ቅረቢኝ ውዴ! የኔ ውድ?»

እራሴን ቆፍጠን አድርጌ «ከእኔ ምን ትፈልጊያለሽ? ሜሪ ነገርኩሽ እንዳትጠጊኝ!»

«ገላሽን ሙቀትሽን ልስላሴሽን ወጣትነትሽን ገባሽ? አሁን ምን እንደፈለግኩ። በጣም ተመኘሁሽ። ለዛሬ ገላሽን ስጪኝ ወደፊት መንፈስሽንና ልብሽን ትሰጪኛለሽ። ልብሽ ላይ እንድደርስ መሰላሎቼ እነዚህ ጡቶችሽ ናቸው። ጫፋቸው ያስጐመጃል ልክ ቸኮሌት ላይ እንደተነከሩ ቼሪዎች ናቸው።

የገዛ ገላዬን እያየሁ «ገላዬን?» አልኩ።

«አዎን ገላሽን አየሽ ጡቶችሽ ይፈልጉኛል። አላልኩሽም ውስጥሽም ሲገር ይታወቀኛል። አታፍኚው .»

ፊቴ በሀይል ሞቀኝ። ምክንያቱ በማፈሬ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ፈለግኩ። አፍሬ መሆን አለበት እንጂ ይህ ሰይጣናዊ ስሜት እኔ ውስጥ መወለድ የለበትም። እራሴን ላሳምን እየጣርኩ ሳለ ሜሪ ደርሳ ያዘችኝ።

አይኗን እና አፍንጫዋን ጨምሮ እንደምርቃት ቁጭ ቁጭ ያለ መልኳና ከአጭር ቁመቷ ጋር ያለው ሚጢጢ ሰውነቷ እንደ ጭራቅ ገዝፎ ኃይልን ተላብሶ ልክ እንደደንዳና ጉረምሳ ጭምቅ ሊያደርገኝ አዕምሮዬ ያልተቀበለውን ወሲብ ሊፈፅምብኝ ከፊቴ ተደቅኖ እኔ ያለ

ምንም አጋዥ ተስፋ ቆርጬ ካሁን አሁን አነቀኝ እያልኩ የማነባ መሰለኝ። አዕምሮዬ በከባዱ ፈተና ተሰቃየ።

ፈዝዤ ቆምኩ። ቀስ ብላ ተንበረከከች። እግሮቼን ከሸር ጀምራ እስከላይ ስታረጥባቸው ተሰማኝ። ውስጤ ተረበሸ። ለምን? እርሷም ሴት! እኔም ሴት! ግን ለምን? እኔንጃ!»

«እንዴት እንደምታፈቅሪኝ አስተምርሻለሁ! እ! ቃል እገባልሻለሁ! አዎን በጣም ትሞቂያለሽ ፍቅርሽ እንደ እሳት ነው አዎን አቃጥይኝ አዎን . . . ወደሽዋል አየሽ . . . ወደሽዋል።»

ያበሻ አምላክ መስቀል ይዞ

«ተይ ይህን ሰይጣን ስሜት አትቀበይ። ህይወትሽን በምድርም በሰማይም ያቆሽሽብሻል። ተይ!»

ሜሪ ከሌላው ጐን

«ላሳይሽ ያላየሽውን። ማየት ምን ሊያመጣ ?

አትከሰሪም ሞክሪ ደስ ካላለሽ ትተይዋለሽ» ፊቷ ላይ የሚርመሰመሰው ፈገግታ ደስ እንደሚለኝ እርግጠኛ የሆነች ያስመስላታል።

ፊቴን ወደ አበሻ አምላክ ሳዞር እናቴን ወንድሞቼ አገሬው ሁሉ ተሰብስቦ «ቱ በስመአብ ቱ» ይሉኛል።

ሜሪ ነጭ ገላዋን ከፊታቸው ሳታገል ትጋፈጣቸዋለች።

«ኑ እኛ የደረስንበት እናድርሳችሁ»

ከተሰበሰቡት አንዱ «ፐ ይህን ስልጣኔ ማድረን ነው?»

«ውሻ ለምን? ስማ አንተ አበሻ እራሴን መሆን መፈለጌ ውሻ አያስብለኝም::»

«እንደውም የሴት ውሻ ነሽ»

«ውሻ ውሻ ነው ምን ልዩነት ሊያመጣ:: ሴት ሆነ ወንድ አየህ እዚህ ላይ ስረታህ:: እናንተ ወንዶች አንፈልጋችሁም ስንላችሁ መቋቋም ያቅታችኋል:: እስካሁን ገዛችሁን አሁን ስሜታችንን እንኳን ልንሰጣችሁ አንፈልግም:: ምንም አይደላችሁም:: ወንዶች ምንም አይደላችሁም::»

የአበሻ አምላክ መስቀሉን እንደያዘ

«ይህን ፀያፍ ነገር ቆሜ የማዳምጠው ላንቺ ስል ነው:: ራቁትሽን መቆምሽ ለምንድን ነው? ተይ! ልበሺ ተይ!»

ሜሪ የኔን ፋንታ አፏን ሞልታ ትከራከራለች::

«ራቁቷን ስትሆን ስለምታምር ነዋ:: ልብስ መልበሷ ራሷን ልትሸፍን ነው?! ለምን መሸፈን አስፈለጋት:: ነፃነቷን ስጣት:: ተዋት ትይበት:: ደግሞ ብዙ ጊዜ ትሰጣት ይመስል» አፏን አሽሚጠጠች አምላኬ ላይ::

እናቴ እራሷን ደፍታ ስትሄድ አየኋት:: ከመሄዷ በፊት ግን «ልጄ እኔ ለዚህ አልላኩሽም:: እራስሽን አታበላሺ! አደራሽን ልጄ!» ሁሉም አበሾች እንዳዘኑ ሲወጡ የአበሻ አምላኩም ተሰወረ::

የሜሪ ሰውነቴን መጨምደድ ከሀሳቤ አባነነኝ:: ሀሳቤ ርቆ ሄዶ ስለወሰደኝ ምን እያደረገች እንደነበር ከማቃስቷ በቀር አልተሰማኝም:: በስሜት እና በአዕምሮዬ መሀል ለማንም ሳልዳኝ ቆየሁ:: አረቦች የልብ ሀሳብና የአዕምሮ ሀሳብ የተለያየ ነው ይላሉ:: ልብ ስሜታዊ ሀሳቦች ያመነጫል:: አእምሮ ደግሞ ረጋ ያለ ሀሳብ ያመነጫል ባይ ናቸው:: እንደኔ ሁለት ሀሳቦች ሲጋጩባቸው «ገልቢ ዋላ አቅሊ» /በልቤ ወይስ በአዕምሮዬ/ ልወስን ይላሉ:: ታዲያ እንደሚሉት «ብገልቢ አሰልሚክ /በልቤ ላዋራሽ/ ወይስ «ብአቅሊ»

የልቤ መልስ ደካማ ነው ማየት ፈለግኩ:: ሜሪ እንዲህ እንድታቃስት አይኖቿ እንዲያናንሱ እንደ ህፃን እንድትድህ ያደረጋት ሪል ማየት::

የአዕምሮዬ መልስ ፍራቻ ነው:: ፍራቻ. . . ከሰው ከባህል ከራሴ ፍራቻ ከሱስ:: እራሴን አጥቼ ሌላ ሰው ለመሆን ፍራቻ:: ታዲያ ያ ባህሌ ከልሎ ያሳደገኝ መጥፎ ፍሬ እንዳልሆን አስቦ እንደሆነስ? አዕምሮዬን በግድ ተቀበልልኝ ማለቱ . . . እኔንጃ . . . ይታይሽ ይህ ባህሌን እጅግ የሚያከብረው አዕምሮዬ . . . ከጋብቻ በፊ ያለምንም ዓይነት የአካል ስሜትን አጥብቆ ያወገዘ አ

እደግ ጠንካራ አስተሳሰቤን. . . እ. . . ከዚህ በክፋ መልኩ የሴት ለሴት ግንኙነትን እንዴት እንዲቀበልልኝ ላስገድደው? የአበሻ አምላክ እርዳኝ! እራሴን እንድቆጣጠር አድርገኝ። መውጣት ከሚያስቸግረኝ ወጥመድ ውስጥ አትክተተኝ እባክህ እርዳኝ።

በዚህ መሀል ወደተበረገደው በር ያየሁት ሜሪን እንዳቀፍኩ ነበር። አፈርኩ። ሜሪን ከላዬ ላይ መንጭቄ ወረወርኳት።

ክሬስ የጥላቻ አይኗን እላዬ ላይ እንደተከለች ሜሪን ከወደቀችበት አነሳቻት። ሜሪ በብስጭት የምትሆነው ጠፋት «ዩ ቢች» /ውሻ/

«ያንቺን ያህል አይደለሁም ሁለተኛ እንዳትጠጊኝ ሰይጣን!»

«እራሰሽን ለምን ታታልያለሽ? እ! እየወደድሺው»

«ሜሪ ነገርኩሽ ቆሻሻ ነሽ በጣም!»

«ከየት ነው የመጣሽው? . . . ከጫካ ነው እንዴ? እስካሁን ይህን የማታውቂ የጫካ ሰው. . . ባሳገር!» ክሬስ በመሀል ገብታ

«ሁለተኛ ፍቅሬን እንዳትነጥቂኝ ሰማሽ?» የትዕዛዝ ነት።

ያደረ የክሬስ ጥላቻ አሁን ገና ገባኝ። እንድትጠላኝ የሜሪ አይን እኔ ላይ የማረፉ ጉዳይ ነው። ግን

ምን እያየሁ ነው? ህልም? አንድ ሴት የወንድ ጓደኛዋ ላይ ልትቀና የምትችለው ዓይነት ቅናት?! ወይ ጉድ! ይህን ሁላ አላውቅም ነበር። ይኸው ይህ ስደቴ አዲስ ክስተትን አስታወቀኝ። አለማችን ከአለማቸው የተለየ ነው። አይገጥምም።

ክሬስ ሜሪን እየሳመች አባበለቻት። በቋንቋቸው ብዙ ነገር ትላት ነበር። በመሀል እኔ እንድሰማ በእንግሊዘኛ «ምንም ቢሆን እንደኔ የሚወድሽ የሚያውቅሽ አታገኚ! ደግሞም ያገርሽ ልጅ ነች። ለቡኒ ገላዋ እንደሆነ ወደ አገራችን ስንሄድ በቦራካይ ባህር ዳርቻ ከፀሐይ ስር እተኛለሁ። የኢሊኢሊ ፀሐይ ለገላዬ አንቺ የምትወጂውን ቡኒ ከለር ይሰጠዋል እ!» ቀስ እያለች ልብሷን አወለቀች።

ሜሪ ድብርቷ ለቀቅ አድርጓት ፊቷ በፊት እንደነበረው የፈካ ሆነ። ልብስ በማውለቁ ክሬስን ረዳቻት የውስጥ ሱሪዋን በጥርሷ ጉተት እያደረገች እስክታች አወረደችላት። ሁኔታቸው አናደደኝ።

«ስሙኝ! ለምን አንዳችሁ ሌላችሁን አንተ እያላችሁ አትጠሩም። በዚህ ዘዴ እራሳችሁን በሚያሳምን መልኩ ማታለል በቻላችሁ ነበር። ክሬስ ለምን አንቺ ክሪስቶቨር ወይም ክርስቲን አትሆኚም . . . እ አንቺም ሆንሽ ስምሽ ወንድ ለመሆን አመቺ ናችሁ» አይሰሙኝም . . . የት ናቸው?! መልስ አልሰጡኝም። የገዛ አልጋዬ ላይ ዘፍ ብለው ወደቁ።

«ወይኔ! አልጋዬ ወይኔ ካልጋዬ ተነሱ ተነሱ!» የሰፈረባቸው ሰይጣን አልጋዬ ላይ እንዳይራገፍ በመፍራት ሮሁኩኝ።

በተቻለኝ አቅም ከአልጋዬ ላስነሳቸው ወደነሱ ቀረብኩ ሁሉም ነገር በግልፅ ታየኝ። የሜሪ ምላስ እኔ ላይ እንደዋለ ሁሉ አርጥበቱና ልስላሴው ተሰማኝ። ጨኸቱ ጋብ ብሎ የሚያደርጉት ነገር ከአቅሜ በላይ በሆነ መልኩ ሙሰጠኝ። አብሬአቸው አቃሰትኩ። መጨረሻ በልቤ እናገርኩሽ።

ጠዋት ሥራ ከመጀመራችን በፊት ዘወትር የቁርስ ጠረጴዛ ላይ እንገናኛለን። የጠዋት ቁርስ የተለያየ ቢሆንም እኔ የወደድኩት ግን ተቆርጦ በደረቀ ዳቦ ላይ የእንጆሪ ማርማላት በጠረጴዛ ቅቤ ተቀብቶ በመሆኑ እዚህ ቤትም ከመጣሁ ጀምሮ ቁርሴን በደስታ እመገባለሁ። ታዲያ ሁለቱ ሴቶች እንደዚያ በሆኑ በነጋታው ቁርሴን ጠላሁት። ከፊት ለፊቴ የሚያስመልስ ሰው እንዳለ ሁሉ ሜሪና ክሬስ የሚጉርሱት ጉርሻ እኔን ወደ ላይ አለኝ። በሆዴ. . .

«አሁን እንደዛ በሆነችበት አፏ እህል ትከታለች? ቱ!» አልኩ

ሜሪና ክሬስ ሊያናግሩኝ የፈለጉት ነገር እንዳለ ሁሉ «አ!» ይሉና ከአፋቸው ይመልሱታል። በእርግጥ ስለአልጋዬ መዘባረቅ በጣም ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው ባይ ነኝ። የእነርሱን መንገድ እንድይዝ የውይይት ሙከራ ከሆነ አሁን ሀሳቤን የሚሰርቅ ስሜት የለም። ትላንት የሆነው ነገር በፊቴ የሚዘገንን ጥላ ሆኖአል። ይልቁንም ወደኔው ንፁህ መንገድ ልስባቸው ሙከራ አደረግኩ።

«ሜሪ! ክሬስ! እኔ እወዳችኋለሁ። የምትሰሩት ሥራ የሰይጣን ሥራ ነው። በመፅሐፍ ቅዱስ አታምኑም? ክቻላችሁ በሁለታችሁ ያለውን ወሲባዊ ግንኙነት ተውት። ፀጣም የሚያሳፍር ነው። ካልቻላችሁ ግን ማታ ላይ እኔን አትረብሹኝ ካለሁበት ፀጥተኛ አለም አታውጡኝ። እንደናንተ መላው ጠፍቶኝ ስሜቴ በላዬ ላይ እንዲመላደቅብኝ አታድርጉኝ። እኔን ተውኝ እርሱኝ እሺ።»

ተያዩና ሳቁ። ክሬስ አፏን ከፍታ ስለሳቀች አፏ ገማኝ። የአፏን ግማት ለመሸሽ ሁሌ ፊቴን አዙሬ መናገር ነበረብኝ። አሁን ግን ነገሩ ፊት አዙሮ የሚነገር ባለመሆኑ በሚሉት ነገር ፊት ለፊት ተፋጥጬ መመለስ ስላለብኝ የክሬስን የአፍ ግማት ቻል አደረግኩት። ድንገት አሰብኩኝ። የአፏ ግማት ከሁኔታው ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን? የሜሪ አፍ ለምን አልገማም ታዲያ? ሜሪ በቅርብ የጀመረች ከሆነና እየቆየች ስትሄድ ግን መግማት ብትጀምርስ? ማን ያውቃል?!

«አይ ሚስኪኗ ስታሳዝኚ ምንም አታውቂም። መሬት ክብናት ሲሉሽ እሺ. . . ቫይረስ የበሽታ መነሻ ነው ሲሉሽ . . . እሺ መተኛት ደስ የሚለው ከወንድ ጋር ብቻ ነው ሲሉሽ . . . እሺ ሁሉን . . . እሺ» አለች ሜሪ

ትናንሽ አይኖቿን በማስረዳት አይነት ብልጥጥ አድርጋ።
ንግግር ቀጥላ

«ቫይረስ ለበሽታ መንስኤ ለመሆን ለመመራመሩ እድል ስለሌለሽ እሺ በይ። ስለሌሎች ሁኔታዎችም መቼም እመኝአቸው። ይህ ግን የግብረ ስጋ ስሜት ያለው በውስጥሽ በእጅሽ ነው። ተመራምረሽ ከእውነቱ መድረስ ትችያለሽ»

ንግግሯ ስላልጣመኝ አቋረጥኳት። ያው ዞራ ብልግና ውስጥ ዘው ነው የሜሪ ነገር። ባለጌነቷ ዛሬ አልጣመኝም። እጄን በኩራት አጣምሬ «እንዲህ እንድትሆኑ የሚያደርጋችሁ የነገሮች እውነተኛነት ለማወቅ መመራመር ፈልጋችሁ አይመስለኝም። ብዙ ነገሮች ምርምር አያስፈልጋችውም። ደግሞም የሰው ልጅ አዲስ ነገር ለመፍጠር መመራመር አለበት እንጂ ሌሎች የተመራመሩበትን እውነት ይሁን ውሸት እራሴ ተመራምሬ አውቃለሁ ማለት የለበትም። ሌሎች በበቂ ምክንያት ምርምራቸውን እስካላዩ ድረስ ማመን ግዴታ ነው። ይህ የምታደርጉት ነውር ግን ለጊዜው ምርጫ ስለሌላችሁ ስሜታችሁን ማሸነፍ ያቃታች ደካሞች ስለሆናችሁ ብቻ ነው። ወንድ የማግኘት ዕድላችሁ ሲጠብ እራሳችሁን ታታልላላችሁ። ያለ ወንድ መኖር እንደማትችሉ ማመን አትፈልጉም። ወንድ ለህይወታችን ምንም አይደለም ብላችሁ ከእውነታ ትሸሻላችሁ ግን ይኼ ተፈጥሮ መሆኑን አትዘንጉ። አገራችሁ ስትሄዱ በነፃነት ከወንድ ጋር እንደፈለጋችሁ መሆን ስትችሉ አጉል ስነ

ምግባር ውስጥ እራሳችሁን ለምን ታስቃያላችሁ። መቼም እኳላችሁ ቢደስትም ስህተት በሆነ መንገድ እንደሆነ ህሊናችሁ ያውቀዋል። ከአንቺና ከክሬስ ይልቅ ሌላ ባልና ሚስቶች የተሻለ ህይወት አላቸው። በህብረተሰቡ ውስጥ ፀጥነት ይመላለሳሉ። ልጆች ይኖራቸዋል ሀላፊነት ይኖራቸዋል። በኔ ሀሳብ የሰው ልጅ ከወሲብ ይልቅ እጅግ ብዙ የሚያስደስቱ ነገሮች አሉት። ሁሉም ነገርኮ ስሜት አይደለም። በግልፅ ንገሩኝ እስኪ ለቅፅበት ከምታልፈዋ አጭር የስሜት ጊዜ በቀር ሁለታችሁን የሚያስተሳስር ነገር አለ? ባልና ሚስቶች ግን ነገራቸው የተሳሰረ ነው። ስለዚህ እኔም ስሜቴን እንዲገዛው የምፈልገው ወንድ እንዲሆን ነው። ቤት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ። ልጆች ወልጄ ጥሩ ቤተሰብ ለመመስረት እመኛለሁ። ህይወቴ በእምነት በባህል በህብረተሰብ የታቀፈች ስትሆን ደስተኛ እሆናለሁ እናም ከእኔ ራቁ!»

ሁለቱም አጨበጨቡ። ባንድ ድምፅ

«ጥሩ ዘገባ ነው ፕሮፌሰር» ብለው ቀለዱ «ንግግራችንን አንቺን በሰማነው መልኩ ልታደምጪን ፍቃደኛ ነሽ?» አለች ሜሪ እጇን እንደድምፅ ማጉያ ግይክራፎን ጨብጣ በቀልድ መልክ ወደአፏ እያስጠጋች።

እራሴን በእሽታ ነቀነቅኩ።

ሜሪ ቀጠለች እጇን በደስታ እያወናጨፈች «ወሲብ እስከሽ ይበርድሻል? አይበርድም አይደል ይሞቃል ስለዚህ ወሲብ የስሜት መናር ነው። ሙቀት ነው ባጭሩ በንክኪ

ወይም ንክኪን በማሰብ የሚፈጠር ስሜት ነው። እነዚህ ንክኪዎች በተለያየ ቦታ የተለያየ ደረጃ አላቸው። ጭኖችሽ ሲነኩ የሚሰማሽ ሙቀት እጅሽ ጫፍ ላይ ስትነኪ ከሚኖረው መቀት እጅግ ይበልጣል። እና መቀቶች የተለያየ ቦታ የተለያየ ደረጃ ካላቸው ሴት የቱጋ ስትነካ በጣም ሞቂት ለእርካታ እንደምትጋበዝ ከወንዱ ይልት ሴት ታውቃለች። የቱጋ ስትነካ እንደሚነዝራትም ልታውቅላት የምትችለው እርሷው ሴት ናት እንጂ ወንዱ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ሴት ሌላዋን ሴት የምትነካው እራሷ እንዲነካላት የምትፈልገው ቦታ ነው። በእርግጥ ለወንዶቹ ቦታዎቹን ማሳወቅ ይቻላል። ያውቁታልም ምናልባት በተፈጥሮ ቢሆንም አነካካቸው እንደሴቷ ፍፁም አይደለም። ታዲያ የወንድ አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው። ከሴት ጋር ከወንድ የበለጠ እርካታ ማግኘት እየተቻለ ደግሞ ወንድ ብዙ ጊዜ በራሱ ስሜት ስለሚገዛ እራሱን ብቻ ሊያዳምጥ ይችላል። ሴት ግን እንዳንቺው ሴት ነች። ስሜታችሁ አነካችሁ ይመሳሰላል። የሚያስጮህሽ ቦታ ያስጮሀታል። በቀላሉ በስሜት ትግባባላችሁ አንድ ስለሆናችሁ።

ክሬስ ተቀብላ

«ተያት ይህ ምን ይጠቅማል ያገሯ ባህል ተብትቦአታል»

ሜሪ የክሬስን ንግግር ከምንም ሳትቆጥር ትላንት ባየችኝ አስተያየት እያየችኝ

«ለምን ማታ አትሞክሪም የወንድ ይበልጣል ወይስ የሴት . . . ሞክሪ ከዛ እነሜሪ እውነታቸውን ነው ወይም ውሸታቸውን ነው ትያለሽ ሞክሪ»

«እ!» አልኩና እራሴን ወደ ጠረጴዛው ደፋሁ። ክሬስ በጥርጣሬ አየችኝና

«ለመሆኑ ከወንድ ጋር ተኝተሽ ታውቂለሽ?»

«ኧረ! አላገባሁም!» መልሴ እንባቸው እስኪፈስ አሳቃቸው።

ክሬስ ደግሞ «ማለቴ ከወንድ ጋር ወሲብ ፈፅመሽ ታውቂያለሽ ወ . . . ይ?» አለች።

በማስረዳት መልኩ ድምፄን ዝቅ አድርጌ «አይ! እኔ ልጃገረድ ነኝ።»

ሁለቱም ከፊት ለፊታቸው ያለ የወረቀት መንዲል ስበው አፋቸውን እያበሱ ተነሱና

«ታዲያ ከመጣሽ ጀምሮ ለምን ታለፊናለሽ? መጀመሪያ ብትነግሪን እኮ የመጀመሪያውን ደረጃ አልፈሽ ከሁለተኛው እንድትገቢ አንተተጉትሽም ነበር!» በፌዝ እያዩኝ ጥለውኝ ተቃቅፈው ከኩሽና ወጡ።

ክሬስ መለስ ብላ

«ታዲያ የወንድ ወሲብን ካየሽ በኋላ የሴቱን እንድናሳይሽ ቀጠሮ መያዙን አትርሺ! የጫካ ሰው!» ብላኝ ወጣች። ክሬስ ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ ጥላቻዋን ቆጠብ

እድርጋ ሰሞኑን ቀረበችኝ። ሜሪም ከበፊቱ ባነሰ ሁኔታ ብዙም ሳትወደኝ እንደሁኔታው ሀይ ትለኛለች እኔም በአዕምሮዬ አዋራሁሽ። ማለቴ «በአቅሌ»

ምዕራፍ አምስት

መጀመሪያ ስገባ ከዋናው በር ግራና ቀኝ የቆሙ ባለስድስት እጆች አስፈሪ ሰው መሳይ ፍጡሮች በጠቆረ ድንጋይ ተቀርፀው ወደ መቃብር ስፍራ እንኳን ደህና መጡ ይግቡ የሚሉ ይመስል ስድስቱን እጆቻቸውን በየአቅጣጫው ቀስረው ያስበረግጋሉ።

ፀጥ አረጭ ጨለም ያለው ቤት ውስጥ ገብቼ ቆሜ ላለሁ ድምፅዋ ከአካሷ የበረታ ለውነቷ ከድምፅዋ እጅግ ድክምክም ያለች ሴት መብራት አብርታ ያለምንም ፈገግታ ለደቂቃዎች አስተዋለችኝ . . . ከላይ እስከታች። ለእርሷ ምን እንደገረማት ባላውቅም እኔ ግን እንደዚህ የድምፅና የአካል ልዩነት አይቼ ስለማላውቅ ይኸው ጉዳይ አስደመመኝ።

«ምን ሂና /በዚህ በኩል/» የሚል ትዕዛዝ ሰጥታኝ ረጅሙን ኮሪደር ተከተልኳት።

ሥራውን ያገኘችልኝ ሴት ባሏ ስለሴትየዋ የነገራትን ሁኔታ አስቀድማ ብትነግረኝም የሴትየዋ አስፈሪነትን በተረት ላይ ከሚነገሩት አስማተኛ ሴቶች በላይ ሆኖ አገኘሁት። ቤቱም እንደመቃብር የከበደ ቀፋፊ ስሜትን የሚፈጥር ነበር።

አድርጋ ሰሞኑን ቀረበችኝ። ሜሪም ከበፊቱ ባነሰ ሁኔታ ብዙም ሳትወደኝ እንደሁኔታው ሀይ ትለኛለች እኔም በአዕምሮዬ አዋራሁሽ። ማለቴ «በአቅሌ»

ምዕራፍ አምስት

መጀመሪያ ስገባ ከዋናው በር ግራና ቀኝ የቆሙ ባለስድስት እጆች አስፈሪ ሰው መሳይ ፍጡሮች በጠቆረ ድንጋይ ተቀርፀው ወደ መቃብር ስፍራ እንኳን ደህና መጡ ይግቡ የሚሉ ይመስል ስድስቱን እጆቻቸውን በየአቅጣጫው ቀስረው ያስበረግጋሉ።

ፀጥ እረጭ ጨለም ያለው ቤት ውስጥ ገብቼ ቆሜ ላለሁ ድምፅዋ ከአካሏ የበረታ ሰውነቷ ከድምፅዋ እጅግ ድክምክም ያለች ሴት መብራት አብርታ ያለምንም ፈገግታ ለደቂቃዎች አስተዋለችኝ . . . ከላይ እስከታች። ለእርሷ ምን እንደገረማት ባላውቅም እኔ ግን እንደዚህ የድምፅና የአካል ልዩነት አይቼ ስለማላውቅ ይኸው ጉዳይ አስደመመኝ።

«ምን ሂና /በዚህ በኩል/» የሚል ትዕዛዝ ሰጥታኝ ረጅሙን ኮሪደር ተከተልኳት።

ሥራውን ያገኘችልኝ ሴት ባሏ ስለሴትየዋ የነገራትን ሁኔታ አስቀድማ ብትነግረኝም የሴትየዋ አስፈሪነትን በተረት ላይ ከሚነገሩት አስማተኛ ሴቶች በላይ ሆኖ አገኘሁት። ቤቱም እንደመቃብር የከበደ ቀፋፊ ስሜትን የሚፈጥር ነበር።

እቤቷ የደረስኩት ገና በቀኑ ቢሆንም የሠራተኛ ክፍል እንደደረሰችኝ ሌሎች እንደሚያደርጉት ስለሥራዬ ሁኔታ ምንም ሳታብራራ «ነቢ /ተኚ/» ብላኝ ሄደች። እኔ አረብኛ አልገባኝም ወይስ ይህች ሴት ልታስተኛኝ ነው የቀጠረችኝ?! እኔ እንጃ።

ፀጥ ባለው ቤት የነገሰው የብዙ ሰዓቶች ድምፅ ቲክ ታክ እያለ ሙሉ አዕምሮን ሰብስቦ የመግዛት ኃይል አለው። ይህ ድምፅ ሙሉ ሀሳቤን እየወሰደ ከዚህ በፊት በማላውቀው አይነት ምስጥ እንድል አድርጉኝ በፍራቻ ስለዘፈቀኝ ድምፁን ጠላሁት። በድምፁ ልክም ድው ድው የሚለው የልቤ ምት ድምፁን ጨምሮ በፍራቻ አሰቃየኝ። በር ላይ ካየኋቸው የሀውልት እጆች ተንጋግተው መጥተው እንቅ የሚያደርጉኝ እየመሰለኝ በሩ ላይ አፍጥጬ እንዴት ልከላከላቸው እንደምችል አውጠነጥን ጀመር። ተረጋጋሁና . . . ቢመጡ እሰብራቸዋለሁ። ሽክላ ቢበዛ ደግሞ ለስላሳ ድንጋዮች ናቸው። ምን ነካኝ . . ምን ነካኝ። ፈራሁ።

በሚቀጥለው ሌሊት እመቤቴ በዚያ ጠንካራ ወንዳማ ድምፅዋ ስለሥራ ሁኔታ አስረዳችኝ።

«የምንተኛው ቀን ነው። የምንነሳው ደግሞ ሌሊት ነው ገባሽ? ያ ማለት የሥራ ሰዓትሽ ሌሊት ነው። ቀን ምንም ከሽታ መስማት አልፈልግም።»

«የመጀመሪያ ሥራሽ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሀውልቶች ባጠቃላይ ማፅዳት ነው። አንድ ሀውልት ላይ

ብናኝ አቧራ ማየት አልፈልግም። ለመሬቱ ለዕቃዎቹ ለወንበሩ ለመስታወቱ ለመስኩቱ ለወጥ ቤቱ ለባኛው ፅዳት ግድ የለኝም። ደስ ሲልሽ አፅጂአቸው ደስ ካላለሽ «ፊ ሲቲን ዳህያ» /ጀሀነብ/ ግድ የለኝም። ሀውልቶቹ ግን በህይወቴ አስፈላጊ ነገሮች ስለሆኑ ተጠንቀቂላቸው። ለእነሱ ብዬ የገዛሁት ሻንጉ አለ ካፀዳሻቸው በኋላ የራሳቸውን ክሬም ትቀቢአቸዋለሽ።

በማግሥቱ ጠየቀችኝ «ሀውልቶቹን አፀዳሽ?» ሀውልት ሀውልት እያለች የምትደጋግመውን ቃል ጋብ ብታደርግና በምትኩ ለቅርፆቹ ትክክለኛ ስማቸውን ሰጥታ ቅርፃ ቅርፆቹን ብትል እኔም ስለሞት ማሰቤን ላቆምና ፍራቻዬም እንዲያበቃ በማሰብ ላርማት

«ቅርፃ ቅርፆቹንም ቤቱንም በደንብ አፅድቼአለሁ እመቤቴ!» ከወገቤ ሰበር አልኩ።

አስበረገገችኝ ድምፅዋን አስጨሀ «ሀውልቶቼን ቅርፃቅርፅ ብለሽ እንድትጠሪያቸው አልፈቅድልሽም። ስማቸው ሀውልት ነው ገባሽ ሀ-ው-ል-ት!»

እራሴን በእሽታ ነቀነቅኩ።

ሁሌ ማታ ማታ አንድ ሰዓት ላይ ሽርጥ ያሸረጡ የሆቴል ሰዎች መጥተው ላንድ ትንሽ ድግስ የሚበቃ ጣፋጭ ምግቦችን ትተው ይሄዳሉ። ሲንጋጋ ሲል እንደገና መጥተው ያልታጠቡ እቃዎችን ሰብስበው ይመለሳሉ።

በሳምንት አንዴ የላውንደሪ ቤት ሰዎች መጥተው የቆሸሸውን የቤቱን ልብስ ሰብስበው አጥበው ተኩሰው ይመለሳሉ::

እንዲህ አይነት ቤት አጋጥሞኝ አያውቅም:: ሴትዮዋ በጣም ሀብታም ሆና ግን ድህ ለመሆን እየጣረች ያለች ትመስላለች:: የምግቦቹ የሆቴሉ ወጪ ቀላል አይመስለኝም:: ለምን እንደሌሎቹ የወጥ ቤት ሠራተኛ ቀጥራ እቤቷ የጣፈጠ ምግብ በቀላል አስቤዛ የማድረግ ሀሳብ እንደሌላት አላውቅም:: ገንዘቧን ለማውጣት መንገድ የምትፈልግ ዓይነት ናት::

እርሷ እንዳለችው ሀውልት የማፅዳት ሥራዬን በሚገባ አከናውናለሁ:: ሀውልቶቹ ከሥራቸው የወከሉት ሬሳ ባይኖርም በየቦታው በሰው ቁመት ልክ ተገትረዋል:: ምናልባት በሀውልቶቹ ብዛት ያህል በየቦታው ተሰቅለው የሚታዩት የቀን መቁጠሪያዎች ቤቱን የተለየ አድርገውታል:: ምን ዓይነት ቤት ነው:: ሰዓት . . . ቁጥር . . . ቀን . . . ቁጥር ሀውልት ሰዓት የቀን መቁጠሪያ . . . ማለት የፈለጉት ሞትን ይሆን? ሞት . . . እኔንጃ ብቻ ስነቃም ስተኛ የሰዓቶቹ የቀን መቁጠሪያዎቹ . . . የሀውልቱ . . . በብዛት መገኘት ሞትን በጥሞና እንዳስብ አድርጉኛል::

በዚህ ቤት ትልቅ ሚስጥር እንዳለ ስለገመትኩ ብቻ ፍራቻዬን ዋጥ አድርጌ ሥራዬን ለመቀጠል ባስብም ስለሞት ማሰቤን ማቆም ያለመቻሌ እንዳያላብደኝ ፈራሁ::

ከሀብረተሰቡ ተገልሎ ብቻውን የቆመው ይህ ቤት ስልክ የለውም . . . ቴሌቪዥን የለውም . . . ሙዚቃ የለም . . . ጋዜጣ የለም . . . የሚመጣ የለም:: ሀውልት ብቻ . . .

የሴትዮዋ ሁኔታ . . . ልብሷን አዙሮ መልበስ . . . ጫማ አጣምሮ መልበስ . . . አብድ ናት? እኔንጃ:: ንግግሯ ውስን ነው ስለጤንነቱ ጠይቃኝ አታውቅም:: ሰላምታ የለም::

«ሀውልቶቹን አፀዳሽ?»

«የትኛውን ሀውልት ትወጃለሽ?»

«መሞት ወደድሽ ዛሬ? ስትወድጂ ሀውልት እንድቀርፅልሽ ንገሪኝ እ! ዘር ማንዘሮችሽ ሊረሱት የማይችሉት አይነት ሀውልት ልቀርፅልሽ ቃል እገባልሻለሁ»

«በስመአብ ምን ገፊዋ ናት» አልኩኝ በሆዴ:: እኔ ገና ሀያዎቹን ዓመታቴን በደንብ ሳላጣጥም ለወደፊቴ በማሰብ ደፋ ቀና ስል ባጭር ልትቀጪኝ ሀውልት ልቅረፅልሽ የሚለው ጥያቄዋ ያስገርመኛል::

የተለያየ ቤት የተለያየ የሕይወት ልምድ አለው:: እኔም ለሥራ የምቀያይራቸው ቤቶች በገንዘብ ብቻ ሳይሆን የህይወትን ድሎትን ሀዘንን ችግርን ተስፋን በመጠኑም በሌሎች እያየሁ ብቻ ለራሴ ኖራዋለሁ:: ለምን እንደሆነ እኔንጃ ይህ የቤት ሠራተኝነት ሥራዬ ወደፊት ለሚኖረኝ ህይወቴ የማይበገር ጥንካሬን የካበልኝ

ይመስለኛል። የብዙ ህይወቶች ቅንብርም ጥሩ ትምህርት ሰጥቶኛል። ልጅ ሳልወልድ የሕፃን አያያዝን የምታውቅ እናት ሚስት ሳልሆን የባል አያያዝን አውቂአለሁ። ለሴት ትልቁ ልምዷን ማለት ነው።

የሰው ሚስጥር የማወቅ ጉብዝናዬን ተጠቅሜ ከዚህ ድብርታም ቤት ለመውጣት ብጥርም ማወቅ አልቻልኩም። ብቻ ብዙ ሚስጥሮች እንዳሉ ይሰሙኛል።

አንደኛ የባልና ሚስቶቹ የእድሜ መራራቅ ሁለተኛ የህውልቶቹ ሦስተኛ የእመቤቴን የመኝታ ክፍል እንዳይም ሆነ እንዳፀዳ ያለመፈቀዱ ሁኔታ አራተኛ የእመቤቴ ፀባይ እንዲህ እንዲሆን ያደርገውና የገፋፋው ምክንያት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ጓደኞቼ እነ ቅድስት የሰው ሚስጥር ላይ የማድፈጤን ጉዳይ ከአወራሬ ስለሚያውቁ አጉል ፀባይሽን ትተሽ የራስሽ ህይወት ላይ ብታደፍጪ ይሻልሻል ብለው ይገስፁኛል። እግዜር ለዚህ ግርድና ባይዳርግሽ ኖሮ ጥሩ የወንጀል መርማሪ ወይ ሚስጥር ፈልፋይ ሰላይ ይወጣሻል።« አዕምሮሽ ነገር ለመገጣጠም እግሮችሽም ኩቴ የማያሰሙ ጆሮዎችሽም ሳተላይቶች ናቸው» ብለው ይተርቡኛል። እኔም የሚያስደስተኝ ልማድ ስለሆነ ሳላፍር በተለያየ መልኩ ልጠቀምበት ወደኋላ አልልም።

የሥራዬ መጨረሻ አመድ አመድ ቀለም ቀለም ብረት ብረት ወደሚሸተው ቀፋፊ ክፍል ገብቶ ጅምር ህውልቶችን ማለቅ አለማለቃቸውን ማየት ነበር። ካለቁ

የሚሰጣቸውን ቦታ እመቤቴን ጠይቆ እንደሌሎቹ ህውልቶች የፅዳት አገልግሎት እንዲሰጣቸው የማድረጉ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል። ግራ የሚያጋባው ነገር የህውልቶቹን ማለቅ አለማለቅ እራሴው አውቄ ሥራ መጀመሩ ነው። ሴትየዋ በዚህ ጉዳይ ገና ስገባ አስጠንቅቃኝ እኔም ተስማምቼአለሁ። ይህን ካላደረግሁ ግን በደሞዝ እንደምትቀጣኝ ተነግሮኛል።

እራሷን የምትመስል ሴት ምስል እየሰራች ባለችበት ሰሞን ከመቅረጪያ ክፍሏ ስትወጣ እንባዋን ስትጠርግ አንድ ሦስቴ አጋጥማኛለች። ሰው ለራሱ ህውልት ማዘን ቢችል በርግጥ ከእርሷ የበለጠ ለማዘኑ ጥርጥር የለውም። ደግነቱ ሰው ለራሱ ህውልት እንዲያዝን ዕድል አልተሰጠውም። እና ለምን ይህች ሴት እድሉን ያገኘች ይመስል ስለራሷ ምስል ህውልት ቀርፃ ታነባለች? የዕንባዋ ምክንያት ባይገባኝም ከፍቷት ሳይ ሆዴ ይንጫበጫል።

ጨረስኩት ብላ የደመደመችው ህውልት ያላለቀ መስሎኝ እስኪያልቅ ስጠብቅ ጉድ ሰራኝ። ይኸው የራሷን መልክ የያዘው ህውልት አንድ ጡት ብቻ አለው። እኔ ሁለተኛውን ጡት እንዲሠራለት ስጠብቅ ባንድ ጡት ብቻ ፀናና ደሞዜን አስቆረጠብኝ። መቼም ስምምነት ነውና አልተቃወምኩም። ግን ለመጀመሪያ ጊዜ እመቤቴ ፊት ቆሜ ባለአንድ ጡት ሴት ተፈጥራ እንደማታውቅ ተክራከርኩ። ለነገሩ እዚህ ቤት ገና ስገባ ያፈጠጡብኝ እነዚያ ባለስድስት እጆች ጥቋቁር ህውልቶችን የመሰለ

ፍጡር የለም። ብቻ በዚህ አንድ ጡት ጥያቄ መረታት የለብኝም።

በቀስታ እንድቀርባት ጠየቀችኝ። ቀረብኳት። በእጇ ሁለት ሶስቴ ጉንጩን እንደሚስም ሰው አመቻችታ ባለ በሌለ ሀይሏ በጥፊ አጮለችኝ። ጆሮዬ ጭውውው ሲል ተሰማኝ። ግን ጥፊው ሰርዓው ዞሮ ያሳመማት ይመስል ከኔ ቀድሞ የሷ ፊት ቲማቲም መሰለ። ይህ ጥያቄ ከኔ ጥፊ ይልቅ ሳያማት የቀረ አይመስለኝም።

«ይህን አምስት ሰዓት ተደብቂ አለበለዚያ ከዚያ በፊት ካየሁሽ የማደርግሽን እኔ አራሴ አላውቅም።» አለችኝና እራሷ ከራሷ የፈራችልኝ ሁለት ሰው መሰለች።

ያለችኝን አምስት ሰዓት ከፍሌ ተደብቄ ስወጣ ፊቷ ላይ ምንም እንዳልተፈጠረ ሆኖ እርጋታን አነበብኩ። ከአናደዳት የአንድ ጡት ነገር በፊት የነበራት ፊት ተመልሶ ቀዝቃዛ አስተያየቷን አስፍናለች። ይህች ሴት ካየኋቸው ሴቶች ሁላ ደስ የሚል ፀባይ አላት። ቅድም ተጣላን አሁን ሰላም ነን። ጥላችን ቂም ሳያስይዛት እንድትረሳው አምስት ሰዓታት ብቻ የሚፈጅባት ከሆነ ባሏና ዘመድ ጓደኞቿ በዚህ ፀባይዋ እድለኞች ናቸው ማለት ነው። ግን ዘመዶች ጓደኞች እናት አባት ቢኖራት ነበራ!! ስራዬን ወደድኩት!!

እንደበፊቱ ሳይሆን የዚህ ቤት ጥበብ እየታየኝ መጥቷል። የእመቤቴ ችሎታ እጅግ የሚደነቅ መሆኑን አመንኩ። ያስፈራሩኝ ቅርፃቅርፆች ለኤግዚቢት ከሚቀርቡ ጥበቦች አይተናነሱም። ቅርፃ ቅርፆቹ ውስጣቸው ያፈኑትን ሀዘን ቀስ በቀስ በውበታቸው ያነቡታል . . . ደጋግመው ሲታዩ።

እራሷን ጥበብ ውስጥ የደበቀች ሚስኪኗ ሴትም በደንብ ስትታይ ከላይ የሸፈናትን የቁጡነት መንፈስ ተገርስሶ በምትኩ ደግነትን ከልክ በላይ የተጉዳ ስብር ልቧን ሀዘኗን ቀስ እያለ እንደ ቅርፃቅርፆቿ ይገለጣል።

ቆይቶ የገባኝን የቅርፃቅርፅ ውበት ለማድነቅ ማንም ሳያየኝ አዳዲሶች ገና ያላለቁ ቅርፃቅርፆች ወደሚገኙበት ክፍል ከመግባቴ በፊት ሰዎቹ ፎቅ እንዳሉ በትክክል አረጋገጥኩ። መብራት አበራሁና ማየት ስጀምር ኮቴ ሰማሁ። ያለሥራ ሰዓቴ ስለሆነ ለመግባቴ ምክንያት ማቅረብ የምችል ስላልመሰለኝ ገብተው እስኪወጡ ቁምሳጥን ስር ገባሁ።

እመቤቴ ከተደበቅሁበት ፊት ለፊት ተሰቅሎ ያለ ስዕል አወረደችና ግድግዳው ላይ ያለ ማብሪያና ማጥፊያ በጣቷ ተጫነች ከጉን ያለ ግድግዳ ብርግድ ብሎ የተከፈተ መሰለኝ። ደነገጥኩ።ግድግዳ መሳዩ ገፅታ የሚከፈት የሚዘጋ ሚጥራዊ መደርደሪያ ሆነ። ቀጠለችና በመስታወትማ ፕላስቲክ የተቀመጠ ዱቄት አወጣች። ከዱቄቱ በትንሽ ወረቀት ቆንጥራ ጠቀለለችና በጥንቃቄ መልሳ እንደገና ያን ማብሪያ ማጥፊያውን ተጭና ግድግዳውን እንደነበረ መለሰችው። ስዕሉን ሰቅላ ሁሉም

ነገር እንደበፊቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ገልመጥ ብላ ዘግታ ወጣች።

በሚቀጥለው ቀን ምሽቱን የሚያሳልፉበትን ሳሎን ሳፀዳ ጠረጴዛ ላይ ያን ዱቄት ስትቆነጥር ያየሁበትን ትንሹን የወረቀት ኪስ አገኘሁ። ውስጡም የቀረ ዱቄት አለ። እጄ ላይ በትንሽ ፈሰስ አድርጌ በጣቶቼ ነካሁትና እየፈራሁ ምላሴ ላይ አደረግኩ . . . ስኳር ስኳር ይላል። መርዝ እንዳይሆን ስለፈራሁ የነበረበት ትቼው ሥራዬን ቀጠልኩ።

የመደርደሪያው ነገር እንቅልፍ ነሳኝ። ለምቾ ሲገኙ በእርጋታ ሚስጥረኛውን ግድግዳ ጠቅ ጠቅ አድርጌ መደርደሪያ እከፍትና በውስጡ ያገኘሁትን የፎቶ አልበም ክፍሌ ቁጭ ብዬ አገላብጣለሁ። ያን ዱቄት የያዘው ይህ መደርደሪያ የቀን መቁጠሪያዎች ደብተሮችና የፎቶ አልበሞች ብቻ ሲኖሩበት ገንዘብና ጌጥ መሳይ የካዝና ንብረቶች የሉበትም።

በዕድሜ በጣም የሚያንሳት ወጣቱ ባሏ አልበሞቹ ውስጥ አንድ ቦታ እንኳን የለበትም። በምትኩ በልጅነቷ ባል ክንድ ውስጥ እንዳለች በቪሉ ደምቃ ትታያለች። አፍንጫዋ ስር ያለው የተፈጥሮ ምልክትን እዚህ ፎቶ ላይ ባላየው ያሁኗ ሴት ናት ለማለት ያስቸግረኝ ነበር። በጣም ቆንጆ ነበረች። አልበሟ ላይ ያለ ፈገግታዋንም ከገባሁ ጀምሮ አይቼም አላውቅም። የልጅነት ባሏ ይፍታት

ይሙት እርግጠኛ ባልሆንም የሀውልቶቹ እና የሀዘኗ መንስኤ የባሏ ሞት ይሆናል ብዬ ገመትኩ።

ደብተሮቹ ሁሉ የተፃፉት በአረብኛ ነው። ድንገት ከስር ውትፍ ያለች ጉስቁላ ቀይ ደብተር ብጤ ላይ አይኔ አረፈ። አንስቼ ሳገላብጣት በተለያየ ዓይነት ብዕር የተሞነጫጨረ ፅሁፍ አለው። የብዕሩ መለያየት በተለያየ ቀናት መፃፉን ያመለክታል። ይህ ደብተር ስለሴትዮዋ ብዙ ወሬ ስለሴትዮዋ ያወራልኛል ብዬ ያለምንም ፍራቻ ደብተሯን ለቀም ሳደርግ ያችን ግብፃዊት አረብኛ ቃላቶቹን እንደምትተረጉምልኝ በማመን ነበር።

በዕረፍት ቀኔ ደብተሯን ይዤ ግብፅዋ ሴት ቤት ስሄድ በፍላጐት የበራ ፊቴን አይታ «ዋህሽቱኪ» /ናፍቀሽኝ ነው?/ ብላ ቀለደች።

«ነአም» /አዎን/ አልኳትና ቀድታ ያመጣችልኝን ከባድ የቱርክ ቡና እንቢ አልኳት።

«የቱርክ ቡና የምትወጂ መስሎኝ ነበር።»

«ወድጀው አላውቅም። አገራችን የቡና እናት መሆኗን ታውቂያለሽ! እንዴት ታዲያ የሌሎች ቡና ይጥመኛል?!»

«እ! ለሱ ነዋ! እሺ ቁምነገር ለምን መጣሽ? ከሥራ አባረሩሽ?»

«አይ! አንድ የማስተዋሻ ደብተር አገኘሁ የተፃፈበትን ነገር ለማወቅ ጓጓሁ። ደብተሩን ያገኘሁት

በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ስለሆነ ይህን ያህል አስፈላጊ ነገር ያለው አይመስለኝም። ሞኝ ሀሳብ ስላለኝ ነው። ትርጉሙን በእንግሊዘኛ ቃል በቃል እንድትተረጉሚልኝ ነው ያመጣሁት። ለዛ ዋጋ በልብስ አጠባ እስማማለሁ። በሚቀጥለው ዕረፍቴ ማስታወሻው ያለውን ፅሁፍ ለማወቅ በመቋመጥ በርሬ ስለምመጣ አደራሽን! እ!»

ሳምንቱን ባገኘሁት አጋጣሚ እዛ መቅረጪያ ክፍል እየገባሁ መደርደሪያው መከፈት አለመከፈቱን እንዲያስታውቀኝ ማብሪያ ማጥፊያውን የሸፈነው ስዕል ላይ ሳያስታውቅ ለምልክት ያስቀመጥኩትን የወረቀት ቁራጭ እያየሁ የማስታሻዋን መሰረቅ እንዳታውቅብኝ ተሳቀቅኩ። የዕረፍቴ ሰዓት ደረሰ። ወደ ግብፅዋ ቤት ከነፍኩ።

«ውሽታም ነሽ» አለችኝ ገና ስገባ «ይህን የመሰለ ጽሁፍ ያቀፈ የግል ማስታወሻ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ወይ ሳይቀደድ ወይ ሳይቃጠል አይጣልም። ከየት አመጣሽው? እመቤትሽ ታሪኳን የሚተርከውን ማስታወሻዋን አንቺ እንድታነቢው አስተካክላ በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ከመጣል ይልቅ ጋዜጦች ታሪኳን በመጀመሪያ ገፆቻቸው እንዲያትሙት መላክ ይቀላት ነበር።»

ሚስጥሩን ለማወቅ አይኔን በልጥጬ ያመጣሁበትን መንገድ ባጭሩ አስረዳኋት «በእውነቱ ቃል በቃል ተርጉሜልሻለሁ። ማንበብ ስጀምር በፊልም

የሚከሰት ታሪክ እንጂ እውነተኛ አልመሰል ብሎ ስለኛል» ብላ አጋነነችልኝ።

«በተጨማሪም የዚችን ሴት የተለየ ስለመሆን ባሌ ሁሌ ተገርሞ ሲያወራልኝ ሳላውቀው በደንብ ሳውቃት በውስጤ ሳልጓጓ አልቀረሁም። ከዚህ የሚቀጥል ሌላ ደብተር አለ ፈልገሽ አምጪና እናንብበው። ሰው የራሱን ህይወት በየጊዜው አጋጣሚውን ደስታውን ፍቅሩን ስሜቱን ሀዘኑን ቢፅፍ ሁሉም ሰው በራሱ ታሪክ ጀግና ደራሲ ይሆን ነበር። ታውቂያለሽ! የዚች ሴት ታሪክ ያሳዝናል። እኔም በየቀኑ የሆንኩትን ብፅፍ የህይወቴን ልዩነት ለማወቅ ይረዳኛል። ግን የኔ ህይወት በጣም ቀላል ናት» አዘን አለች። ገረመችኝ። ነገረ ሥራዋ ያሳዝናል ባለችው የእመቤቴ ታሪክ ቀንቼአለሁ የሚል አይነት ሆነብኝ።

«የእኔ ህይወት አሰልቺና ተደጋጋሚ ነው። አዲስ ነገር ተፈጥሮብኝ ወይም እራሴው ልፈጥር ሞክሬ አላውቅም። ጠዋት እነሳለሁ ልጄን አጥባለሁ አበላለሁ ለባሌ ምሳ እሠራለሁ። ከምሳ በኋላ ልጄን አስተኛለሁ። ለባሌ ቡና አፈላለሁ። ማታ ባሌ ከመምጣቱ በፊት ልጄ ያተራመሰውን ቤት በትክክል አስተካክላለሁ። ባሌ ደክሞት ይመጣል። ትንሽ ቁጭ ብሎን ቴሌቪዥን እናያለን። አንዳንዴ እንደባልና ሚስት አንዳንዴ እንደ እህትና ወንድም እንተኛለን። በጣም አንጣላም በጣም አንፋቀርም። አንዳንዴ ልጃችንን ልናጫውት የመጫወቻ ስፍራ አንዳንዴ ሱቅ እንሄዳለን። ታዲያ እኔ እንደዚህች ሴት ስለህይወቱ

መግፍ ቢኖርብኝ በየወሩ መጀመሪያ ላይ የአንድ አንቀፅ ውሎዬን እፅፍና ከዛ በየቀኑ እንደትናንትና! እንደትናንትና! እንደትናንትና! እያልኩ የተቀሩትን ሀያ ዘጠኝ ቀናት እንደትናትና ብዬ ልደመድም ነው ማለት ነው። ታዲያ ይህን ህይወት ትይዋለሽ?! ውስጤ ሁሌ የሚያልመው ነገር ክንፍ ላውጣና ልብረር ይለኛል። ይህ ጉዳይ ደስተኛ አያደርገኝም።»

«ኡም ሰዒድ /የሰኢድ እናት/» እንደኔ ናት ማለት ነው። እኔም መግለፅ አልቻልኩበትም እንጂ የተመሳሰለ ህይወት ይሰለቸኛል እንዳለችው ብበር ደስ ይለኛል።

ያለችው አኗኗሯን በጥቂቱ አይቼው ነበር። ይህን ሥራ ከመጀመሬ በፊት እዚህች ግብፅ ቤት ለአስራ አምስት ቀናት ሰርቼ ነበር። እዚህ አገር ከገባሁ በልጇ ስም እንድጠራት እመቤቴ ሳልላት የሰዒድ እናት ብዬ እንዳቀርባት የፈቀደችልኝ ብቸኛዋ አረብ ሴት ነች። ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ ግን የወር ደሞዝ መክፈል እንደሚከብዳት ነግራኝ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ለተወሰኑ ሰዓታት ብቅ እያልኩ ልብስ አጥቤ እንድተኩስላት ብቻ በርካሽ ዋጋ ቀጠረችኝ። የሆቴል ሰራተኛው ባሏ ሥራው ከብዙ ሰዎች ጋር ስለሚያገናኘው ሥራ በቀላሉ እንደሚያገኝልኝ በማመን በርካሽ እርሷ ጋር መሥራቱን ተቀበልኩ።

እንዳሰብኩት ሥራ አግኝቶልኝ ሀውልቶቹ ቤት አስቀጠረኝ። ከዛ በኋላ ግን ባሏ ሥራ ስላስቀጠረኝ ውለታዋን እንድከፍል በነፃ እየሄድኩ እረዳታለሁ።

«እሀና አፍሪቃ አኽዋት /እኛ አፍሪካዎች ወንድማማች ነን/» እያለች ወደ ስጋዋ አቅርባ ከገንዘቧ አራቀችኝ። አዲሱ ሥራዬ ላይ ለመስከኔ እርግጠኛ እስክሆን ኡም ሰኢድ ጋር በየሳምንቱ መጨረሻ እየሄድኩ ከባዱን የቱርክ ቡናና አጠባ ሳልወድ ተጋትሬ ወደ ቤቴ እመለስ ነበር።

«እንዴ! ያች ትንሽ ማስታዋሻ ይህ ሁላ ሉክ ወጣት?»

«በቋንቋው የተነሳ ነዋ። አረብኛ ለእያንዳንዱ ድርጊት የራሱ የሆነ አጭር ቃል አለው። ታዲያ ወደ እንግሊዘኛው ልተርጉመው ስትይ በአረብኛ የፃፍሽትን አንድ ቃል ለመተርጉም ሦስት አራት ቃላት ተጋግዘው ያችን አንድ ቃል መተካት አለባቸው። አረብኛ ሰፊ ነው። ለዚህ ነው በእንግሊዘኛ ሲጻፍ የበዛብሽ። አንቺ ደግሞ በቋንቋሽ ልፃፍ ብትይ ቋንቋሽ ከእንግሊዘኛው ስለሚያንስ፤ በቃላት ብዛት ማለቴ ነው፤ ተመጣጣኝ ትርጉም ለማግኘት ቃላት ማጋጨት ስለሚኖርብሽ ይበልጥ ይበዛል።»

«በጣም አመሰግንሻለሁ።»

ከመውጣውቴ በፊት «ዛሬ አጠባ የለኝም የሚቀጥለው ሳምንት መጥተሽ ማጠብ አለብሽ። ቃልሽን ጠብቂ!»

የምኖርበት ቤት ከግብያቹ ቤት በጣም ቅርብ ስለሆነ ራመድ ራመድ አልኩ ቸኩዬ ለማንበብ። እቤት ስገባ እነቅድስት የሉም። ተመስገን ንባቡን አያቋርጡኝም። ወረቀቱን ገልጬ ለማንበቡ ተደላደልኩ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

«ምነው በጣም የደከመሽ ትመስያለሽ? የስፖርት ቤቱ የገጠመውን አዲሱን የስፖርት መሣሪያ ሰውነትሽ አልወደደው ይሆናል ለስ ያለ ውሀ የገላ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ሙይና አብረን እንነከር ቀለል ይልሻል» አለኝ ሰሚር ገና ከሥራ ሲገባ የዛን እለት።

ክንዴን ሊነካኝ ክንዴ ውስጡ በጣም የመለብለብ ህመም ተሰማኝ። «ውይ ክንዴ ለበለበኝ» አልኩ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተለይ የግራ ክንዴን የመለብለቡ ህመም የዘወትር ስቃዬ እየሆነ መጣ። ይህም ሕመም እያለኝ ሆስፒታል አልሄድኩም። ባሌንም ስለህመሜ ነግሬ ላስጨንቀው አልፈለግኩም። እናቴን የገደላትን የጡት ነቀርሳ አስቤውም አላውቅ። በህይወቴ

ለደቂቃ እንኳን ቢሆን የዚህ በሽታ ባለቤት እሆናለሁ የሚል ፍራቻ አልነበረኝም።

ለዕረፍት ከባሌ ጋር ውጭ አገር ለሽርሽር ሄደን በነበርንበት ጊዜ ከባህር ዳርቻ ጉዞ በኋላ ባለንበት ሆቴል በባኛ ቤት መስታወት ሁለቱን ጡቶቼን ሳይ ከቆየሁ በኋላ ባሌን ጠራሁና «ጡቶቼን ተመልከታቸው ዛሬ በጣም የሚያስቅ ቅርፅ አላቸው» አልኩት።

ሰሚር ነገሩን በቀልድ አላለፈውም። ፊቱም እንደመሸበር ብሎ «ጡቶችሽ እንደበፊቱ አይደሉም። ይህን ከዚህ በፊት አይቻለሁ። ያሁኑ ግን አሳሳቢ ለውጥ ነው ሆስፒታል መታየት አለብሽ።» አለና በሚያጠና አይነት አነካክ የጡቶቼን ዙሪያ ነካ። የግራ ጡቴ ላይ የሚጠጥር ነገር እንዳለ ነገረኝ።

ወደ ሆስፒታል እየሄድን እያለ የእናቴን ስቃይና ነቀርሳ በጣም አስታወስኩ። ከልቤም

«አምላኬ አባክህ የእናቴን እድል አትስጠኝ!» እያልኩ በፀሎት አነበነብኩ። የሚሾፍረው ባሌም ውስጡ የሚተራመሰውን የጡቶቼን ጥርጣሬ እንዳይወጣበት ለማፈን ድምፁን ዋጥ አድርጉአል።

የመጀመሪያው የምርመራ ውጤቱ ለሁለተኛው ተላለፈ። ሀኪሞቹ ያዩትን ለማረጋገጥ ብዙ ዓይነት ምርመራ ተጠቅመዋል። ከደክተሮቹ ፊት ላይ ምን እንደሆንኩ ማንበብ ባያቅተኝም እነሱ ግን በግልፅ ስለህመሜ አላስረዱኝም። የሚሉኝ ነገር ቢኖር ተስፋ

መቁረጥ እንደሌለብኝ ነው። ዶክተሬ ለሆነ ጉዳይ ካለበት ሊንቀሳቀስ የምርመራ ውጤቴን የያዘውን ፖስታ ሰርቁው ወደ ሌላ ዶክተር ሄድኩ።

ለዶክተሩ የእህቴ የምርመራ ውጤት እንደሆነ ዋሽቼው ስለእህቴ መጨነቄን ነገርኩት። ዶክተሮቹም የሆነችውን በትክክል ሳይነግሩን እንደገና ለሦስተኛ እና ለመጨረሻ ምርመራ ቀጠሮ መያዟን ዋሽቼ አስረዳሁት። ዶክተሩ ትንሽ አመነታና በጣም ስለለመንኩት በውጤቴ ስላለው ዝርዝር ነገረኝ። የሰው ልጅ ሊሸከመው የማይችለውን ጭንቀት አሸክሞ ላከኝ።

የመጀመሪያው ዶክተሬ ባሌን አፈላልጎ የሕክምና መዝገቤን ሰርቄ መውጣቴን ነግሮት «በሽተኛዋ እራሷ ላይ የምትፈጥረው ሽብር የህክምና ክትትሏ ላይ ችግር ስለሚፈጥር ነው እኔ ያልነገርኳት» አለው።

ቅዱሱ ባሌ እንደለመደው ከጉኔ ቆሞ ሁኔታዬን በቁጥጥሩ ስር አዋለው።

«ሰሀር ለኔ ስትይ ሁሉን ነገር እንደምታደርጊ ቃል ገብተሻል ትዝ ይልሻል?»

«አዎን»

«በሽታሽን በትክክል ትጋፈጪለሽ። እኔም ይኸው ከጉንሽ አለሁ። ለችግራችን መፍትሄ አብረን እንፈልጋለን። ኑሮአችንን ካሁኗ ደቂቃ ጀምረን ደስተኛ ለማድረግ እንጥራለን እሺ! እባክሽ አግዢኝ።»

ለሰሚር ስል ተመልሼ ለመጨረሻው ወሳኝ ምርመራ እራሴን አዘጋጀሁ። ስካነር የተባለው የምርመራ መሳሪያ የመጨረሻ ተስፋዬ ነበር። ረጅሙ ደረቅ አልጋ ላይ አስተኝተውኝ መሳሪያው ወደሚገኝበት ብርሃናማ ክፍል ለብቻዬ አንሸራተው ሲያስገቡኝ ከዚህ በፊት ከቶ ባልተማፀንኩት አይነት በፀሎቴ ተማፀንኩ።

«አቤት ይህ ሁሉ ስህተት ነው። ጤነኛ ነሽ። ስላስፈራራንሽ ይቅርታ አድርጊልን» ቢሉኝ ብዬም ተመኘሁ። የሆነ ተአምር መቶ እንደነበርኩ ጤነኛ እንዲያደርገኝ ለመንኩ።

ስካነሩ ግን በጡቶቼ አንሰራርቶ የሚገኘውን ነቀርሳ በግልፅ አሳየ። ስለነቀርሳዬ እርግጠኛ ሲሆን ዶክተሩ በቶሎ ለቀዶ ጥገና እንድዘጋጅና ስለበሽታዬ ከባሌ ጋር እያለሁ በግልፅ አስረዳኝ። መላ አካላቴ ተንቀጠቀጠ። አይኖቼ አናንሰው ሊጠፉ እስኪደርሱ አነባሁ። ባሌ አብሮኝ እንዲሆን ባለመፈለጌ ለብቻዬ የሆነ መኝታ አዘጋጀሁ። ባሌም ሳይረብሸኝ ሁኔታው እስኪበርድልኝ እና የነቀርሳዬን እውነታማነት አዕምሮዬ እስኪቀበለው ጊዜ ሰጠኝ። ለማልቀሱ ለማዘኑ አምላክን ለማማረሩ ድክም ብዬ እስክዝል ድረስ ደህና ጊዜ አገኘሁ። ጮህኩ! ፈረጥኩ! አጨስኩ! የተቀየረ ነገር የለም። ብቻዬን ሆኜ ረጅም መንገድ ተጓዝኩ። ረጅሙ መንገድ አዲስ ሀሳብ አስተማረኝ።

በደረቴ የያዝኩትን በሽታ እንደያዝኩት ቁጭ ማለት ያለመፈለግ አዲስ ሀሳብ ውስጤ ሲያድግ ተሰማኝ።

ሚስኪኑ ሰሚርን ለምን አሰቃየዋለሁ ብዬ ባሌ የማኮራ ጠንካራ ሴት መሆን አለብኝ አልኩ።

እቤት ስገባ ጥሩ እራት አዘጋጅቼ ለሰስ ባለ ውስ ተነከርኩና ተቆነጻጅቼ ሰሚርን ጠበቅኩት። ምንም አዲስ ነገር እንዳልተፈጠረ ሁሉ ተሳስቀን ጥሩ ለሊት አሳለፍን። ጠዋት ላይ ስለበሽታዬና ቀዶ-ጥገናዬ በርጋታ አወራን።

በሚቀጥለው ቀን ሆስፒታል አብረን ሄድን። የመረመረኝ ዶክተርም ለቀዶ-ጥገናው ብቸኛ ወሳኝ እኔው መሆኔን ነገረኝ። በነገሩ ለማሰብ ብዙ ጊዜ ባልወስድም እንደሚያዋጣኝ መከረኝ።

እኔ ግን ተስፋ በመቁረጥ «መሞቴ ላይቀር ለምን ጡቴን አቆረጣለሁ። ሳልቆረጥ ከነሙሉ አካሌ ብሞት እመርጣለሁ» አልኩ።

ሀኪሙ ለበሽታዬ የጥርስ ህመምን ምሳሌ ሰጠኝ። በጣም የሚጠዘጥዝሽን ጥርስ ብትነቅይው እፎይታን ታገኛለሽ። ይሽም እንደዛ ነው አለኝ። ከዚህ በፊት ታምሜው በማላውቀው መልኩ የሚያሳብድ ስቃይ በጡቴ ላይ ይሰፍራል። ያኔ አሁን በቀን አራት ጊዜ የምትወስጂው የስቃይ ማስታገሻ ክኒኖች ስቃይሽን መቆጣጠር ያቅታቸዋል። ያኔ ለእርዳታ ወደ ህክምና ስፍራ መሄድሽ አይቀርም። የዛን ጊዜ ለሀኪሙም ላንቺም አስቸጋሪ የሆነ ቀዶ-ጥገና ይጠብቃችኋል። ለበሽታው

በጣም እንዲያንሰራራ ዕድል ስለሰጠሽው **የሚናሩሽን** ኣመታት በስቃይ እራስሽን በመርገም ታሳልፊያለሽ። ነለዚህ እንድንረዳሽ ብቸኛው አማራጭ የግራ ጡትሽን ኦርጦ ማውጣት ነው። ብሎ ተነተነልኝ።

ሰሚር በዶክተሩ ፊት እንባውን አፈሰሰ። ዶክተሩ ነአይኑ ሲገስፀውም አይቻለሁ።

«የኔ ማር! መፍትሄ ነው ያሉት የጡትሽን መቆረጥ ከሆነ እኔን የጡትሽ መቆረጥ አይቀይረኝም። ምንም ነገር ቢሆን በጣም እንደምወድሽ አወቂልኝ። እወድሻለሁ በጣም።» ብሎ ባሌ ጥብቅ አድርጐ አቀፈኝ።

አይኔን ጨፍኜ ለጡቴ መቆረጥ ፈጥኜ ተስማማሁ። ቀዶ-ጥገናውን በማላውቀው አገር ማድረጉን ባለመውደዴ በዚያው ሳምንት ሽርሽራችንን አቋርጠን ወደ ቤታችን መጣን።

የምርመራ ወረቀቱን የተቀበለኝ ሀኪም እላዩ ላይ ተቀባ ልዩ ነገር አለው። ልብ ያሰክናል። በቀላሉ አንዳምነው አደረገኝ። ለቀዶ ጥገናው ስኬታማነት መጀመሪያ በሽተኛው ዶክተሩን መውደድ አለበት። ካልወደደው ወደ ሌላ ዶክተር ይሄድ ዘንድ ይመክራል። እኔ ግን የመጀመሪያውን ዶክተሬን ወድጀው አምኜዋለሁ። እድለኛ ነኝ።

እንደሚሉት ከሆነ ጡቶቼን በየቀኑ መቆጣጠር ይገባኝ ነበር። ይሽን ባለማድረጌ ነቀርሳው ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ጡቶቼን ጉድቶአቸዋል።

እየሾለ ለመጣው ጡቴ ደስተኛ ነበርኩ። ስፖርት ቤት እየሄድኩ ስፖርት እሠራ ስለነበር እስፖርቱ የሰጠኝ ውበት እንደሆነ ነበር የገባኝ። በክንዴ ላይ ለሚወጥረኝ ህመም ቁብ መስጠት አልፈለግሁም። ወጣትነቴን እስከመጨረሻው ብቻዬን እየቦረቅሁ አፍላ ጉልበቴን በስፖርት መገምገም በጣም ያስደስተኝ ነበር። ልጅ ውለጅልኝ እያለ የሚለምነኝንም ባሌን ቀጠሮ አስጠዋለሁ። ሰላሳ ሁለት ወይ ሦስት ሲሞላኝ እወልድልሀለሁ እያልኩ እስከዛ ግን ልጄ አንተ ነህ ብዬ ጥያቄውን እንዲረሳ እየሳምኩ አባብለው ነበር።

የሚገርመው ነገር ስለዚህ በሽታ የተፃፈውን የዶክተሮች አባባል ሳነብ ከሰላሳ ዓመቷ በፊት ልጅ ወልዳ ያጠባች ሴት ለዚህ በሽታ የመጋለጧ ዕድል የቀነሰ መሆኑ ነው። ቆጨኝ። ጥሩ ዕድል አመለጠኝ። ቢያንስ ባሁኑ ወቅት ፀጉሩን እያሻሸሁ የማስተኛው ህፃን ይኖረኝ ነበር። ካሁን በኋላ ልጅ የመውለዱ ነገር የማይታሰብ ነው። ፈፅሞ።

ዶክተሬን ስለበሽታው መንስኤ ጠየቅሁት። ለበሽታው መንስኤ ከግምት በቀር ትክክለኛ መልስ አልተገኘለትም። ብቻ ግምቶቹ ወደእውነተኛው መንስኤ የቀረቡ ዓይነት ናቸው። ጭንቀት የሚፈጥረው የሰውነት መከማተርም ይህን በሽታ ያመጣ ይሆናል ተብሎ ተገምቶአል። አንቺ በምን መጣብኝ ብለሽ እራስሽን አታስጨንቂ ይኼ መሺአትላህ /የአምላክ ትዕዛዝ/ ነው

ብሎ ነገረኝ። እኔ ግን የእናቴ ነቀርሳ ተከትሎኛል ባይ ነኝ።

ሐኪሜ አማራጭ የቀዶ-ጥገና ዘዴዎችን አንድ በአንድ ዘረዘረልኝ። እኔም ጡንቻዎችን በመጠቀም የሚካሄደውን ዘዴ መረጥኩ። ምክንያቱም ይህ ዘዴ የሆድ ስብን ከመጠቀሙ ዘዴ ያጠረ ቀዶ-ጥገና ስለሆነ ነው።

ስለቀዶ-ጥገናው የማስታውሰው ክንውን ወይም ህመም የለም። ከዛ በኋላ ግን ከታሸገው ግራ ጡቴ ይልቅ ግራ ክንዴን ቀፍድዶ ያያዘ ሀይለኛ ህመም ተሰማኝ። ሀኪሜም ሙሉ ጡቴንና ባካባቢው ያሉትን ስቦች ሙሉ ለሙሉ ማስወገዱን ነገረኝ። ፋሻው ሲፈታ ስለሚኖረው ጎድጓዳ ቦታ እንደውም በቀዳዳው ሳንባዬን ወይም ልቤን ስመለከት ብዙ ጊዜ አለምኩ። በሕልሜ ያየሁትን በውኔ ላለመድገም ያ ፋሻ ለዘለዓለም እላዬ ላይ ተጠምጥሞ እንዲቀር ተመኘሁ። እንደኔ ላለች ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ስለሰውነቷ ቅርፅ ለምትጨነቅ ሴት የጡት መቆረጥ ምን ዓይነት የቀን አስፈሪ ቅዠት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። እጀን ወይም አንድ እግሬን ባጣ ከሚለማኝ ስሜት የበለጠ ውስጤ ሲቆስል ተሰማኝ። ባዶ የሆንኩ መሰለኝ። ሴትነቴም ትርጉም እንዳጣ ይገባኛል።

የቀዶ-ጥገናውን ጨርሼ በቀላሉ አልተገላገልኩም። ራዲዮቴራፒ በየቀኑ ለተወሰነ ጊዜ ማድረግ ነበረብኝ። ይህ የህክምና ክትትል ውስጤን እየረበሸው በማስመለስ ብዙ

ተቸግሬ ነበር። ከቤቱ እስከሆስፒታሉ ያለውን መንገድ ለማየት በጣም አስጠልቶኝ የግዴን ደጋገምኩት።

ነገሮች ሁላ እንደበፊቱ አልነበሩም። እቤቱ ስገባ ለሚር በጣም የሚጠላውን የቻይናዎችን ቅመማ ቅመም ለነቀርሳ የሚሰጠውን መድኃኒት/ላይድኢፊክት/ የሚጉዳ መልኩን ይቀንሳል የሚለውን የሀኪሞቹን ምክር ተቀብሎ ኩሽናዬን በቻይናዎቹ ቅመም ሞልቶልኝ ወጥ ቤቱ በቅመማ ቅመሞች አስቀያሚ ሽታ ታምቆአል። እንኳን ምግቤ ውስጥ ገብቶ ይቅርና ሽታው አንገሸገሸኝ። ሰሚር ግን የበሽታሽን ውጊያ የምንጀምረው ከዚሁ ነው ብሎ በቻይና ቅመም የተንተከተከ ሾርባ አስዋጠኝ። ሰሚር እቤት እስክመጣ በካሮት ጭማቂ አጨማመቅ ጀምሮ ሁሉን ነገር ተምሮ ቆየኝ።

ጠዋት ላይ በካሮች ጭማቂ ብቅ ይላል። እራሱ ጨምቆ እራሱ ቁርስ አዘገጅቶልኝ ሠራተኖችንን እንኳን ሳያስቸግር . . . መልአክ ነው።

«አልበዛም?! በጣም አቀበጥከኝ። ስለታመምኩ ነው? እንክብካቤህ . . .»

«እንደምንከባከብሽ ዛሬ ገና ማወቅሽ ያሳዝናል። እኔ ካየሁሽ ጀምሮ ነው እንክብካቤ የጀመርኩት። አንቺ ግን ያየሽው ዛሬ ነው። በፊት በብዙ ነገር በጣም ስለምትጠመጂ የኔን ድርጊት አታጠኝም።»

«ይቅርታ አድርግልኝ ሰሚር የማላይ እውር ነበርኩ።»

እውነቱን ለመናገር እንዴት ይንከባከበኝ እንደነበር በደንብ አውቅ ነበር። ብቻ ባሌ እንደዛ የሚሆንልኝ ለሚያምረው ቅርፄ መልኬ ቁመናዬ ይመስለኝ ስለነበር ባጭሩ ኮራ ብዬ «ይገባኛል!» ብዬ ወስጀው ነው።

ከምወደው እስፖርት በስጋ ከሚሰራው ምግቤ ተለይቼ በምትኩ ነጭ ሽንኩርት። የምጠላውን ነጭ በቁሙ እውጣለሁ። ጠረኔ፣ ትንፋሼ ወይ የቻይናዎቹን ቅመም ወይ ነጭ ሽንኩርት ወይ መድኃኒቶቼን ብሉ ምንም ላሙናና ውሃ ሳይቀይረው የራሴው ሆኖአል።

የሴለሪይ ጭማቂ እና የሲትረስ ፍራፍሬዎችም የግዴታ መጠጦቼ ናቸው። የካሮቱን ጭማቂ ጨምሮ። የሰሚር ቤተሰቦች ሊጠይቁኝ መጡ። አይናቸው ላይ «ሉፍ ልንገላገልሽ ነው። ቶሎ በሞትሽ የልጃችንን ሕይወት ገሀነብ አደረግሽው ለሞትሽ እንፀልያለን።» እንደሚሉኝ አነበብኩ። እነም ተመልሰው እንዳይመጡብኝ በአስተያየቴ ቀጣኋቸው . . . ሰሚር ሳያይ። በርግጥ ደረቴ ላይ የተፈጠረውን ጉደሉ በጭንቀት ለሚቃኙት አንዳንድ አዛኝ ጓደኞቼ አስቀይሜ መለየት ባይኖርብኝም

«ስታሳዝን መሞቷ ነው ቻው አፈሩ ይቅለልሽ» የሚለውን አስተያየታቸውን ልሸከመው አልቻልኩም። «አይናቸሁን ማየት አልፈልግም አትምጡብኝ» ብዬ ከቤቴ ባስወጣቸውም እንደማይጠሉኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

አንዷ ጓደኛዬ አስቀያሚ ፊት ያለው ትልቅ የድብ አሻንጉሊት አመጣችልኝና ተሰናብታኝ ከመሄዷ በፊት

«እንደኔ ከሆንሽ በጣም ስትበሳጪ ይህን ድብ እየሰደብሽ ደብድቢው። እመኚኝ ከዛ በኋላ ውስጥሽ እፎይ ይላል። ይህን የሚመስል ድብ እቤቱ አለኝ የንዴቴ ማብረጃ ነው። ሞክሪው!» አለችኝ።

በእውነቱ ትልቅ እርዳታ ነው።

ፋሽዬ የተፈታልኝ ዕለት ከትልቁ መስታወት ፊት ቆሜ ለማየው ነገር ለመዘጋጀት ከአስር ደቂቃ በላይ ፈጀብኝ። ትንፋሼን ሰብስቤ የቀሚሴን አዝራር መፍታት ጀመርኩ። ፈታሁ። አይኔን ጨፈንኩ። እንደምንም ስገልጠው ያየሁት የራሴን ገላ መሆኑን ተጠራጠርኩ። ጩኸቴን አቀለጥኩ። እራሴን መቆጣጠር ተስኖኝ መስታወት ላይ የማየውን ምስሌን ለማጥፋት ያገኘሁትን ነገር ሁላ መስታወቱ ላይ ወረወርኩ። ቀረብ ብዬ የተሰነጣጠቀውን መስታወት በቡጢ ሳጉነው እንክሽክሹ ወጣ።

ሰሚር ድምፁን ሰምቶ ደረሰልኝ። የሚንዘፈዘፈውን ሰውነቴን እቅፍ አድርጉ በጆሮዬ-

«አይዞሽ ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል» አለኝ። የመስታወቱ ስባሪ የቆረጠውን እጀን አከመልኝ።

በነጋታው ተመሳሳይ ትልቅ መስታወት አስመጥቶ ነይ ብሎ ከመስታወቱ ፊት አቆመኝ። ያደረግሁትን የመኝታ ቀሚስ እያወለቀ አንገቴን እየሳመኝ

«ተቀበይ! ይህ አዲሱ ሰውነትሽ ነው ተቀበይው!» ብሎ አንሾካሾከልኝ።

እረጋ ብዬ የተጉዳ ደረቴን አየሁ። ሰሚር እንባዬን ጠረገ። እጀን ይዞ ደረቴን አብረን ዳበስን። መጥፎ ስሜቴ ሲቀንስ ገላዬን ባለበት ሁኔታ ስቀበለው ተሰማኝ። ሰሚር ተአምረኛ ባል ሆኗል።

ክንዴን ለማንቀሳቀሱ ጊዜ ፈጅቶብኝ ሰሚር እንደሕፃን ልጅ እያቀማጠለ ፀጉሬን ያበጥርልኝ ነበር። ወደመዳኑ ስደርስ አንድ ቀን ሰሚር እንደለመደው እያሳሳቀ ሲያበጥር ድንገት ተንተባተበና ማበጠሪያውን ወደኋላው ሲደብቅ አየሁ። ምክንያቱ በትክክል ባይገባኝም ልጫነው አልፈለግኩም። የችኩል ፈገግታ ፈገግ ብሎልኝ ወደመታጠቢያ ቤት ሲሄድ ቀስ ብዬ በጣቶቼ እየተራመድኩ ተደብቄ አየሁት። የሽንት ቤቱን ውሃ ለቆ ተመልሶ መጣ።

«ሁሌ እኔው እንዳበጥርልሽ ትፈቅጅልኛለሽ?»

«ተገኝተህ ነው»

«አንቺን አላምንሽም የኔ የሆነውን ፀጉርሽን እኔ ሳልናር ታበጥሪብኛለሽ ስለዚህ ማበጠሪያሽን ሁሉ መደበቅ አለብኝ» ብሎ አሳቀኝ።

እኔን ሊያስደስተኝ የማይፈጥረው ስበብ የለም አልኩ። ሽሚዙን ወደቆሻሻ ልብስ ማጠራቀሚያ ስወስድ ማበጠሪያዬን አገኘሁ። ቀልዱን አስቤ እየላቅኩ ባኞ ቤት

ገብቼ ከቀዶ-ጥገናው ቀኔ ጀምሮ አበጥሬው የማላውቀውን ፀጉሬን ማበጠር ጀመርኩ። ፀጉሬን በማበጠሩ ይህን ያህል ደስታ ተሰምቶኝ አያውቅም። እያንዳንዱ የአካሌ ክፍል ውድ መሆኑን በበሽታዬ አውቄዋለሁ። በመቀጪያዬ ጊዜ ይህንን ማወቄ ያሳዝናል። ረጅሙ ፀጉሬን በአንገቴ ወደኋላ መታ አድርጌ ከፊት ያለውን ፀጉሬን ላስተካክል ቀና ስል እጅግ ብዙ ፀጉሬ ማበጠሪያውን ሞልቶ አየሁት። ሰሚር ያስደነገጠው እና ማበጠሪያዬን ያስደበቀውን ምክንያት የፀጉሬ ከልክ በላይ መነቀል መሆኑ ገባኝ። እኔንም ክው አድርጎ አደረቀኝ። የራሪ ቅሌ ብቻውን የቀረ መሰለኝ። «ለምን ይህ ሁላ ይደርስብኛል ምን ክፉ ሰርቼ ነው» ብዬ ወደሰማይ ሳንጋጥጥ ደካማ አይኖቼ እንባ አፈሰሱ። በየቀኑ ሰውነቴ ላይ አዲስ ለውጥ አያለሁ። ነቀርሳዬ ወጣትነቴን ያለጊዜው እንደሚወስድ ሊያስታውቀኝ አይኖቼ ስር፣ ጉንና ጉን በኔ እድሜ ከቶ የማይከሰተውን መስመር አጋደመልኝ። የራሱ እንደሚያደርገኝ እያወቅኩ ዕድሜዬን እንደሚቆርጠው እያወቅኩ ፊቴ ላይ የተመሰመሩትን ሽብሽብ መስመሮች እጅግ ከብደው ታዩኝ።

አይኔ ስር ያለውን አዲስ ሽብሽብ ቆዳዬን ልለጥጥ በጣቶቼ ስታገል ሰሚር እጀን ከፊቴ አነሳና በፈገግታ እያየኝ «ጥሩ ክሬም መጠቀም ትችያለሽ ለምኑ ነው ሀዘኑ!» ባሌ ጣፋጭ ነገር ነው። ተሰብሮ ብትንትን ያለውን ልቤን መጠገኛ ቃላት አያጣም።

«እኔ ጥሩ ክሬም አልፈልግም እኔ የምፈልገው. . .» ተናነቀኝ። «ይገባኛል ሳሀር ይገባኛል ብቻ አንቺ በአላህ ተመኪ ነገ የሚከሰተውን ማን ያውቃል?!»

«መድኃኒት ይገኛል ብለህ ታስባለህ?»

«ይሆናል።» ፊቱ ላዩ ግን «አይገኝም» የሚል መልስ ይነበባል።

ከእርሱ ጥንካሬን አግኝ ዘንድ አጥብቆ እንዲያቅፈኝ መጠየቅ መፍትሔ ሆኖኛል።

ሰሚርም የቤተሰቦቹን ሌላ አግባ ጉትጉታን የኔን ስቃይ ባንድ ላይ አጣምሮ በውስጡ ይዞታል። ፊቱ ግን ምንም ችግር እንዳልተጋፈጠ ሁሉ እኔ ፊት የፈካ ነው።

ቤተሰቦቹ የመጀመሪያ መነሻዬ ክርስቲያን ስለሆነና የሌላ አገር ሰው ስለሆንኩ አልወደዱኝም። የእኔ ወደ እስልምና መቀየር ብቻ በቂ አልመሰላቸውም። ቢችሉ እንዳለ ወደ ሊባኖስ ሄደው ዘርማንዘሬን ቢያሰልሙ ደስታቸውን አይችሉትም። የኔና የሰሚር ፍቅር ግን ሊበገር ያልቻለ በጣም ጠንካራ ነበር። ሰሚር ከልቡ ወደደኝ እኔም ከስሜ ጀምሮ ሀይማኖቴን ሁሉን ነገሬን እንዲቀይር ፈቀድኩለት። አዲስ ስም አወጣልኝ። እኔም ያወጣልኝን ስም አመለኩ። ደጋግሜ ሰሀር እያልኩ ስሜን ተለማመድኩ። ሊባኖስ መጥቶ እያለ ነበር የተዋወቅነው። በፍቅሩ በጣም ሰምጬ ገባሁ። የሚለው ነገር ሁላ ትክክል መሆኑን ልቤ አመነ። ሀይማኖቴን ከመለወጤ በፊት ጥሩ ጥሩ አላማኝ የቁርአን ታሪኮችን ያለመታከት ይነግረኝ

ነበር። ከሁሉም ከሁሉም የመካን ዘምዘም /ጠበል/ ታሪክ ጭንቅላቴን ቀይሶበታል። ወስዶም አሳየኝ።

በዚያ ድብን ባለ ደረቅ ስሀራ ቦታ ላይ የመነጨው ጠበላዊ ምንጭ በእስላሞች የተለየ ታሪክ አለው። አጀማመሩ እንደ ክርስቲያኑ አብርሃምና ሳራን ታሪክ ያወሳል።

ሳራ ኢብራሂምን ከገረዱ እንዲወልድ ከፈቀደችለት በኋላ ገረዲን ከሕፃኑ እስማኤል ጋር ስታያት ትቀናና አርቀህ ውሰዳቸው ትለዋለች. . . ኢብራሂምን። አላህ ለኢብራሂም ልጁን ከነእናቱ ከሳራ ቦታ አርቆ ስሀራማው ቦታ ትቶት እንዲሄድ ይነግረዋል። ኢብራም ሁሉን ነገር በአላህ ትቶ ጭው ባለ በረሀ ሕፃን ልጁን ከነእናቱ ይተወዋል። ቦታው ውሃ የለበት የሚቀመስ የለበት። እናትየው ለልጇ ውሃ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ስትል ሕፃኑ እስማኤል በእግሮቹ ጫር ጫር ሲያደርግ የጠራ ውሃ ከእግሮቹ ስር ፍልቅ ፍልቅ ይላል። ይህ ቦታ ነው እንግዲህ ዘምዘም /ጠበል ውሃ/ በመካ አስካሁን የሚፈሰው። እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ አብሮኝ የኖረውን ክርስቲያንነቴን ባይ ባይ ብዬ ሰሚርን ተከትዬ ወደአገሩ ስመጣ ያኔ ከዘርማንዘሮቹ ጋር ተቆራረጥኩ። በድሮ ስሜም ሆነ በሰሀር ሊጠሩኝ ሊያስቡኝ ሊያዩኝ አይፈልጉም። ረስተውኛል። አባቴም ልጄ አይደለችም ብሎ ቆርጦ ፊቱን አዙሮብኛል። ያን ሁሉ ኪሳራዬን አብቃቅቶ የሚተርፈኝ ልዩ ዓለም ውስጥ ከሰሚር ጋር ገብቼ እኔም በበኩሌ ረስቼአቸዋለሁ። የሰሚር ቤተሰቦችም

ሰሚርን ከኔ ጋር ትተው ቢረሱት ደስታውን አልችልም። በተለይ ከታመምኩ በኋላ። የሚደወለውን ስልካቸውን እንኳን ለመመለስ ተሳቀ ሞቷል።

አንዴ እህቱ ስትደውል በሌላኛው ስልክ ሳዳምጥ «እኔ የምትወዳትን ሚስትህን ተዋት አልልህም። የምትወልድልህን ሌላ ሴት እንድታገባ ሕጉ ይፈቅድልሀል እባክህ አግባ። ስለ እናትና አባቴ አስብ። ስለአንተ መጐዳት በጣም ይሰማናል። ከበሽተኛ ሴት ጋር እራስህን አፍነህ. . .» ስትለው ሰማሁ። እውነቷን ነው አልኩ የሰሚር ጉዳት ተሰማኝ። እኔስ አንዴ ፈርዶብኛል የሱን ሕይወት መበከሌ ግን ራስወዳድነት ነው ብዬ ላናግረው አሰብኩ። እርሱ ግን ሕይወቱን ከሕይወቴ ጋር ጠፍሮ አስሮአል።

ማንኛውንም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒን የግድ ማቋረጥ ስላለብኝ ዶክተሩ ያቀረበለትን ምርጫ ያለምንም ማወላወል ተቀብሎታል። በሁለታችን ያለው ግንኙነት እንዲቀጥል ለወንዶች የሚሰጠውን የወሊድ መቆጣጠሪያ ለመውሰድ ተስማምቶ ወስዶአል። ይኸን የገዛ ዶክተሬ በአድንቆት ነው የነገረኝ።

«እሱን የመሰለ ወንድ በአለም ላይ አጋጥሞኝ አያውቅም» ብሎ።

የእህቱን ስልክ እንደዘጋ የእህቱን ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ መስማማቴን ስነግረው «አንቺ ሕይወቴ ነሽ መቼ ነው ያ የሚገባሽ?!» ብሎ በጣም ሳመኝ።

የዛኑ አለት የስልክ ክሩን አስቆረጠ።

የመጀመሪያውን ቀዶ-ጥገናዬን ባደረግኩ በአሥራ ስምንተኛው ወር በተደረገልኝ ምርመራ በቀኙ ጡቴ ላይ ተመሳሳይ የነቀርሳ ሙሽራ መብቀሉን አረዱኝ። እርሱ ብቻ ሳይበቃ በቀኝ ክንዴ ስርም ይኸው ሙሽራ ቁጭ ብሎአል። በጭላ ድምፅ «አምላኬ ሆይ ሳታሰቃይ ውሰደኝ አካሌ ተቆራርጦ ማለቁ ነው» ብዬ ጮኽኩ።

ሰሚር ይህን ዜና እንደበፊቱ እረጋ ብዬ እንድቀበለው አልገፋፋኝም። በፊት ለፊቴ ጭንቅላቱን ይዞ በድምፅ አለቀሰ። ከዛ በኋላ በጣም ተለወጠ። እንኳን እኔን ሊያፅናና ለራሱም አፅናኝ ፈለገ። «ነገሩ እኮ በበፊቱ ስቃይ ብቻ ያለፈልሽ መስሎኝ ነበር። ስቃይሽ እያሰቃየኝ ታግሼ ስቃዬን በውስጤ ይዤ ፈገግ እል ነበር። አሁን ግን ያን ማድረግ የምችል አይመስለኝም። ሰሀር ይህ ሁላ ይህ ልስልስ ገላሽ ላይ?!» ብሎ ከሚገባው በላይ አዘነልኝ።

የመጨረሻ ያየሁት ቀንም ሀዘንተኛ ፊቱን አልደበቀኝም። ትክዝ እንዳለ ነበር የወጣው። የመኪና አደጋው የእኔን ሕይወት ቢወስድ ምን ነበረበት. . . የሞቱ ብቸኛ ተጠያቂ እኔ ነኝ። ይህ ካንሰሬ ያመጣው ጣጣ የወደፊት ሕይወቴን ብቻ ሳይሆን በህይወት እያለሁም ህይወቴን ሙልጭ አድርጉ ወሰደ። ምንም ጠንክሬ ብገኝም ሞቱ ህይለኛ ሆኖ ጣለኝ። የባሌንም ጭምር ዕድሜ ቀጨ።

የሰሚር እናት ለገላጋይ አስቸግራ ለሀዘን በተሰበሰቡት ሴቶች መሀል «ገፊ ነሽ ገፊ! ልጄን ገፋሹ» ብላ በሰሚር ሞት ተጠያቂ አደረገችኝ። አንገቴን ሰብሬ

«እውነትሽን ነው እኔ ነኝ የገደልኩት ይኸው ከፊትሽ አለሁ ቅጪኝ?! መቼም አምላክ ሰሚርን ወስዶ ከቀጣኝ የባሰ ቅጣት በዚህ ምድር የለም። ሰሚር ላንቺ ልጅሽ ነው። ለኔ ግን ምን ልበል . . . ሁሉም ነገር ነበር።» ብዬ መለስኩላት።

ሰሚር እንዲያቅፈኝ እንዲደብቀኝ ተመኘሁ በዚያች ደቂቃ። ዞር ብል ዞር ብል ሰሚር የለም። ጉሮሮዬን እየመረረኝ እየከረከረኝ ተንሰቀሰቅኩ። በዚያችው ሳምንት እንባዬን አደረቅኩ።

ለሁለተኛው ቀዶ-ጥገናዬ አጠንክሮ ያዘጋጀኝ አንድ ጉዳይ ነበር። «የልጃችን ሚስት ሞቷን የምትጠባበቅ በሽተኛ መድኃኒት በሌለው የጡት ነቀርሳ የምትሰቃይ ሴት ስለሆነች የሰሚር ንብረት ለእኛ ይገባናል። ሰሚስቱ የሚደረገውን ማንኛውም የህክምና ወጪ በቅርብ ሆነን እንከታተልላታለን።» የሚለውን የንብረት ይገባኛል ጥያቄያቸው ነበር ለሁለተኛ ጊዜ ያዘጋጀኝ። ምክንያታቸው ዳኛውን አናዶታል። ንብረቱ የሚስቱ ነው እርሷ የፈለገችውን የማድረግ ሙሉ መብት አላት ብሎ ምንም እድል ሳይሰጣቸው የሰሚር ብቸኛ ወራሽ አደረገኝ። በርግጥ እኔ ይህን ሁላ ንብረት ባለው አጭር ጊዜዬ ምንም ልጠቀምበት አልችልም። ለራሴ አብዛኛውን

ጊዜዬን የማሳልፈው በሆስፒታል ሆኗል። ግን የሰሚር ቤተሰቦች ያደረጉት ነገር በጣም ስላናደደኝ ከሰሚር ንብረት አንዲት ሚስማር እንኳን ለእነሱ ትቼላቸው አልሞትም ብዬ ቀዶ-ጥገናዬን አፋጠንኩ። በሰሚር መሞት ቅስሜ ተሰብሮ ፈጥኜ እንድከተለው የሁለተኛ ቀዶ-ጥገና ችላ የማለት ሀሳብ ነበረኝ። ስቃዩንም የምወደው መስሎኝ ነበር። አሁን ግን እነዚህን ጨካኝ ሰዎች መቅጣት አለብኝ ብዬ የንብረቱን ጉዳይ ለማስተካከል ሰል ብቻ መኖር ፈለግኩ።

ከባሌ ሞት በኋላ በሽታዬን አስታኮ ሊጐዳኝ ወይ ሊጠቀምብኝ የመጣን ሰው በበቂ ሁኔታ የመበቀል አዲስ ፍላጐት አደረብኝ።»

የሁለተኛው ጡቴ ሊቆረጥ ከበፊቱ የባሰ ስቃይ ነበረው። ሦስተኛው ሙሽራም በቀኝ ክንዴ አውጡኝ እያለ አሞጥሙጧል።

ለሶስት ወራት ያህል በየቀኑ ለሀያ ደቂቃ ያህል በራዲዮቴራፒ ስር ደረቴን ሰጥቼ እተኛለሁ። ልብስ ማውለቅ ልብስ መልበስ እራሱ ለጉዳተኛ ክንዶቼ አሰልቺ ነበር። ያን ሁላ ጥርሴን ነክሼ ቻል አደረግኩ።

በፊት የቀረፅኳቸውን የደስታ ቅርፃ ቅርፆቼን ሰባብሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የነቀርሳን ምስል ያዘሉ ሁለቱን ሀውልቶች ቀርጬ ከበሬ በራፍ ግራና ቀኙን አቆምኩ። አንዱ የባሌ ህይወት ላይ የሆነ የውስጤ በሽታ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ እኔው ውስጥ አልወጣም ብሎ ስብዙ

መድኃኒቶችና ቢላዎች አልበገር ብሎ እንድልሻለሁ የሚለኝን ጭራቅ መሳይ ነቀርሳን ይወክላሉ። ባለ ብዙ እጆቹ ይህ ሀውልት ባሌን አዘናግቶ የመኪና አደጋ ላይ የጻረገውን ስራስራሙን ሙሽራ በትክክል ይመስላል።

ይህን በሽታ ከያዝኩበት ጊዜ አንስቶ በየአራት ሰዓቱ የምወሰደው የስቃይ ማስታገሻ ቀለቤ ሆኖአል።

ሁለተኛውን ባሌን ረገብን እዚያው ሆስፒታል ነው ያወቅኩት። የሰሚርን ቤተሰቦች የማደማበት ብትር እየፈለግኩ ነበር። ወጣቱን ጥሩ ማድሚያ ባል ወዲያውኑ አግብቼ እቤቴ ይዤው ገባሁ። ጋብቻችንን የፈፀምነው እዚያው ሆስፒታል ነበር። የሰርጉ እለት ዶክተሬ ነርሴ እና የማላውቃቸው ምስክሮች «መእዙን /በእስላም ሕግ የሚያስተሳስር የመስጊድ ተወካይ/ እና ሙሽራው እኔ ብቻ ሆነን በብርቱካን ጭማቂ ደገስን።

ለነርሴ ሁሉን ነገር እነግራት ነበር። የዚህን ጋብቻ ዋና ምክንያት የምታውቀው እሷ ብቻ ነበረች። የሰሚርን ንብረት ለዚህ ወጣት ትቼለት ብሞት ፅድቅም ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር።

ምን ያረጋል! ረገብ አዲሱ ባሌ ሊያታልለኝ፤ ታሪኬን ከነርሷ ሚስቱ ሰምቶ በኔ ላይ ሻጥር ተማክረው፤ ኮንትራት ጋብቻ ከኔ ጋር ለመፈፀም ሚስትየው የገዛ ነርሴ ስቃዬን ሕመሜን ያየችው ሴት ፈቅዳለት መሆኑን ደረስኩበት። ሁለቱንም ልቀጣ አሰብኩ። እርሷን ባሏን በማታስበው መንገድ ነጥቄ የራሴ ብቻ ላደርገው። እርሱን

ደግሞ ገንዘቤን በማይወደው መንገድ ልግተው. . . ይህንንም እንዳይ አምላኬን እድሜ ጠየቅኩ። ለነርሱም ሆነ ለረገብ ባልና ሚስት መሆናቸውን ማወቁን አላስታወቅኳቸውም። ሲመለሱ እየሳቅሁ ፊልማቸውን አደነቅሁ። የፊልሙ መጨረሻ የኔ ተራ እንደሚሆን ሳስብ ፈነደቅሁ። ሀውልቶቼን ከመቅረፅ በኋላ የሚተርፈኝን ሰዓታት ረገብን በመበቀል አሳልፋለሁ ብዬ ወሰንኩ።

በጫጉላ ጊዜአችን ቡና እያፈላሁለት በውድ ዋጋ የገዛሁለትን ስጦታ አደንዛዥን ዕፅ ከስኳር ጋር አማስዬ አጠጣዋለሁ። እርሱም ቡናዬን እጅግ እየወደደው መጣ። ሱስ እንደሆነበት ሳውቅ ከለከልኩት። ለመነኝ። ሚስቱን በፊት ለፊቴ እንዲፈታ አዘዝኩት። ትዕዛዜን ያለማወላወል ፈፀመ። ነርሴ የምትወደው የአምስት ዓመት ባሏን አጣች። ብልጣ ብልጥ ባሏም ከቀን ወደ ቀን እየተጃጃለ ሸውነቱ እያለቀ እግሬ ስር እንደውሻ ረገጥኩት። የማሸትተው ሀሺሽ የትም እንዳይንቀሳቀስ አደረገው። በቀሌን ጨረስኩ ብሞት ግድ የለኝም።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

የሚስጥሩ ማስታወሻ ደብተር ጉዳይ ከግብፃዊቷ እሙ-ሰዒድ ጋር አቃቃረን። ከዚያች ሴት ጋር ልቃቃር ወይስ ልፋቀር የቱን መምረጥ እንዳለብኝ አላውቅም። የሆቴል ሠራተኛው ባሏ ሥራ እንዲያፈላልግልኝ ስል

ልጣላት አልፈልግም። ግን ደግሞ በነፃ እያሳሳቀች በምታሰራኝ ስበብ እቤቴ ስገባ እራሴን መስታወቴ ላይ ላይ ሞኛ ሞኝ ምስል ስለማይ እበሳጫለሁ።

እራሴን መስታወት ላይ ሳየው የተለያየ ይሆንብኛል። ይህ ሁኔታ ሌሎች ላይ ደርሶ ነግረውኝ ስለማያውቁ ነው መሰለኝ እኔ ላይ ብቻ ያለ ልዩ ልማድ አድርጌ እቆጥረዋለሁ። እሙ-ሰዒድ አጃጅላኝ ልብሷን ሙልጭ አድርጌ አጥቤላት እቤቴ ገብቼ ፊቴን በመስታወት ላይ ለሀጫ የተዝረከረከ ጅላጅሏ እኔነቴን አያለሁ። አብዛኛው ጊዜ ግን ጥንካሬዬንና በራስ መተማመኔን ማየቴ ለስደቱ ምስቅልቅል ህይወቴ ኃይልን ይሰጠኛል።

ታዲያ እሙ-ሰዒድ የደብተሩን ዝርዝር ትርጉም ለለሰጠችኝ ብዙ አስባበት ለአመቤቴ እንደምትናገርብኝ አስፈራርታ የወር ድፍን ደሞዜን ደፍራ ጠየቀችኝ። ይመስለኛል ተመሳሰለብኝ ብላ የምታማርረውን ህይወቷን በኔ ደሞዝ ለመቀየር የወሰነች ትመስላለች።

ሞቷን እየተጠባበቀች ያለችው እመቤቴ የጠቀሰችው አረፍተ ነገር ትዝ አለኝ። «ከባሌ ሞት በኋላ በሽታዬን አስታኮ ሊጐዳኝ ወይ ሊጠቀምብኝ የመጣን ሰው በበቂ ሁኔታ የመበቀል ልዩ ፍላጐት አደረብኝ» የሚለው ታዲያ ሚስጥሯን ያለፍቃዷ ሰርስሬ አውቄ ሌሎቹንም አሳውቄ . . . እሙ-ሰዒድ ከነገረቻች ምኔ ሊተርፍ ነው በሰው አገር ብዬ ፈራሁ።

የግብፃዊቷን ፉከራ ለማክሸፍ ተነኮልኩ። ለአረፍቴ ስወጣ ተዘጋጅቼ ግብፃዊቷ ቤት ሄድኩና

«አንቺ ስለተረጉምሽልኝ ደብተር ለሴትየዋ ልትነግሪ ከወሰንሽ እኔም ለእመቤቴ የምለው አለኝ።»

የቀልድ ሳቅ ሳቀችና በርከክ ብለሽ «ሰም ሂኒ . . . ሰም ሂኒ» /ይቅር በይኝ/ ብለሽ ልታለቅሺ . . . ያ አይሆንም . . . የምትምርሽ ይመስልሻል? ከማረችሽ እንኳን ያለ ደሞዝ ከሥራ ታባርርሻለች ገባሽ?» አለችኝ።

መቼም ልነግራት ያሰብኩትን የተነኮልኩላትን ብትሰማ ከሳቋ ጋብ ብቻ ሳይሆን . . . ባሏን ምን ያህል እንደምትፈራው አውቃለሁ። ፍርሀቷ የመነጨው እርሱ እየሠራ ስለሚያበላት ስለሚያለብሳት የሚፈጠረባት ተፅእኖ እንደሆነ እገምታለሁ።

«ትዝ ይልሻል እህና አፍሪካ አኽዋት /እኛ አፍሪካ ወንድማማቾች ነን ስትይኝ/?»

«ማ አሌሽ /ግድ የለም/ ይቅርታ አድርጊልኝ» ለስለስ አለችና እንደገና የወር ደሞዝ ጥያቄ ላይ ከረረች።

«እንግዲያውስ!» አልኳት «ያን ደብተር እንዳመጣ የላከኝ የሆቴል ሠራተኛ ባልሽ እንደሆነ ዋሽቼ ብነግራትስ? እ! ምን . . . ትል . . . ይ-መ-ስልሻል?!»

ክው አለች ክቤቷ እንድወጣ በትህትና ነገረችኝ። ነገሩን እንርሳው ብላ እራሷው ጠየቀችኝ። ፊቷ ያስቃል። እቤቴ እንደገባሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚያች ግብፅ ቤት

ስመጣ መስታወቴ ላይ የማየው ፊቴ ተቀይሮ ቆየኝ። ፍርስ አስክል በተንኮሌ ሳቅኩኝ። ደግ አደረግኳት ኡሁሁ . . . .።

* * * * * *

አገር ሰላም ብዬ ስራዬን ጨርሼ ክፍሌ ነበርኩ። ቀበጥ ሲያደርገኝ የጨኸቱን መነሻ ለማወቅ ተስፈንጥሬ ወጣሁ። ኮሽታ እንዳላሰማ በጣም ተጠንቅቄ የባልና ሚስት ንትርክ ለማዳመጥ ጆሮዬን በቀጥታ ያሉበት ክፍል በር ላይ አስደገፍኩ።

«ባህቢክ /እወድሻለሁ/።»

«ካም መራ /ምን ያህል/?»

«እልፍ መራ /ሺ ጊዜ/።»

«ውሽታም አንተ መጀመሪያ ወደህ የመጣኸው ገንዘቤን ነበር አሁን ደግሞ የምቀልብህን ዱቄት ነው የምትወደው። ለነገሩ እንዳንተ ያለ ልፍስፍስ እንዲወደኝ አልፈልግም። ወንድ እንዴት ለሴት ይንበረከካል? ይታይህል ተንበርክከህል እኮ ኡሁሁ. . .» የፌዝ ሳቅ የእመቤቴ ድምፅ ነው።

«ይህን ሁልጊዜ ትነግሪኛለሽ። ታስታውሻለሽ ለመጀመሪያ የወንድ ወንድ ነበርኩ። ደግሞ ሁሌ ወንድ

አይደለህም ትይና ወንድ ሁን ብለሽ ናልኝ ትይኛለሽ። ህይወቴን እንዴ ወስደሻታል። እጠላሻለሁ። ያላንቺ መኖር እንዳልችል አደረግሽ። ሰውነቴ ሁላ ሲሰባበር እየተሰማኝ ነው። ዱቄቴን ካልሰጠሽኝ እንደምሞት አውቀዋለሁ ከመሞቴ በፊት ግን እገድልሻለሁ! አንቅሻለሁ! ገባሽ ድምፁ ወደ ህፃን ተቀየረና አለቀሰ «ዱቄቴን የት አደረግሽው?»

«ዛሬስ እንደፈለግክ ብትሆን አልሰጥህም ብዙ ብሬን እንደማፈስበት እወቅ አሁን ሀሳቤን ቀየርኩ ገንዘቤን ባንተ ዱቄት አልጨርስም ሌላ ነገር አስቤበታለሁ»

ምን እንደደበቀችበት ገብቶኛል። የሚያፈላውን ሲያስቅ ሲያስፈነድቅ ሲያዘፍነው የሚያድረውን ነገር ነው። ያ ሁሌ አፍንጫው ውስጥ እንዲገባ በቀሰም መሳይ ካርቶን የሚስበውን ከዛም እሰይ የሚያሰኘውን እፅ።

ይህን ሁኔታ በግልፅ ማየት ከጀመርኩ ሳምንታት ቢያልፉኝም ምንም ሚስጥር ሳይቀር አውቄም እያለ አፍዞ እዚህ ያስቀመጠኝ ምን እንደሆነ እኔንጃ። በርግጥ ሴትዮዋ የካንሰር በሽተኛ መሆኗን ካወቅኩ በኋላ ልተዋት አልፈለግኩም። እንደውም ቀስ በቀስ ልቀርባትና የቀራትን አጭር ዓመታት የእስላም ንሰሐ እንድትገባ ልመክራትም እቅድ ነበረኝ። በሌላ በኩል ይህ ሞት የሚያስፈርደው የጌታዬን ያን መጥፎ ዱቄት መጠቀም የፖሊስ ሁኔታ እያስላለልኩ ባካባቢዬ ያጠረኝን አደጋ ለመጋፈጥ አለመንቀሳቀሴ የሚገርም ነው። በዚያ ላይ የመኖሪያ

ፍቃድ የለኝም። አንዴ ሳሚ ባለበት ስለሀሺሽ ሲወራ ሳሚ የነገረንን ታሪክ አልረሳውም።

አንድ ፓክስቲያናዊት ናት አሉ . . . ሴት ሕፃን ልጅ ይዛለች። ለካ የያዘቻት ሕፃን ትኩስ ሬሳ ናት እና የሆድ ዕቃዋን አውጥተውት ሆዷን በጥበብ ሀሺሽ ሞልተውታል። . . . አቤት ስንት አይነት ቀውጢ ሕዝብ አለ . . . ከዛ ረጅም ሰዓት የሕፃኗን መተኛትና የሴትዮዋን መረበሽ ያስተዋለች አስተናጋጅ ትጠራጠርና ትጠይቃታለች በዚህ ሁኔታ ተያዘች። ሴትዮዋ መፍዘዟ ሞቷን ፈርታ ነው። አውሮፕላን ውስጥ ወደስዑዲያ ሲገባ የሚሰጠው ፎርም ላይ በቀይ ፅህፈት ሞት ለሀሺሽ አጓጓዦች ይላል። እርሱ ይሆናል የሀሺሿን ፓክስቲያን ያርበተበታት።

ጆሮዬን እንዳስደገፍኩ በሀሳቤ ይህ ዱቄት የሚያመጣው ሰበብ ውስጥ በማላውቀው ሁኔታ ብገባና . . . ወዲያውኑ ልብስሽን ጠቅልለሽ ውጪ ውጪ አለኝ። ጌታዬ ማልቀሱን መሮሁን መለመኑን አላቋረጠም። ቆየና «ትሰጪኛለሽ . . . አትሰጪኝም» ብሎ አስፈራራ

«ስበረው ሌላ ኤቀርግለሁ» አለችው ረጋ ብላ። ወዲያው ቧ ብሎ የተፈረካከሰ ነገር ሰማሁ። ድንገት በሩን ሲከፍት ተንደረደርኩና ክንዱ ላይ ወደቅኩ።

«ኦ! ነገር ስትጠቢ ነበር» አለኝ በንዴት። የእመቤቴ ፊትም በንዴት ቀልቷል። እኔም ድርጊቱ አሳፈረኝ።

«ጥሩ ጊዜ ነው የደረሰሽው» ብሎ ሻሼን ጨምድዶ እንደያዘ ቀሰደ «እቃ ሲከሰክስ ቧ ይላል እንደሀውልትሽ፣ ሰው ከፎቅ ሲከሰክስ ምን ድምፅ ይፈጥር ይሆን?» ብሎ ጐተተኝ። ሰውዬው ሙሉ ለሙሉ አዕምሮውን ስቶ የሚያደርገውን አያውቅም።

መጀመሪያ የተቀጠርኩ ሰሞን እያስበረገገ ያስነሳኝ የነበረው ክፉ ቅዠት እውን ሆኖ ከፊቴ ሲራመድ አየሁት። ፀጉሬን ጨምድዶ እየዛተ ወደ ፎቁ መጨረሻ ሲጐትተኝ ለይቅር በለኝ ነፍሴን በሰላም ተቀበላት ፀሎትን ለመድገሙ እንኳን አዕምሮዬ በፍርሀት አልሰከን አለ። በሽንቴ የራሱ እግሮቼም እየተንቀጠቀጡ አልታዘዝ አሉኝ።

«ፀጉሬ ወደመነቀሉ ደርሶአል። ጭንቅላቴ ላይ ያለው ሀመም ሲበረታ እግሮቼን ወደሚጐትተኝ ሀይል አቀረብኩ . . . ተራመድኩ . . . ወደፎቁ ጫፍ ላይ እንደደረስን።

«አቲኒ ሽም ዋላ? /የሚሸተተውን ስጪኝ ወይደሞ!/ ብሎ ታች ላለችው እመቤቴ በማስፈራራት ጮኸ። እኔ ውሳኔዋን አውቄአለሁ። ለእኔ ስትል ያን ውድ ዱቄት አትሰጠውም። ሀውልቷን የምትወደውን ሀይወቴ ነው እያለች የምትደጋግመውን . . . ሀውልቷን ሲሰብር ያልሰጠችው እኔማ ምንድነኝና . . .። ወይኔ መከስከሴ ነው። የዱቄቱን ቦታ አውቀዋለሁ ብዬ እንኳን ለመናገር አማርኛ ብቻ እየቀናኝ ሰውየው አልገባውም አረብኛም

እንግሊዘኛም ጨርሰው ጠፉብኝ በዚያች ቀውጢ ደቂቃ። ተከስክሼ ብሞት እንኳን ጥሩ . . . ያሳሰበኝ የመዳን ጉዳይ ነው። ብድንስ? ፎቁ በጣም ቢረዝም እንኳን እንደሚገድለኝ እርግጠኛ እሆን ነበር። ይሀ አጠር ያለ ነው። እግሬን . . . ወይ እጀን . . . ወይ ጀርባዬን . . . ወይ ደግሞ አእምሮዬን ክጥቅም ውጭ አድርጉልኝ. . . ወይ አልሞት . . . ወይ አልድን ።

ጭው ያለ ሌሊት ስለሆነ ሊረዳኝ የሚሞክር የለም። ራሱን ሊቆጣጠር ያልቻለው ጌታዬ አይኖቹ ደፍርሰው የሞት መላክ ሆኖ ታየኝ።

ዝልፍልፍ ብዬ ልወድቅ ስል ከንዴን ጨምድዶ ብድግ እያደረገ «ለመሞት አትቸኩይ! ደግሞ ማን አንቺን ሊሸከም እና ሊወረውር ነው?! እራስሽው ነሽ የምትዘይው!»

እመቤቴ ለነገሩ በጣም የተዝናናች ትመስላለች

«ካላስ /በቃ/ ተዋት ሀውልት እንደምቀርፅላት ቃል ገብቼላታለሁ። መጀመሪያ ከመሞቷ በፊት ሀውልቷ ማለቅ አለበት። ከዚያ ሀውልቷን በገዛ እጇ ታፀዳለች። ከዛም ለሀውልቷ ታነባለች። ከዚያ እንደፈለግክ ትከሰክሳታለህ!» አለችና ቀለደች። ዱቄቱን ልትሰጠው ተስማማች። ሽንት ሽንት የሚለውን እግሬን እንኳን ለመታጠብ ጊዜ ሳልወስድ በጠዋቱ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

ወዲያውኑ ቦታዬን መቀየር ነበረብኝ። አብረውኝ የተከራዩትን ቅድስትና ሰባህን ማሳመኑ አስቸጋሪ ነበር። አዲስ ሥራ ለመፈለጉም ሆነ አዲስ ቤት ለመከራየቱ ማሰቡ እራሱ ከባድ እራስ ምታት ነው። ለአንድ ወር እንኳን ሥራ መፍታቱ ሲያስከትለው የሚችለው ችግር አመቱን ሙሉ ይጮትታል። ደግነቱ አብረውኝ የተከራዩት እነሰባህ ፖሊስ በጣም ይፈራሉ ሁላችንም የመኖሪያ ፍቃድ የለንም። የምታሰራኝ ሴት በፖሊስ ታስፈልገኛለች ብቻ ማለቱ አስፈንጥሮ ሻንጣቸውን እንዲያዘጋጁ ያደርጋቸዋል።

በዚህ ሁኔታ ከከባዱ ፍርሀቴ እፎይ ብዬ ተገላገልኩ።

ምዕራፍ ስድስት

በዚያን ወር በጣም ብዙ የሳዑዲ ሴቶች የአበሻ ሠራተኛ ይፈልጉ ነበር። ለኔም ይሄ ጥሩ አጋጣሚ ሆነልኝ። ምክንያታቸው የፊሊፒን ሠራተኞችን ከቤታቸው ማስወጣታቸው ነው። እኚህ የሳዑዲ ሴቶች የአንድ አገር ሰው አንድ ይመስላቸዋል።

ነገሩ እንዲህ ነው ወሬው የተናፈሰው ከሌላዋ አረብ አገር ከኩዌት ነው። የኩዌት ሴቶች የቤት ሠራተኞቻቸውን በጣም እንደሚያሰቃዩ ይታማሉ።

እናም አንዲት ፊሊፒናዊት እመቤቷ እንደጋርዮሽ ዘመን እየጠፈጠፈች ታሠራታለች። ፊሊፒኗ በጣም ትማረርና ቂም ትይዛለች። ከዛ የሁለት ወር ዕድሜ ብቻ ያለውን የአሠሪዎቿን ሕፃን የማቀዝቀዣ /የበረዶ መሥሪያ/ ውስጥ ከትታ መሞቱን ስታረጋግጥ ከአልጋው መልሳ ታስተኛውና ዝም ትላለች። ሕፃኑ ሆስፒታል ሲመረመር በሀይለኛ ብርድ መሞቱ ይታወቃል። የሕፃኑ ወላጆች በሕፃኑ ክፍል የተደረገለትን የአየር ማቀዝቀዣ መቋቋም አቅቶት መሞቱን ተረድተው ሠራተኛዋ ሳትጠረጠር የሥራ ጊዜዋን እየተጠፈጠፈች ትጨርስና ወደ አገሯ ትገባለች። አገሯ ሆና ላሰቃየቻት እመቤት የቂም በቀል ደብዳቤዋን ትልካለች። ደብዳቤው የሕፃኑን አገዳደል በቅደም ተከተል ይገልፃል።

ይህ ወሬ ጅዳ እንደደረሰ ወዲያውኑ የፊሊፒን የቤት ሠራተኞች ተፈላጊነታቸው ቀነሰ። እኛ ሀበሾቹ ቦታቸውን ልንተካ መልካም አጋጣሚ ሆነልን።

እመቤቱ አጠር ያለች ሆና ከአገጯ ስር የተንጠለጠለው ስጋ ጉትቻት ይበልጥ ያጠረች ትመስላለች። ያለምንም ስጋ እንቢ ብሎ ለብቻው የተገተረ ዘለግ ያለ አፍንጫዋ ከወደላይ እንደቁራ ምንቃር ሰበር ያለ ነው። ስትናገር የሚያነፋንፋትም ስብራቱ ሳይሆን አይቀርም። ሰውነቷ እጅግ በጣም ወፍራም እያለ ፍጥነቷ የማይታመን ነው። ከቂጧ ጋር ብቻውን የሚንቀሳቀስ አካሏ ሌላ ስም ያሻዋል። እንደው አንድ አሽሚጣጭ አዝማሪ ሽንጧ ሲውረገረግ አቤት ወገቧ እያለ የሚያዜምላት አይነት ነች። ስታወራ ከመጠን ያለፈ እጆቿን ስለምታወናጭፍ የምትለው ከእጆቿ መወራጨት ጋር ዝብርቅርቅ ይልብኛል። ትናገር ትናገርና ብረታማ ጥርሶቿን ፍልቅቅ ታደርጋለች። አንዳንዴ የራሷ ያልሆኑት ብረታማ ጥርሶቿ እየተንገጫገጩ የራሳቸው ጆሮ ሳይዘገንኑ አይቀሩም። ሴትዮዋ የሴት ወዘና የለባትም።

ልጆች እንደሌላት ገና ስገባ ነው የነገረችኝ። ለማየት የጓጓሁት ባሏ ያልጠበቅሁትን ውበት ይዞ ክው አደረገኝ። የገረመኝ ደግሞ በመሀላቸው ትልቅ የውበት ልዩነት እያለ በባሏ ሳትቀና እንደሌሎቹ እመቤቶች የተለመደ ማስጠንቀቂያ ፈፅሞ አላሰማችኝም . . . «ባሌን ቀና ብለሽ ብታይ?! . . .» የሚለውን። እኔም «ፐ ደግሞ ቀሚስ ለብሶ ለሚንጀላጀል ወንዳቸውን ወንድ ብለው . .»

በሚለው ማሽሚጠጤ ፋንታ «ወንዱ እብድ ነውን? ይህን ሁሉ ውበት ለዚች አስቀያሚ እንዴት ይሰጣል። እርሷስ ይህ ሁላ ውበት ያለው ወንድ እንደማይገባት እያወቀች እንዴት ይህን ከባድ የተፈጥሮ ወንጀል ትፈፅማለች!» በሚለው ተካሁ።

የአረብ ወንዶችን በቀሚሳቸው መናቄ ከልብ አልነበረም። ነገሩ ሌላ ነው። የአረቡ ወንዶች በጣም በጣም የሚያጓጉ ናቸው በጣም . . .

«ጆዲድ ሽቃላ /አዲስ ገረድ/?» ጠየቀ

«አይዋ /አዎን/» አለችው

ከአይኑ ስር ሊሸሸገው ያልቻለ ፈገግታ አየሁበት። በጣም እረጅምና ደልዳላ አካል አለው። ልቤ ወዲያውኑ መጨፈር ጀመረ። ግን ቁመቱን ችላ እንዳለ ሰው አይኔን ወደመሬቱ አደረግኩ። ተስማምቼ ሥራ ጀመርኩ።

ልጆች ስለሌሉ ብዙ የሚያደክም ሥራ አልገጠመኝም። ብቻ ወጣትነቴን የሚፈታተን ውበትን ፈርቻለሁ። ቀስ በቀስ ከሰውዬው ጋር ሳላስበው የአይን ንግግር ጀመርኩ። የዓይን ጨዋታ . . . ባይኑ ብቻ።

ከወደመሀል ጥቁር ሰማያዊ የሆነውን የዓይኑን ብሌን ወደ አመዳማ ግራጫ የሚያደላ ወፍራም ክብ ሰርቶ አድምቆታል። የተቀረው የዓይኑ ክፍል ነጭ ነው . . . የንጣት መጨረሻ ነጭ። እንቅልፉ እንኳን ቢመጣ ይቀንሳሉ እንጂ አይደፈርሱም ሁሌ የነፁ ናቸው። በእግር

ጣቶቹንና እጆቹን የወረሰው ፀጉሩ አካላቱ በሙሉ ፀጉር ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። ፀጉር የሞላው ወንድ ውድድ የማደርግ ይመስለኛል። ልክ ሕፃናት እያለን አባ ጨጓሬ እያልን የምንጠራው ተክልን ቆርጠን እጆቻችን ላይ ስናነካካው የሚፈጥረውን ልስላሴ ዓይነት ልስላሴ መሳ አካሌን . . . ገላዬን በመላ በፀጉሩ የሚያጫውተው ይመስለኛል።

ሁሌ ማታ ማታ ሥራ ጨርሼአለሁ ብዬ ለመኝታ ስሰናበት እመቤቴ አይኗን ከቴሌቪዥን ላይ ሳትነቅል

«ነሚ /ተኚ/» ስትለኝ ባሏ ግን ስርቅ አድርጉ የሚያጠግብ ፈገግታ በዓይኑ ይሰጠኛል። ባይኑ ፈገግ የሚል ሲያሰኘው የሚፈነድቅ ቆንጆ ነው ብዬ ተመኘሁት። በማያገባኝ በሚስቱ ስቀና ተሰማኝ።

«ለምን አትወፍር ይህን የመሰለ ገላ እያቀፈች» አንዳንዴ በሀልሜ በዚያ ወንዳወንድ ቁመናው በጣም ሲጫነኝ ደክሞኝ አድራለሁ። የእውነት አብሮ ያደረ ያክል ሰውነቱ በምኞት ድቅቅ ሲል ይውላል።

ምኞቴ ምኞት ሆኖ አልቀረም አንድ ቀን አይኔን ስከፍት የእውነት ከፊት ለፊቴ ቆሞ አየሁት። ያን የመሰለ ወንድ የክፍሌን በር ከፍቶ ካልጋዬ አጠገብ . . . የምሆነው ጠፋኝ። ረጋ ብሎ አልጋዬ ጫፍ ተቀመጠ።

«ባህቢክ /እወድሻለሁ/» አለኝ እኔ ዝም

«ምን አወል ነዝራ /በመጀመሪያ እይታ/» አለኝ። እኔ ዝም

«ሊንቲ ጀሚላ ወቡኒ /ቆንጆና ቡናማ ነሽ/» አለኝ። እኔ ግን ዝም።

ብድግ ብዬ አልፈው ልወጣ ስል ወገቤን ያዘኝ . . ጠንከር አድርጉ መተንፈስ አቃተኝ። ወደ ላይ ብድግ አደረገኝና እንደሕፃን አየኝ። ደግሞ አወረደኝ። መፍዘዜን እርግጠኛ ሲሆን ቀስ አድርጉ አስተኛኝ። ረጅም የመኝታ ቀሚሴን ከእግሩ ጀምሮ እስከ አንገቱ ቀደደው . . . በመንገብገብ ዓይነት። ቢጃማዬ ሲቀደድ ያሰማው ድምፅ ሚስቱን ከእንቅልፏ የሚቀሰቅስ የመድፍ ድምፅ ሆኖ ጉልቶ በጆሮዬ አንጣረረ። በጣም ስለሰጋሁ ከእጁ ተሰፈንጥሬ ተነሳሁ።

«እንዴታ ዳዋ አሻን ትነም /እንድትተኛ መድኃኒት ሰጥቼአታለሁ/» አለኝ። ፍራቻዬን አቃለለልኝ። ግን ደግሞ በውበቱ የሚያታልለኝ ሲይጣን መስሎ ተሰማኝ። ለወትሮ ያስቀናችኝ ወፍራሟ ሚስቱ አሳዘነችኝ ሲጠጋኝ ገፋሁት። እርሱ ግን ሀይል አልተጠቀመም። ዓይኖቹ ብቻ የተለየ ሀይል አላቸው። ልከላከለው የማልችል የውበት ጌታ ነው። እንዴት ላመልጠው እችላለሁ?

የለሰለሱ አረብኛ ቃላት እያለልኝ በትላልቅ እጆቹ እሽት አደረገኝ። ሀሳቤን አንስቼ ለልቤ ፈቀድኩለት። መላ ሰውነቴን የመንከስ ያህል ሳመኝ። እንደዛ ተስሜ አላውቀም። ቀስ እያለ እውስጤ ሲገባ ሀይለኛ ህመም

ተሰማኝ። ሰውነቴን ማንቀሳቀስ አቃተኝ። አቅፎ አነሳኝና ባጭ ቤት ከተተኝ . . . አጠበኝ እያባበለ። አንሶላዎቹን ማጠቢያ ማሽን ከትቶ እስኪጨርሱ በተፈጠረው ነገር እንዳልሰጋ ሌላ ቤት ተከራይቶ እንደአመቤት እንደሚያስቀምጠኝ ቃል ገባልኝ።

ማሽኑ አንሶላዬን አድርቆ ሰጠው። አልጋዬን በትክክል አንጥፎ ሁሉም ነገር እንደነበረ ሆነ ከእኔና ከመኝታ ቀሚሴ በስተቀር። ጠዋት እየታመምኩ ተንቀሳቀስኩ።

በሦስት አራት ቀን ዩስሪ እንዴት ነሽ ይለኛል። ለሊቱን ከኔ ጋር ያሳልፋል . . . ሚስቱን በመኝታ ድባብ ቆልፎባት። እየበዛ ሲመጣ እኔው መቅናት አመጣሁ . . . በወፍራሟ ሴት ። ቅናት ቅጥል ሲያደርገኝ አትንካኝ ስለው እርሱ በእልህ ጭምቅ ሲያደርገኝ ሲያሳምመኝ ብዙ ቆየን።

አነስ ያለች ቆንጆ ቤት ተከራይቶልኝ ሥራዬን ለቀቅኩ። ሴትዮዋ ምንም ሳትጠረጥር ባሏን ይዤ ወጣሁ። ማንም ሳያውቅ ጐጆ . . . ትዳር ግን ላጭር ግዜ። ምግብ ውሃ ሁሉንም ነገር ያመጣልኝና የቶሎ ቶሎ ሳም ሳም አድርጐኝ ውልቅ ይላል።

ለሽርሽር ከከተማ ወጣ ብሎ ከባህር ዳር የተሠሩ ትናንሽ ቪላ ቤቶች ካሉበት ወሰደኝ። «ይኼ ትንሽ ነፃነት አለው ግን የሚፈቀደው ለተጋቡ ሰዎች ብቻ ነው» አለኝ። እኔ ታዲያ «መች ተጋባን እኛ» አልኩት። የደረት ኪሱን

እየዳበሰ «አትጨነቂ» አለኝ የሆነ ወረቀት እንዳለ ገባኝ። ወረቀቱን ለማየት አልጓጓሁም። እንዳልተጋባን አውቃለሁ።

እስካሁን ባአገራቸው ያላየሁትን ውበት አሳየኝ። እኔ ደግሞ ውበት ላይ ከምግብ ጀምሮ የሁሉ ነገር ፍላጐቴ ይቀሰቀሳል . . . ኡፍ ውበት ይገዛኛል። ቦታው ውብ ነው።

የሰማዩና የባህሩ ከሰር ተመሳስሏል። ባህሩ ፀጥ ያለ ነው. . . በዚያ ላይ ጥርት ብሎአል። ከላዩ ላይ የሚነፍሰው ሽውታ ህይወት ነው። በበረሃ ላይ ይህን የመሰለ ውበት . . .። አየሩም በተናጥል ለዚህ ስፍራ ብቻ የተሠራ ይመስላል . . . ቀዝቀዝ ያለ ነው።

ባህር ዳር ተቀመጥን። ሁለታችንም ለለበስነው ልብስ መበሰበስ አልተጨነቅንም። ተቀራርበን ተቀምጠናል። እግሩን በውሃ ውስጥ ከእግሬ ጋር ቆለፍ ፈታ እያደረገ እሩቅ እሩቅ ያያል። እኔ ቀስ እልና አየት ሳደርገው ዩስሪ የማላውቀው ቆንጆ ነገር ይሆንብኛል። የተቀመጥንበት ቦታ ጨምሮለት ነው መሰለኝ ይበልጥ አምሮአል። እሱም እኔን የመሰጠኝ ቦታ እጅግ መስጦታል። በሀሳቤ አረብ ባይሆን ኖሮ ሰዓሊ ይወጣው ነበር አልኩ. . . እነሱ ክልጅነታቸው ጀምረው የሚጫናቸው ከባድ ድሎት አሟሙቆ ስለሚያስተኛቸው ደስታ ፍለጋ አይደክሙም ለስዕል . . . ለፅሁፍ።

አካኋኑን ሳይለውጥ የአገጩን ፂም ሳብ ሳብ እያደረገ በአንደኛው እግሩ ከጣቱ ጀምሮ ወደ ጭኔ . . . ቀስ እያለ ወደላይ ወጣ። እኔም የባህሩ ውሃ ሞቅ እያለ የመጣ መሰለኝ። ሙቀቱ ደስ ይላል። ለስለስ ያለ ነው። የዩስሪ እግርም።

እኔ ስቁነጠነጥ እሱ ግን ርቆ ሄዶ ወደ ሄደበት ሊሰበኝ ይሞክራል። ተጠጋሁት አሁንም አያየኝም ብቻ እግሬን እንደቅድሙ ደጋግሞ ያደርጋል። መላ ሰውነቴ ጋለ። ወደ ባህሩ ሳይ ባህሩ ለእኔ ብቻ የተንጣለለ የራሴ መሰለኝ። እጀን በውሃ ውስጥ ከተትኩና ስነካው እርሱም ከእኔ የበለጠ እንደፈለገኝ ተረዳሁ። ዞሮ አላወራልኝም። እንደሚፈልገኝ አልነገረኝም። ከቤት ውጪ የፍቅር ተግባራት ነውር ነው። እራሴን ወደባህሩ ገፋሁና ውሃው እስከአንገቴ አለበሰኝ። የድንብሩን አካባቢውን አየና «ሌብ /ነውር/» አለኝ። የክፍላችንን ቁልፍ ሰጠኝና «ሂጂ እከተልሻለሁ» አቃሰተ።

እክፍል ውስጥ ብቻችንን ስንሆን ዩስሪ የተለየ ነው እብድ ይሠራኛል። በሴትነቴ እስካመልክ ድረስ እየካበ በአይኖቹ ፍቅር መበተን ይችልበታል። አይኖቹን ፍዝዝ ካደረገ ቁንጅናው ይበልጥ ይገንና ውበት ወዳጁ ልቤን ቅልጥ ያደርግብኛል። አንዳንዴ እራሴን በእንባ ስታጠብ አገኘዋለሁ።

ከሽርሽሩ መልስ አዲሷ ቤታችንን ቆልፎብኝ ሲሄድ ግን እስኪመጣ ብዙም አልናፍቀውም። ፍቅር ናፍቆትን ያስከትል የለ? እኔ ግን በግማሽ ፍቅር ተጠምጄ ወይ ጉድ ማለት ጀምሬአለሁ። እኔ የማፈቅረው ሲዋብ አይኖቹ ሲፈዙ ብቻ የመሆኑ ጉዳይ ገርሞኛል።

ነገሮቹ ሁላ በፍጥነት አድገው በፍጥነት ሊጠፉ ነው። ብዬ ብዬ ስለሚስቱ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት። ለምን እንደሆነ እራሴም አላውቅም። ከሁለት ሳንዱ ሁኔታዬ እንደሚሆን ግን አርግጠኛ ነኝ። ስለሚስቱ ሲያወራልኝ በቅናት ነድጄ እየከሰመ ሊሄድ የተቃረበውን ፍቅር እፍ ብዬ ለማንደድ ወይ ደግሞ ስለ ሚስቱ ሲያወራልኝ ምንም ሳልቀና እየጠፋ የሄደው ፍቅር እፍ ብሎ ጨርሶ ለማጥፋት . . . እራሴን አዘጋጀሁ።

«ስለሚስትህ ንገረኝ»

«ሚስቴ እንዳየሻት አስቀያሚና ወፍራም ሴት ነች»

«ታዲያ ምኗ ነው . . .»

«ታውቂያለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሚስቱ ለሌላ ሴት ፍላጐት ሲኖረኝ! ምናልባት በህይወትሽ የመጀመሪያው ወንድ ስለሆንኩ ይሆን እንዲህ ስለሁሉ ነገር የማወራልሽ? ብቻ ምን ያህል ጥሩ ልጅ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ?» ሳመኝ።

የፍቅር ጨዋታ ውሰጥ እንዲገባና ውይይታችንን እንዲያበቃ አልፈለግኩም። ለወሬው ብቻ ሳይሆን ፍላጐቴ ቅዝቅዝ ብሏል . . . ዩስሪ አጠገቤ ሆኖም። ያ ሁሉ የጋለ ስሜት የት ገባ? ስለፍቅር ብዙ ሲባል ሰምቼአለሁ።

ላጭር ጊዜ አፍቅረው ቶሎ የሚረሱ ዓይነት ሰዎች እንዳሉም አውቃለሁ። እኔ ከእንደነሱ አይነት ሰዎች አንዷ እንድሆን ፈፅሞ አልመኝም። ይሉኝታም በጣም እየተሰማኝ መጥቶአል። በዚች ሦስት ወራት ዩስሪን በቃኸኝ ማለቱ የእብደት ያህል ተሰማኝ። በየሦስት ወራቱ የሚያክትም ፍቅር የሚይዘኝ ፍጡር ከሆንኩ በህይወት ዘመኔ የስንት ፍቅር ባለቤት ልሆን ነው?! ወይስ የያዘኝ ፍቅር አልነበረም?! ያ ሁሉ ቃጠሎስ ሌላ ስም ይኖረው ይሆን?!

ዩስሪ የሚስቱን ገለፃ ቀጠለልኝ።

«ሚስቴ እስከሁን ካየኋቸው ሴቶች ሁላ የተለየች ናት ማለቴ ከእናቴ እህቶቼ ከዚህ በፊት ካየኋቸው ፍቅረኞቼ . . . ከሁሉም።»

አቋረጥኩትና «ዩስሪ ሚስቴ አትበል በኔ ፊት በስሟ ጥራት»

«ለምን? ትቀኛለሽ?» የደስታ ፊቱ ቦግ አለ፡

«አይ ሳይሆን . . .»

«እሺ ልቀጥልልሽ ሚስቴ . . . ይቅርታ . . . ናዲያ ሁለት ወንድማማቾች የወለዱን የአጐት ልጆማቾች ነን። በልጅነታችን ጊዜ ብቻዋን የመሆን ልማድ ስለነበራት ምንም የልጅነት ትዝታ ከእርሷ ጋር የለኝም። ስንጋባ የመረጥኳት እኔው ነበርኩ። እናቴ በተለይ አስቀያሚነቷን እንደ ትልቅ ነውር ቆጥራ ሰርጉ

እንዲሰናከል ብዙ ጥረት አድርጋ ነበር። እኔ እንግዲህ እንዲህ ነኝ ሚስት ስመርጥ። ሚስቴ ለእኔ ብቻ መሆን አለባት ባይ ነኝ። ቆንጆ ከሆነች ብዙ ነገሮች ይጋሩኛል። ወንድ ማለቴ አይደለም። የሳውዲ ሴቶች የሚያደርጉት ግብዣ ብዙ ነው። እንደውም ብዙዎቹ ግብዣ ህይወታቸው ነው። ይጋብዛሉ ይጋበዛሉ ይለብሳሉ ይፈነድቃሉ። ይህ ሁላ ባላቸው ትከሻ ላይ ነው። እንደምታውቂው ሚስቱን የሚያሠራ ወንድ ወንድ አይደለም የሚል ባህላዊ ተፅእኖ አለ። ወንድ ይሠራል ሚስት የሠራውን ሁላ በግብዣ ምሽት ውድ ቀሚሶች አፍሳ ትጨርሳለች። በተለይ በተለይ ለአራሳቸውና ለልጆቻቸው በቂ ነው ብለው የገመቱትን ሀብት ከያዙ የተትረፈረፈ ሀብት የሚያመጣባቸውን ሰበብ ለመቅጨት ጥሩ የገንዘብ መበተኛ ዘዴአቸው ግብዣቸውን ማብዛት ነው። በግብዣ ወቅትም ተሰብስበው የባላቸውን ንብረት የመቀነስ ወይም በራሳቸው ስም ለማድረግ ውጥን ይወጥናሉ። ሞኞች ናቸው። በርግጥ ሁለተኛ ሦስተኛ ሚስት ለማግባት ገንዘብ ወሳኝነት አለው። ይህን የሚያደርጉት ባሎቻቸውን ጠልተው ሳይሆን ሀይማኖቱ እና ሕጉ የሚፈቅደውን ከአንድ በላይ ጋብቻ እንዳይፈጠር ለመከላከል ነው። ታዲያ በሌላ ጐኑ ሚስት እንዲያገባ መገፋፋታቸውን አያውቁትም። ሌላ ጋብቻ የመፍጠሩ ሁኔታ የሚፈጠረው በገንዘብ ብቻ ይመስላቸዋል። በዚህ መንገዳቸው የባላቸውን ህይወት አሰልቺ ማድረጋቸውን አያገናዝቡም። ይህን ሕይወት ከማግባቴ በፊት በታላላቅ እህቶቼ በእናቴ በአጐቶቼ በሁሉም አይቼዋለሁ። ታዲያ

ቆንጆ ሴት ካገባሁ እንደፈለግኩ ላደርጋት አልችልም ብዬ ናዲያን አገባኋት።

ካገባኋት በኋላ ግን ይህችን ሴት የሴቶች ሁሉ ቁንጮ አድርጌ እንዳከብራት የሚያደርገኝ ብዙ ባህሪያቶችን አገኘሁ። እርሷን በማግባቴ በየቀኑ ደስተኛ ሆንኩ። ይገርምሻል ናዲያ ሙሉ ነፃነትን ሰጠችኝ። ማውራት የምፈልገውን አወራላታለሁ . . . ካልፈለግኩ አትጠይቀኝም። የት ሄድክ ከየት መጣህ አትልም። ዝም ያለች ናት። እና ይህ ሁኔታዋ ከእርሷ ያላገኘሁትን ቅጥነትና ቁንጅናን ከሌሎች ባገኘሁ የማትቃወም መሆኗን አረጋገጠልኝ። ህይወቴ የእርሷ እንደሆነች ታውቂያለሽ? ከእርሷ ፍፁም ሰልችቼ አላውቅም። የምሳ ሰዓትና እራት ሰዓት አሳልፌ አላውቅም። በጣም እንዳከብራት አክብራኛለች። ስሜቴን የሚነካ አንድ ቃል ተንፍሳ አታውቅም። ይህች ሴት እራሷን ጠንቅቃ ያወቀች ብቸኛ ሴት ነች። ብዙ ጊዜ ሴቶች ባሎቻቸው ወደሌላ ሲሄዱ ምንድን ነኝ ብለው እራሳቸውን በትክክል ከመገምገም ይልቅ ሽንጣቸውን ይዘው «ከእኔ በምን ትበልጥና ነው እርሷ ጋር የሄድከው» ብለው ይንጣጣሉ። እኔ ልሰጥህ ያልቻልኩት ምንድን ነው ብለው እራሳቸውን አይጠይቁም። እርግጠኛ አይደለሁም እንጂ እኔ ከተለያዩ ቆንጆዎች ጋር እንደምተኛ ሚስቴ ሳታውቅ የምትቀር አይመስለኝም። ዝም ብትልም ሞኝ አይደለችም። ግን ውበት እንደሚሰለች ታውቃለች። ውበት ይሰለቻል። ስለዚህ የማይሰለቸውን የህይወት እርጋታን ትሰጠኛለች።

ሚስቴ የማይሰለች ውብ የሆነ . . . ውስጧ ቆንጆ ነው። ሥራዬ ሳይሳካልኝ ሲቀር ታረጋጋኛለች። ከውጭ ተናድጄ ስመጣ ታረጋጋኛለች። ከጭቅጭቁ ዓለም በሬን ከፍቼ ስገባ ርጋታ የሞላበትን ንፁህ ቤቴ ውስጥ ለእኔ ተብሎ በየቀኑ የሚቀየር አበባ ንፁህ አየር ንፁህ ሴት ንፁህ አልጋ ጣፋጭ ምግብ ይቆየኛል። እኔ ያለ እርሷ መኖር አልችልም የጐደላት ቁንጅና ነው ቁንጅናን ባሰኘኝ ጊዜ ከሌሎች አገኘዋለሁ። ከሌሎች ሴቶች የማይገኘውን እርሷ በትልቁ ይዛዋለች። በጋብቻዬ ደስተኛ ነኝ። ሁሉም ጓደኞቼ ስለጋብቻቸው ሲያወሩ ጀሀነብ ነው ይሉኛል። ናዲያ ህይወቴን ገነት ውስጥ ከታታለች።»

አልቀናሁም። ሴትዮዋ አሸነፈች ሁሌም ታሸንፋለች። ጐበዝ ሴት ናት። ህይወትን አውቃበታለች። ባሏን አሸክርክሮ ወደርሷው የሚሰብ ከባድ ማግኔት አላት።

ደግሞም ዩስሪ ከእኔ ፊልም የመጣውን ነገር ስለነገረኝ እፎይታ ተሰማኝ። እኔም ውበቱን አይቼ ነበር የወደድኩት እውነቱን ነው ውበት ይሰለቻል። ተሰለቻችተናል . . . መሆኑ ነው። ለማንኛውም ውብ ወራትን አብረን አሳልፈናል።

የረመዳን ፆም ሊገባ ሦስት ቀናት ሲቀረው ስለፆሙ አስረዳኝ። «በረመዳን ወር ስህተት አይሠራም። በርግጥ በሁሉም ወቅት ስህተትን መሥራት ሀይማኖቱ ቢከለክልም ይህ ወር ግን የተለየ የሚያደርገው የሰው ልጅ

ለጌታው እራሱን በሕግጋቱ ተገዥ ለማድረግ አክብሮቱን የሚገልፅበት ልዩ ወር ነው። በመፆምም ይቅርታን ይጠይቃል። ወንድ ያለጋብቻ ከሴት ጋር መተኛቱ ሀጢያት ነው። ይህንን ስህተት እንዳይሠራ አላህ ወንድ ያማረችውን እንዲያገባ የጋብቻ ቁጥርን ለወንድ ከፍ አድርጉአል። በየታ ጥያቄ ወንድ ከሴት ደካማ እንደሆነ አላህ ስለሚያውቅ ወንድ ከአንድ ሴት በላይ እንደምታስፈልገውም ለእኛ ተረድቶልናል። ግን ከጋብቻ ውጪ ሀራም /ሀጢያት/ ነው። እኔም ይህን ሀጢያቴን ማፅዳት አለብኝ። ስለዚህ እኔና አንቺ በሰላም እንለያያለን። ጥሩ ልጅ ነሽ።»

ምክንያቱ ይህ መሆኑን አልጠበቅኩም እንጂ ከሁለት አንዳችን የመዝጊያ ንግግር እንደሚጠበቅብን አውቄው ነበር። የፍቅሩም ነገር ሲያልቅ ታውቆኛል። እኔም የምፈልገው ውሳኔ ይህ ነበር . . . መለያየት። ብቻ ከዩስሪ ጋር መቀያየሙን አልፈለግኩትም። ጠንካራ ምክንያት ሰጥቶኛል . . . ረመዳን።

ፈገግ አልኩና የውሸቱን

«በቃ . . . አ . ረመዳን ሲያልቅ እንደገና እንገናኝ»

«በአላህ ልታሾፊ እየሞከርሽ ነውን? እንዳልጠላሽ ደግሞም የሰው ልጅ አንድ ስህተትን የሚሠራው አንዴ ብቻ ነው። አል መሰል ቢኡል ላይውልዳእ ኢብን አዳም ምንጁሀሪን መራቴን /የአዳም ልጅ በእባብ መርዝ ሁለቴ አይወጋም/ ይላል ተረትና ምሳሌው። ካንቺ ጋር

ላደረግኩት ስህተት ይቅርታን ጠይቄ ተመልሼ ካንቺው ጋር ስህተት መስራቴ ህፃን አያስብለኝም?»

«እውነትም፣ ህፃን ነህ! ስቀልድህ ነው! በዚህ አይነት ከሚስትህ ሌላ ሁለተኛ ከሌላ ጋር አትተኛም ማለት ነው?»

«አ .... ይህ የታወቀ አይደለም። እኔ ለእራሴ በሀይማኖት ታስሬ ከናዲያ ጋር ብቻ ብተኛ ደስ ይለኛል። ግን ሴቶች ሰይጣኖች ናቸው። እኔም ደካማ ነኝ። አይሆንም ማለት አልችልም። ሌላ አንችን የመሰለች ሴት ስታሳስተኝ ደግሞ የሚቀጥለውን አመት ረመዳን የይቅርታ ፀሎት ከማድረጌ በፊት ከሀይወቴ አወጣታለሁ። እኔ እንዲህ ነኝ።»

«በያመቱ ሴት ስትቀያየር ጀህነብ መግባትህ ነበር። ረመዳን ባይኖር።»

«ካንቺ ጋር ግን ረጅሙ ነበር። በርግጥ አሳብደሽኝ ነበር። ሁሉን ነገር ትችይበታለሽ። ጥሩ እድል እመኝልሻለሁ። ስራ እስክታገኚ ድረስ እንዲጠቅምሽ ይህን ብር እንቺ። ደግሞ ስራ ቦታ እንደ እኔ ሊያታልልሽ የሞከረውን አይቻልም በይ። የወንዶች ፀባይ እንግዲህ በእኔ አይተሽዋል ብልጥ ሁኚ።»

ሁለታችንም የፊለግነው መለያየትን ስለነበር አልተጨቃጨቅንም ነበር ከመውጣቱ በፊት ግን የመጀመሪያ ጊዜ የሳመኝ አሳሳም አይነት ምጥጥ አድርጉ

ሳመኝ። እኔም በቀልድ ሸኘሁት። የሰውነት ቅርፄን ጠንቅቆ ያወጣ ቀሚስ አድርጌ

«ይህን ሁላ ጥለህ ልትሄድ?» አልኩት

«ረመዳን ባይመጣ.... » አለኝ።

ሀሳቡን እንደመቀየር አለና ተመለሰ። እኔም ለመጨረሻ ጊዜ ከዩስሪ ጋር መተኛቱ አስደሰተኝ። ከዚያ በኋላ ግን አልተመለሰም።

ምዕራፍ ሰባት

ስራ ለማግኘቱ ላበሻ ይቀላል። ምክንያቱ በውድ ዋጋ መስራታችን ነው። የንጉስ ዘር ቤተሰቦች ርካሽ ነገር ስለማይወዱ በርካሽ ለሚሰሩት ፊሊፒኖች፣ ባንግላዴሾችና፣ ሱማሌዎች ብዙ ቦታ አይሰጡም። ፊሊፒኖችና ባንግላዴሾች በሆነው ዋጋ በርካሽም ቢሆን የሚሰሩት የሳውዲው ብር ወደ አገራቸው ሲመነዘር ከበድ ያለ ዋጋ ስለሚኖረው ነው።

ሌሎች ደግሞ አሉ በደም የንጉስ ዘር ያልሆኑ ግን በገንዘባቸው ከንጉስ ዘር እኩል የሆኑ ስማቸው ሼክ ይባላል። ታዲያ ስሙ በሼክ የሚጀምር የናጠጠው ነው። እነዚህም እኛኑ ለማሰራት ይፈቅዳሉ።

አንዳንዶቹ ደግሞ የንጉስም ዘር ሳይሆኑ ሼክም ደረጃ ሳይደርሱ ገንዘብ አለን ለማለት ሲሹ እኛን ይቀጥራሉ። ታዲያ እነርሱ ጋ መቀጠር ይለለቻል። ጥሩ ልብስ እንደሚያሳዩ ሁሉ የአበሻ ሰራተኛ በውድ የሚያሰራ ሀብታም ነኝ ለማለት በየድግሱ ቤት በየጓደኞቻቸው ቤተዘመድ ቤት እነርሱን መከተል ያስፈልጋል።

እንደነዚህ አይነት ሰዎች ቤት ስራ ስጀምር ከስን ስርዓት በላይ የግዙት ትህትና መማር ነበረብኝ። የእመቤቴ ጓደኞች ወይ ይመጣሉ ወይ ደግሞ እርሷ

መሄድ ስለነበረባት አባያዋን በክብር እንዳወልቅላት ይዛኝ ትዞራለች።

የሚያወሩት ወሬ ስለልብስ ስለባሎቻቸው ስለጌጣጌጥ ወይንም ስለ ውጭ አገር ሽርሽራቸው ብቻ ስለሆነ አሰልቺ ነው። እኔም የእመቤቴ እግር ስር በርከክ ብዬ ስለምቀመጥ ያኔ አያቴ የነገረችኝ የካፐቱሼ ታሪክ ትዝ ይለኛል። ካፐቱሼ የጥንት ምስኪን ገረድ ታሪክ ነው። ታሪኩ ድሮ በጣም ስለሚያሳዝነኝ አያቴን ደጋግሞ ተረቱን እንድትነግረኝ እጠይቃት ነበር። አሁን ግን ያን ተረት ጠላሁት። እራሴን በማላውቀው ሁኔታ ካፐቱሼ እያልኩ ማሰቡ ዘግንኖኛል።

ብዙም ሳልቆይ ቀበጥኩ። የካፐቱሼ ታሪክን ለደቂቃ ልቀይር ሳስብ ጉድ ሆንኩ።

በእንቁዎች የተጠለፈ እጅግ ውድ የእራት ቀሚስ እመቤቴ ገዝታ መጣች። ቀሚሱ ከሳንድሬላ የለስማት ቀሚሶች የበለጠ እጅግ ያማረ ቀሚስ ነው። ከላይ ጀምሮ እስከታች እንደላስቲክ ይለጠጣል። ሴትዬዋ ሳምንቱን ሁላ በጉጉት እያወራች ለምትጠብቀው የእራት ምሽት ያዘጋጀችው ነው።

ሰዎቹ ሲወጡ ከሁለት ሰዓታት በፊት እንደማይመለሱ በጣም እርግጠኛ ነበርኩ። ያን ቀሚስ በክብር ከተሰቀለበት መስቀያ በድፍረት አወረድኩና አልጋ ላይ ዘረጋሁት። ፊቴን በሚገባ ታጥቤ ፀጉሬን የራሴ ክፍል ሆኜ በደንብ አስተካክልኩና የእመቤቴ መቆነጃጂያ ወንበር ላይ ጉብ አልኩ። ከፊት ለፊቴ የተደረደሩትን

የፊት ማዳመቂያ ዱቄት የአይን ማስዋቢያዎችና የከናፍር እርሳስና ቀለም ሁሉንም ልክ ሴትዮዋ እንደምታደርገው በጥንቃቄ ተቀባባሁ። ፈገግታዬ የእርሷኑ መሰለ። አካሄድም ኮረጅኳት። የከናፍሬ ቀለምና ኩል ቀሚሱን እንዳይነኩብኝ እየፈራሁ አጠለቅኩት። በጣም ያምርብኛል። ቀሚሱ የሰጠኝን የራሴኑ ቁንጅና ሳደንቅ ደቂቃዎች አለፉ።

ሙዚቃን ፈለግኩ፤ በምቱም መውረግረግ አሰኘኝ። ሙዚቃ ከፍቼ ስውረገረግ ስሽከረከር በየግድግዳው ያሉ አንፀባራቂ መስታወቶች እራሴን ስድስት ሰባት ቦታ እያባዙ ከጮን ከኋላ ከፊት ሲያጀቡኝ የቀሚሱን ባለቤት ረሳሁ።

በር ሲከፈት የሰዎች ኩቴ ሰምቼ ችላ ልበል ወይስ አልሰማሁም ብቻ ዞር እንዳልኩ የእመቤቴን ቁመና እንደኔው በየመስተዋቱ ስድስት ሰባት ቦታ አየሁ። ያለችበትን አቅጣጫ በትክክል ለማወቅ ለመጨረሻ ጊዜ በዚያ ነብስ ቀሚስ ተሽከረከርኩ።

ጉንጭዋ ቲማቲም መስሎ ልትበጭቀኝ የተዘጋጀች ትመስላለች . . . ኖራ መሳይ ነጭ ቀለም የተቀቡ ረጃጅም ጥፍሮቿን እንደውሮ ቀስራዋለች። ደነገጥኩና የራሴ ያልሆነውን ቀሚስ ጭምቅ አድርጌ ስይዘው በጥንቃቄ ከተጠለፉት እንቁዎች የምታምረዋ ሮዟ ተበጥሳ ንጥር እያለች እመቤቴ እግር ስር ደረሰች።

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ እራሴን ከስራ ተባርሬ አቤት አገኘሁት።

ምዕራፍ ስምንት

የቆንጆ መኪና ስሞችን እንደሻጭ ከነዋጋቸው አጥንቼአለሁ። እነ ሮዝራይስ ካዲላክ ሌክሰስ . . . ሌሎችም እያልኩ። ቢመሽም ባይመሽም ከጉንና ጉናቸው የተሸጉጠላቸው አንቑል የመኪናውን ከለር ሳይቀር ለመለየት ያስችላል። የታርጋ ልዩነትንም ጠንቅቄ አውቄአለሁ። የግል ወይም የድርጅት ስለመሆኑ።

ችግሩ አንዳንድ የሀብታም ተቀጣሪ ሹፌሮች በተለይ ሊባኖስና ግብፆች ሶሪያዎች የመኖች ከስዑዲዎች ጋር የመልክ ልዩነት ስለሌላቸው እንደጌቶቻቸው ለብሰው የሸፈሩ ጊዜ ነው።

የገንዘብ ማግኚያው ነገር የቀለለ ይመስላል። አዕምሮዬ ዛሬ ገና የመሸጡን ነገር አምኖበታል። ስራ እንዳላፈላልግ «ቅድስት የለች! በማን በኩል ማን ተያዥ ይሆነኛል?» አለዋለሁ እራሴን ሳሳምን። ስራ ማጣቴ ሳይሆን ስንፍና ተደርድሮ ደፍ ብሎ ወድቆብኛል . . . . ላዬ ላይ። ኩሩው አስተሳሰቤ ቀለለና ለመቅለሉ ሙሉ ነፃነት ሰጠኝ። አጋጣሚዎች ብቅ እያሉ የነአይሻን መንገድ ማየት አለብሽ ይሉኛል። እኔ ከማን እበልጣለሁ ስደት የሚጋርደውን ሁሉን ነገር መቅመስ ደግሞ መጥፎ

አይደለም ብዬ ስለተቀበልኩ ውሰጤ ወደ መሸጫው ቦታ ግፍት እያደረገ አቀረበኝ።

ሀብታሞች የሚገበያዩበት ሱቅ ሄድኩኝ። አባያዬን በሻንጥ ሙልጭ አድርጌ አጥቤ አሳምሬ ተኩሼዋለሁ። ዕቃ የምገዛ አስመስዬ በአይኖቼ ሊያየኝ የፈለገ እንዲለ ገልመጥመጥ አልኩ። ሁኔታዬ ስለሚያስታውቅ ሁለት ወንዶች ተከተሉኝ። በአይኔ ሀብታም ወደመሰለኝ ሰው አዘነበልኩና አንደኛውን ጠፋሁበት።

ሁለተኛውን ሰውዬ በአይኔ ጠቀስኩትና ወደ አንድ ሱቅ ዘው አልን አንድ ላይ።

አልተርበተበትኩም ይልቁንም ባንዴ ከፍ ምንጥቅ የማለት ጥልቅ ፍላጐትና ድፍረት ሰጠኝ . . . ማን ሞኝ አለ አልኩ ለራሴ . . . ማን ሞኝ አለ በትዕግስት ደረጃ በደረጃ የሚወጣ?! ሽው አድርጐ ፎቅ የሚያወጣ . . . . እያለ።

«የላ ክልሲ /ቶሎ ጨርሺ/» አለኝ የገዛ ሚስቱን እንደሚያዝ አባወራ።

የሱቁ ተላላኪ አይኔ ያረፈበትን ቦርሳ አውርዶ

«ማዳም ኩዲያ ኢንቲ አህበብቲያ /እመቤቴ ውሰጂአት ወደሻታል/» አለኝ።

የተከተለኝ ሰውዬ ዓይን ዓይኔን እያየ ዋጋ ተዋዋለ። ከፈለ። ቦርሳው ውድ ነው። ሰውዬው ለመክፈል

አላወላወለም። ሰውዬው ሀብታም ነው ማለት ነው። ተከትዬው ወደ መኪናው ገባሁ።

«ጥቁር ሴት ጣፋጭ ናት»

የንግግሩ ሁኔታ ደስ አላለኝም። ስሜን ይጠይቀኛል ብዬ ገምቼ ነበር። ለስሜ ግድ የለውም። ማን ልሁን ለማወቁ ምንም ስሜት የለውም። ግንኙነታችን የታወቀ ሆኖ እርሱ ሴት ፈልጐ እኔ ገንዘብ ፈልጌ ቢሆንም እኔ የእርሱ ቦታ ብሆን ስሙን እጠይቅ ነበር።

እቤቱ ይዞኝ ሲገባ አምስት ጊዜ ያህል በመኪናው አሽከረከረኝ። ሁለት ጊዜ እቤቱ ገብቶ እየተቁነጠነጠ ተመለሰ። ለሁኔታው አዲስ ነው ብዬ ገመትኩና ዕድለኛ ነኝ አልኩ።

ቁንጅናዬን ለማድነቁ ከአይኑ አነበብኩ። ይህ ደግሞ ትንሽም ቢሆን ጥሩ ስሜት ይሰጠኛል። ፍቅርን ለመመሰሉም ይረዳኛል።

«ከገመትኩሽ በላይ ነሽ ይህ አጭር ቁመት ይህን ሁላ የሰውነት ውበት ይዟል! ታስጐመጃለሽ! ገላችሁ ላይ ቸኮሌት እንዳፈሰሳችሁ አንድ ጓደኛዬ ነግሮኝ ነበር። እውነቱን ነው። ይገርምሻል አበሻ ሴት እራቁቷን ሳይ አንቺ የመጀመሪያዬ ነሽ»

«እኔም አንተ ፊት እራቁቴን መቆሜ ገርሞኛል። ከተዋወቅኩት አንድ ሰዓት እንኳን የማይሞላኝ ወንድ ሁሉ ነገሬን ሲያይ አንተ የመጀመሪያው ነህ»

«ሁላችሁም ውሸታሞች ናችሁ። ማሉቱ እናንተ»

«ሴቶች ማለትህ ነው?»

«አይደለም እናንተ . . . .» እጁን በንቀት አወዛወዘ። ገባኝ ሊል የፈለገው። በአካሉ ሊያቆስለኝ የተዘጋጀው ሳያንሰው በቃላቶቹ ሊቀቅለኝ ነው ማለት ነው።

«ቶሎ መሄድ አፈልጋለሁ»

«እኔም ብዙ እንድትቆይልኝ አልፈቅድም። የማዝሽን ነገር በትክክል ፈፅሚ!»

«ፈገግ በይ! »

«እሺ» ሙዚቃ ከፈተ።

«ከወገብሽ በታች ተወዛወዢ»

ፊልም የምሰራ መሰለኝ። ከወገቤ በታች በደንብ ተወዛወዝኩ። ይህን ያህል መወዛወዝ መቻሌን እስከዛሬ አላውቅም ነበር።

ከራስ ቅሉ እና ፊት አንገቱ በቀር መላ አካሉ ፀጉር ብቻ ነው። ይህ ሁላ የፀጉር ሀብት ከወደ አናቱ የማነሱ ጉዳይ አስገራሚ ሆነብኝ። እርግጠኛ ነኝ የደረቱ ጥቅጥቅ ፀጉር ለአናቱ እንዲያደርግለት አማሮ ፀልይዋል። 'ቆጥራ' ሲያደርግ የሸፈነውን በረሃ ጭንቅላቱን አሁን ገልጦት ከመጀመሪያው ግምቴ በዕድሜው አስር ዓመት ጨመረብኝ።

«ሳሚኝ!»

ልስመው ካለበት አጉነበስኩ።

«ላ . . ላ» ተስፈንጥሮ ተነሳ።

አፉን ቶሎ ቶሎ ጠረገ። ሁኔታው የመረረውን እሬት አፉን የቀቡት ያስመስለዋል። አኳኋኑ ልቤን ሰበረው። በጣም ጉዳኝ። ከንፈሩን መሳሜ ይህን ሁላ ነገር አስከተለ።

«ከንፈሬን ማን ሳሚኝ አለሽ . . . ቱ» ደጋግሞ በመጠየፍ ተፋ።

«ይቅርታ» አልኩ። እንባዬ ጉንጮን አቀዘቀዘው። መቼ እንዳነባሁት አላወቅኩም።

«ከዚህ ጀምረሽ . . .» ከአንገቱ በታች እየወረደ በምልክት አሳየኝ።

ያለቀውን ትዕግስቴን ባዶ በሆነው ማቀዝቀዣይዬ፣ የምግብ መደርደሪያ እና የቤት ክራይ ክፈይ በሚለው የአከራዬ ድምፅ አበረታሁት። የቤት ክራይ መክፈል አለብኝ።

ደረቱን . . . እጁን . . . አንገቱን . . . እየቀፈፈኝ ሳምኩ።

«እንደሱ አይደለም በፍላጉት ባህር ግቢ ይህንን ገላ ስትስሚ ገባሽ!»

ጥሩ ሀሳብ መጣልኝ . . . ዩስሪ። ውበቱን ናፍቄአለሁ። አይኔን ጨፈንኩና አሰብኩት። ከዩስሪ ጋር ሆንኩ። ዩስሪን ዳበስኩ ዩስሪን ሳምኩ።

«ውረጅ አምን ወደ ታች» ትዕዛዝ ከዩስሪ አነቃኝ። የሰማሁትን ማመን አቃተኝ። ውስጤም ድንገተኛውን ትዕዛዝ መቋቋም ተስኖት ከሆዴ ያለውን ሁላ የሰውዬው ደረት ላይ ለቀቅኩት።

ሰውዬው ወደባኛ ቤት ሲሮጥ እኔ ቶሎ ብዬ ለበስኩና ተንደርድሬ ወጣሁ።

በነጋታው ቦርሳ የተገዛበት ሱቅ ሄጄ

ካንድ ቀበጥ ወይዘሮ የሚጠበቅ እመቤታዊ አባባል ተጠቅሜ የቦርሳውን ሙሉ ክፍያ ተቀበልኩ።

«እንዴት የአሜሪካ ቦርሳ ትሰጠኛለህ። እኔ የወሰድኩት የፓሪስ መስሎኝ ነበር» የሚል። የቤት ክራይ ከፈልኩ። የዚያች የሚጢጢ ቦርሳ ዋጋ ለአስራ አምስት ቀን ያህል ቁርስ ደህና ምሳና ቀላል እራት ትችልልኛለች . . . . እፎይ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ዛሬ ከቅድስት ፊት ስቆም አይሻ ያለችው ትዝ አለኝ።

«እኔ ቅድስት ፊት ስቆም ሀሊናዬ ፊት የቆምኩ ይመስለኛል። ስለዚህ አይኗን እንኳን አተኩሮ ማየት ያስፈራኛል። ስለዚህ አይኗን እሸሻለሁ ልክ ሀሊናዬን እንደሸሸሁ ሁሉ» ብላ ያለችው። እነ አይሻ ቅድስትን ለምን እንደሚፈሯት አሁን ገባኝ።

ለሰላምታዋ ተንተባተብኩ። በናፍቆት አቅፋ ሳመችኝ።

«እ! ምን አዲስ ነገር አለ?» በአይኗ የሳባን ሻንጣ እያማተረች።

« . . . . ሰባህን ጠረዟት።»

ትንሽ ትክዝ አለች። ግን ምንም አዲስ ነገር አይደለም። ብዙ ሰዎች ሳያስቡ ወደ አገራቸው ይላካሉ። የተለመደ ነው።

«ምንም አትሆን። በደንብ ቀጥ ብላ ሰርታለች። ታውቂያለሽ?! እንደውም እግዜር ሲያድናት ነው። ወደ መጨረሻ ሁኔታዋ አላምር ብሎኝ ነበር። ስራ ሰለቸኝ አስጠላኝ እያለች ልትቀየር እየወላወለች ነበር። ከምትበላሽ በሰላም አገሯ መግባት ይሻላታል። አንቺስ ስራ አገኘሽ?»

እራሴን በአሉታ ነቀነቅኩ። ይበልጥ ቀርባ ተቀመጠችና «አይዞሽ እናገኝልሻለን . . . አ . . አ» አለች የሆነ ነገር እንዳስታወሰች ዓይነት።

«ሰባህ ከሄደች ስንት ጊዜ ሆናት?»

«አንቺ ደማም በሄድሽ በአራት ተንሽ [redacted] ውስጥ የያዟት። ለዘመዶቿ ደውላ ሻንጣዋን መጥተው ወሰዱላት»

«ታዲያ እስካሁን የቤቱ ኪራይ አ . ል . ም ተከፈለም?»

«ከፍዬዋለሁ»

«ወርቄን ሸጥኩ እንዳትይኝ?»

«አልሸጥኩም»

«እ . . .» አይኗን አፍጣ በጥርጣሬ

«እነሳልዋ መጥተው ነበር? ከነርሱ ጋር ሄድሽ?» ትከሻዬን ይዛ ወዘወዘችኝ። «እረ ሰው የሚባል አልመጣም?»

«ታዲያ ገንዘቡን ከየት አመጣሽ እውነቱን ንገሪኝ»

«ምን ለውጥ ሊያመጣ» አንገቴን ደፋሁ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ላገባ መወሰኔን እነአይሻ ሲሰሙ «ገና ካሁኑ ልትታጠሪ ነው» ብለው

«ታጠረች አሉ በትዳር . . .» የሚለውን ዘፈን እያጨበጨቡ ዘፈኑልኝ።

አስመሮም መጀመሪያ ያየኝ የቅድስት ዘመድ ቤት ስሰራ ነበር። ብዙ አላወራንም። እርሱ ግን ጥሩ አድርጉ ሳያስተውለኝ አልቀረም። እንደሌሎች ለጓደኝነት ሳይሆን ለጋብቻ ስለጠየቀኝ ደስ ብሎኛል። ትዳር እዚህ አገር እንደማይጥም ባውቅም አንድ ቀን የሚያማምሩ ልጆቼን ይዤ አገሬ እገባለሁ። ደግሞም ፍቅር ከተጋባን በኋላ ሊመጣ ይችል ይሆናል ብዬ አመንኩ። እርሱም በዛ ያመነ ይመስላል። እሰራባት የነበረችው አበሻ ሴትም ስለ እሱ ስታወራ ሁሌ ጥሩነቱን ታወሳ ነበር። ትልቁና ዋናው ነገር ያገሬ ልጅ ነው።

ሁለተኛው ለጋብቻ መስማማቴን ቶሎ ያጠነከርኩበት ጉዳይ የፈራሁት ነይ እያለ የሚጐተጉተኝን አሳሳች መንገድ ለማምለጥ ነው። በቀደም ተሳስቼ ወጥቼ ያን ቦርሳ የገዛልኝ ሰው ጋ የደረሰብኝ እንዲደገም አልፈልግም። ስራ መስራቱም በጣም አስጠልቶኛል። ስለዚህ አግብቼ አዲስ ህይወት ቢኖረኝ አይከፋም። ይህ ትዳር ከአሳሳቹ መንገድ ያድነኛል። ቤተሰብ መስርቼ ከባሌ ጋር ሆነን አገራችን መግባቱ ትልቅ እድል ይሆነኛል። ቁጭ ብለን ስለቤተሰባችን ስናወራ ስበሳጭ ሳዝን በጥብቅ እቅፉ ተስፋን እንዲሰጠኝ ብቸኝነቱን ጥሶ አብሮኝ እንዲሆን ባል ማግባት መረጥኩ።

አስመሮም ስራው ሽፋጥ ነው። ሽፋጥ የሚለው ቃል መሸፈጥ ከሚለው አረብኛ የተወሰደ ነው። ሽፋጣ

የሚባሉት እዚህ አገር በሽንት ቤት መጣጭ መኪኖች በሹፌርነት ወይም በባለቤትነት የሚሰሩ ናቸው። ታዲያ እዚህ ያለ ሀበሻ ወንድ ዘጠና አምስት በመቶ በዚህ ስራ የተሰማራ ነው። ላገባው ያሰብኩት ሰው ታዲያ የሽንት ቤት መጣጭ መኪና ባለቤት ነው። እናም ሽፋጣ አለው ከተባለ ሀብታም ነው ማለት ነው። የሰርጌን ምክንያት በደንብ ያወቀች ቅድስት ብቻ ናት።

«እኔ አስመሮምን ለምን ልታገቢ እንዳሰብሽ አውቃለሁ አዕምሮሽ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሊያሰላስል የፈለገውን ነገር እንዳያስብ አስመሮም ጀርባ ልትሸሸጊ ነው። አራስሽን ሽጠሽ ስራ ጠልተሽ በቀላሉ ገንዘብ ልታገኚ የምትችይበትን መንገድ ፈልገሻል። ግን ደግሞ ያን እንዳታደርጊ የሚከለክልሽ ከባድ እንቅፋት በመፍጠር አራስሽን ከዚህ ሀሳብ ትገላግያለሽ። እመኚኝ ይህ ጥረትሽ ላሁኑ ሁኔታሽ ለጊዜው መከላከያ ይሆንሽ ይሆናል። ግን ወደፊት አንድ እኩይ ሀሳብ በመጣልሽ ቁጥር ከራስሽ ሀሳብ ለመሸሽ ጠንካራ ምክንያት ስትሺ መኖር እንዴት ትችያለሽ። ለምሳሌ አንድ ሰው ለመግደል አስበሽ ግን ደግሞ ያን ሰው ላለመግደል መልአክ መጥቶ «ተይ አትግደይ» ብሎ እንዲያግድሽ ትመኛለሽ። ለምን ከራስሽ ጋር አትስማሚም!? ለምን ራስሽን ይህ አይሆንም ብለሽ አሳምነሽ ጠንካራ ውሳኔ አትወስጅም? እናም የፈራሽውን የነአይሻን መንገድ ላለመቀበል የምትከላከይው ሙሽራ ሆነሽ ነው? ትገርሚያለሽ! ፈሪዋ ሙሽራ! ቦቅቧቃ ነሽ! ጠንካራ አይደለሽም እኔ እንደምገምትሽ! እንዴት ሰው የገዛ ሀሳቡን ይፈራል።» አለችኝ። ቅድስት የዋዛ አይደለችም።

የሰርጉ ቀን ተፋጠነ። ከድግሱ በፊት የሚፈረም የጋብቻ ውል አለ። አስመሮም ከሽማግሌዎች ጋር እያለን የጋብቻ ውሉ ፎክ ተብሎ እንዲነበብ ጠየቀ። የጋብቻ ውሉን የፃፈው እራሱ መሆን አለበት።

«የሕይወት ጓደኛዬን ከመምረጤ በፊት ያፈራሁት ንብረትም ሆነ እርሷ እኔን ከመምረጧ በፊት ያፈራችው ንብረትም ሆነ ገንዘብ ከጋብቻችን ውጭ ሆኖ አብረን በሆንበት ጊዜ ብቻ የምናፈራው ገንዘብ በሁለታችን እኩል የሆነ ንብረትነት እንዲኖረው ይቀል ዘንድ የራሴን ንብረት በእንዲህ ሁኔታ ስዘረዝር የእርሷንም በሽማግሌ ፊት እንድትዘረዝርልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

የኔ አነስተኛ ተመኗ አርባ ሺ ሪያል የሆነ የቤት መኪና በባንክ . . . .

ንብረቱን መዘርዘር ቀጠለ። በእውነቱ ንብረቱን አላዘቶ ስለካልሲው ሁላ የሚናገር ሰው ላይሆን አይቀርም። እኔ ኑሮን ፈርቼ ሕይወቴን ሕልሜን እርሱው እንደፈለገ እንዲያንቀላቅስ ልፈቅድለት ስዘጋጅ እርሱ በንብረቱ ጠረጠረኝ።

አላው በሽማግሌዎች ፊት ጋብቻዬን መሰረዜን አስታወቅኩ።

* * * * * *

ከዚያን ቀን በኋላ የቅድስት ምክር ጭቅጨቃ ሆነና እየሰለቸኝ መጣ። ስንት አጠያይቃ ያመጣችልኝን ስራ ደክሞኛል ብዬ ላልቀበለው ቀረሁ።

በዚህ መሀል ወደ መረጥኩት የህይወት መንገድ ይበልጥ የሚያበረታኝ ወሬ ዱብ አለ።

ጀሚላ ለቅድስት ስራዋ ቦታ ደውላ ጥሩ ቦታ ማግኘቷንና ከነአይሻ ጋር የነበረች ጊዜ የነበራትን ፍሪጅና ልብሶቿን ሁለ ነገሯን ለሳልዋና አይሻ እኩል እንዲካፈሉ ብላ መልዕክት ነገረቻት።

እኔና ቅድስት መልዕክቱን ለነ አይሻ ልንነግር የሄድን ጊዜ የጀሚላን ቦታ ለመተካት ሀሳብ መጣልኝ።

በዚያ ሰሞን የጀሚላ ሁኔታ በጣም ያስገረማት ሳልዋ ወሬ ለማጠናከር የአበሻ ፀጉር ሰሪዋ ቤት ሄዳ ብዙ ብዙ ወሬ ይዛልን መጣች።

«ስለ ፀጉር ሰሪዋ ሴት እንዴት ሀሳብ መጣልሽ?» አልኳት ገርማኝ።

«በጅዳ ውስጥ የምናውቃት ፀጉር ሰሪ እርሷ ብቻ ነች። በምትሰራሽ ወቅት ብዙ ታስለፈልፍሻለች። ስለዚህ እንዳለችው ጥሩ ቦታና ገንዘብ ካገኘች ፀጉሯን ለማስዋብ ፀጉር ቤት ብቅ ማለቷ አይቀርም። የአረቦቹ ፀጉር ቤት ልሥራ ብትል ፀጉሯን ይበልጥ አስርድደው አቁመው ነው የሚልኳት። የአበሻ ፀጉር ፀባይን የምታውቀው እዚች ፀጉር ቤት ጋ መምጣቷ አይቀርም። በወሬ የምታጣድፈዋ

ፀጉር ሰሪ ጀሚላ የእኛ ጓደኛ እንደሆነች ታውቃለች። ስለዚህ ስለ ጀሚላ ከፀጉር ሰሪዋ የሆነ ወሬ እንደማገኝ እግጠኛ ሆኜ ነበር የሄድኩት። ይገርምሻል ስለጀሚላ ልታወራልኝ ገና ስታየኝ የምታጥባትን ልጅ ገፋ አድርጋ እጇን እያደረቀች በምልክት ጠራችኝ።»

«አ! ጀሚላ መጥታ ነበር። ባንዴ ተመነጠቃችሁ አይደል። ተሳካ ውጥኑ!. . . ሰው እንዲህ ባንዴ ይለወጣል . . . ሹፌሯን ከበር አቁማ . . . የእጅ ሞባይል ስልኳን ይዛ እመቤት ሆናለች . . . » አለችኝ።

«ስልኳ የእርሷ ባሏ ያንስ?»

«የራሷ ነው ታስታውቃለች። በዚህ ወር ብቻ አምስት ጊዜ ፀጉሯን ተሰርታለች። ፀጉሯን ብቻ መሰለሽ?! ጥፍሯንም ተረከዟንም . . . ደግሞም የባሯ ውድ ዘይት አድርገንላት እንፋሎት ካስክ ውስጥ ገባች። የእንፋሎት ካስክ ከገዛሁ የመጀመሪያዋ አበሻ ተጠቃሚ ሆነች። እስካሁን ማንም አበሻ ሴት ይህን ካስክ ደፍራ አትጠቀምም። ዋጋው ውድ ስለሆነ!።» ብላ ትንፋሽ እያጠራት ስለጀሚላ ሀብታምነት ማስረዳ ሰጠችኝ። እርግጠኛ ነኝ ከአንድ 'አሚር' /የንጉስ ዘር/ ጋር ናት ያለችው። ምን ያረጋል ታዲያ ወንዷን እንዳንሰርቃት እራቀችን።»

«ወንዷን እንዳትሰርቋት?!» አልኩ

«እ . ሀ . ሀ አምን» ሳቀችና ሳልዋ ቀጠለች «ግን እውነቷን ነው። አንድ ጊዜ አይሻ ምን አደረገቻት መሰለሽ?! ከሆነ አመዳም አረብ ጋር ጀሚላ ትዋዋልና ቀንና ሰዓት ብቻ ተነጋግራ እቤት ያደርሳትና ይሄዳል። ሰውዬው ቀደም ብሎ ሲመጣ አይሻ በር ከፍታ የሆነ ነገር ትሰውና ተመልሶ ይሄዳል። ጀሚላ ተሰናድታ ሰውዬውን ብትጠብቅ ብትጠብቅ ሰውዬው ሳይመጣ ቀረ። ከዛ ብዙ ቆይቶ በድንገት ጀሚላ ሰውዬው አይሻን እቤት ሲያደርሳት ታያለች . . . . ውው . . .ውውው! ብታይ ሊባሉ ነበር። ከዚያ ጀሚላ ማለች ጥሩ ወንድ ስትይዝ ፈፅማ ላትገናኝን . . . አትገርምም?! ጥሩ ናት ለማንኛውም።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሳምንቱን ሙሉ ሳሰላስል ሳሰላስል ሰነበትኩ። ለቅድስት አነስ ያለች ማስታወሻ ፅፌላት ሻንጣዬን ይዤ ወጣሁ።

እነሳልዋ ቤት ስደርስ ሳልዋ በሙሉ ልቧ ተቀበለችኝ። አይሻ ሻንጣዬን ተሸክማ አስገባች።

«የጀሚላን ቦታ አገኘ ይሆን?»

«ምንግዜም!» አለች ሳልዋ በእንግሊዘኛ።

አይሻ የግብፅ አረቦች በጣም የሚወዱት ሰው እቤታቸው ሊጠጋ ሲጠይቃቸው የሚጠቀሙበትን ልባዊ አነጋገር ተጠቀመች።

«ለማሼሌቲክ አርድ ንሺሊክ ጉዋ ዓይንና /መሬት ኢልሸው ብትልሽ እንኳን እኛ አይናችን ውስጥ አናስቀምጥሽለን/።»

አቀባበላቸው ደስ አለኝ። ለምን እንደመጣሁ አልጠየቁም? ግን አውቀውታል። ቅድስትን አሸነፉ። በነጋታው ስናወራ ስለዩስሪ አወራሁላቸው።

ሳልዋ በቁጭት እራሷን ነቅንቃ «ትዝ ይልሻል እኛንና አንቺን ያጣላው ያ ዱባ አረብ ቅድስትም የተቅየመችንና ለረጅም ጊዜ እቤቱ እንዳትደርሱ ያስባላት

ጉዳይ ትዝ ይልሻል? ያን የምነግርሽ ጥሩ ጊዜ አሁን ነው። አሁን አንቺም የኑሮ ሁኔታ በደንብ ስለገባሽ ይቅርታ ሳታደርጊልን አትቀሪም። እኔ ግን አውቅ ነበር . . . የሆነ አረብ አታሉ ክብርሽን እንደሚወስድ . . . ይህ የተለመደ ሆኗል ለእኛ። ታዲያ ያ መሆኑ አይቀር ብትጠቀሚበት ይሻል ነበር። እኔ ተዋውዬልሽ የነበረው አረብ ለክብርሽ ብዙ ይከፍልሽ ነበር። በዛ ብር ብቻ አገርሽ ትገቢ ነበር። አየሽ ነገ የተቀመጠልንን አናውቅም። ህይወትሽ በተለይ በስደት እንደፈለግሻት አትሄድም። ፍቅር . . . ፍቅር ብለሽ ምን ላይ ደረስሽ? እ!። እኔ ያመጣሁልሽን ዱባ ብትከትፊ ግን ይዤኔ ዱቢኖ ትሆኚ ነበር። ይህን የተከፋ ፊትሽን ዛሬ አላይም ነበር። እኛ በተወለድንበት ዘመን ላንቺ አይነቷ ቡቡ ቦታ የለውም። በዚህ ዘመን ሁሉም ነገር በተመን ነው። የምታገኚው ነገር በተመን እንደሆነ ሁሉ የምትሰጪው ነገርም በተመን መሆን አለበት። ፍቅርም ቢሆን እንኳ በተመን። እኔ ገና ሳይሽ ህይወት እንደምታደክምሽ ገምቼአለሁ። እንደነገርኩሽ ይህች አለም እንዳንቺ ቡቡ የዋህ ስፍቅር ብርግድ ብሎ የተከፈተ ልብ ላለው አትሆንም። ልምክርሽ አንቺ ካሁን ወዲያ ራሷን ልትከላከል የምትችል ቁጡ ድመት መሆን መቻል አለብሽ። ለፍቅር ብለሽ ያለተመን የሰጠሽው አረብ በነፃ የሰጠሽው ፍቅር አይጥመውም። እነርሱ እንደዚያ ናቸው። ምን ያህል ነች ለኔ አይደለም ጥያቄአቸው ምን ያህል አወጣሁላት ነው። ይህ ነው ፍቅር እዚህ አገር። ተለወጪ!»

እኔ ግን በግልፅ ከዩስሪ ጋር ያላለፍኩትን ወራት እንደማልፀፀትበት ስነግራቸው ሁለቱም ልባቸውን ይዘው ቀለዱብኝ «ልቤን! ልቤን! » እያሉ።

እኔም ቀልዳቸውን በቀልድ ስመልስ

«ገልቢ ዳ ምሽ ሙትአድብ! በስ አነ አርፍ እዘይ እረቢ! /ይህ ልቤ አደብ የለውም እኔ ግን አንዴ እንደማድበው አውቃለሁ/» አልኳቸው በአረብኛ። እነ አይሻ ልባቸውን ለቀው ልቤን እየያዙ

«ትረቢ አልቢክ? /ልብሽን ልታድቢ?/» አሉኝ። ከዛ በኋላ ግን አይሻ በቁም ነገር ተኮሳትራ « ዱሲ አለ አልቢክ አቅሊክ ቢክፊኪ /ልብሽን እርገጪው አዕምሮሽ ብቻ ይበቃሻል/ አለች።

ሳልዋ በተራዋ «አነ አኡሊክ ዱሲ ኢትፈን አልቢክ ወአቅሊክ/ እኔ የምልሽ ደግሞ ሁለቱንም ዋጋ የላቸውም እዚህ አገር። ባዶ መሆኑ ያዋጣል። ያለ ልብ ያለ አዕምሮ» አለች። የተማረች ትመስላለች።

አይሻ «አትስሚያት! አዕምሮ አስፈላጊ ነው። ግን ላንቺ ብቻ የሚፈርደው አይነት መሆን አለበት። ሁለተኛውን አዕምሮ ለእውነት የሚቆመውን ይህ ስራሽ ስህተት ነው ቀጥ በይ ብሎ ሊያቃና የሚሞክረውን የሚገስፀውን የሚፀፀተውን አዕምሮሽን ግን እርሺው!» አለችና ንግግሯን ደመደመች። እኔም ስለሁለቶቹ አዕምሮዎች እያሰላሰልኩ ወደ አልጋዬ ሄድኩ። ለነገሩ እኔ

የነበረኝ አንድ አዕምሮ ነበር። አሁን በቅርቡ ደግሞ ሌላኛውን ተረከብኩ። ስለዚህ የአይሻ አባባል በደንብ ገብቶኛል።

እነ አይሻ እንዳሉት ለለውጤ የመጀመሪያ እርምጃ እነርሱን በተስፋ የምትሞላ ቻድአዊት ጠንቋይ ጋር መሄድ ነበር ደስ ሳይለኝ ተስማማሁ

አስደንጋጩን ትዕይንት አየሁ ቻዳዊቷ ጠንቋይ ጋ ቀይ ብርሃን፣ ቀያይ የለበሱ ሰዎች የሚያፍን ጭስ የሚዘገንን ድምፅ የከበሮ ድም ድም-ታ ድው ድው ዳ . . . . ዙሪያውን ተደርድረው በስልት በከበሮዋና በዕልልታው አመታት ቀና ጐንበስ ቀና እያሉ ይናጣሉ። መጨረሻ ላይ እንዲ ጣ ብላ ተዘረጋች። ጠንቋይዋ የማይገባ ቋንቋ ለፈለፈችና ዶሮ አርዳ ደሟን የወደቀችዋን ሴት ለቀለቀች። የሴትዬዋም ሆነ የሰዎቹ መልክ አያስታውቅም። ቀዩ መብራት መልካቸውን ብዥ አድርጐብኝ ነበር። ጠንቋይዋ ቤት ባዩት ነገር በተመሰጠ ሌላ አለም ውስጥ የገቡትን ጓደኞቼን በአግርሞት አስተዋልኩ። ስለጠንቋይዋ ያለኝን አስተያየት ዋጥ አደረግኩ።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

አይሻ ያመጣችልኝን አዲሱ ስራዬን ባንድ ስነስርአት ፊዕሞ ባልፈጠረበት ወንድ ጀመርኩ።

አብሬው አልጋ ውስጥ እያለ ለሚስቱ ደውሎ ማውራት ጀመረ። ገላዬን ጨመቅ እያደረገ ሚስቱ ላይ ይቀልዳል። እኔ ላይም . . . አኳኋኑ ቢያስጠላም ተናድጀ ጠዋት የማገኘውን ብር ላለማጣት እራሴን ተቆጣጥሬ ዝም አልኩ። ደስ ላሰኘው ፈገግ አልኩለት። አስተያየቴ «ጀግና ነህ! በሴቶች የምትጫወት ጀግና!» እንዲለው ፈለግኩ። እርሱም ያን ማወቅ ሳያኮራው አይቀርም። ለሚስቱ 'ያ አዩኒ አነ ያ ሀያቲ /የኔ ሕይወት/' እያለ የፍቅር ወሬውን አደራ። አቤት እንዴት ውሸታም ነው። ቢያንስ የሌላ ሴት ገላ ታቅፏል።

በጣም የተቀራረበው ገላችን የመታከት ምልክት ችፍፍ አደረገ። ነጭ ገላው አስጠላኝ። ብቻ የኔንም ጥቁር ገላ ንቋል። ስልኩን ዘጋና በአረብኛ «እኔ ስልክ ከሚስቴ ጋር ላወራ ምን ያስገለፍጥሻል» አለኝ። ክው ስላልኩ መልስ አጣሁለት። ንግግሩን ቀጥሏል «ይኼኔ ነጠቅኪት እያልሽ ደስ ብሎሽ ይሆናል እኮ!። ከሚስቴ እግር እጣቢ አትደርሽም። ሽርሙጣ!» ብሎ በጥፊ አላሰኝ። የሁኔታው ዱር ዳሩ ገባኝ። መለያያችን ስለደረሰ ክፍያ ሊከለክለኝ የጠነሰሰው ጥንስስ ነው። ጥፊው ተጨምሮልኝ ምንም ሳላገኝ አንገቴን ሰብሬ እቤት ተመለስኩ።

እነ አይሻ በዚህ መንገድ ከሚደርሰው መጥፎ እድል አንዱ እንደሆነ ነገሩኝ። ለዚያውም ቀላሉ ነው። ብቻ ለሁለተኛው እድልሽ ፀልይ አሉኝ እንደቀላል።

* * * * * *

ቅመማ ቅመሙ ብዙ አይነት ነው። ሽታውም ይለነፍጣል። ከመሀላቸው የተላጡ ጥውልግ ነጭ ሽንኩርቶች አሉ። ትልቁን ቢጫ የድንጋይ ቁራጭ በጣም አየሁት። የሚሸተውንም ሽታ አስታወስኩ . . . . . ድኜ።

ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ 'ሰልፈር' ብለን በተግባራዊ የኬሚስትሪ ትምህርት ሰዓት እንማርበት የነበረ ግማታም ድንጋይ . . . . ድኜ።

አይሻና ላልዋ ይከራከራሉ።

«ሴትዬዋ ያለችው ፈጭተሽ በጥብጠሽ የሰው ትንፋሽ በማይዞርበት አስቀምጪውና ጠዋት አንድ ብርጭቆ በባዶ ሆድሽ በግራ ጉንጭሽ ብቻ ፈላሹ እንዲያልፍ አድርገሽ ትጠጪና በቀኝ ጥርሶችሽ ምግብሽን ትወስጂአለሽ። በግራ ጉንሽ መተኛት መጀመር አለብሽ። የመገላበጥ ልማድ ካለሽ አንድ ሰው እንዲያስርሽ አድርጊ። ብቻሽን ተኚ። እራቁትሽን ሰው እንዳያይሽ። ከቤት በፍፁም እንዳትወጪ . . . . ነው ያለችሽ።» ስትል አይሻ

ላልዋ በተራዋ «በደንብ ሰምቼአታለሁ አረብኛው ተዘባርቆብሻል ማለት ነው። ጠዋትም ማታም እንድጠጣ ነው የነገረችኝ።»

ስለማ ንግግር እንደሚያወሩ በደንብ ገብቶኛል . . . ስለዚያች የቻድ ጠንቋይ ነው።

በመሀል ገብቼ «ላልዋ እኔ ያችን ቻድ አላምናትም። እስከዛሬ ያለችው ነገር ምንም አልደረሰም

ብላ ብላ መርዝ ትሰጥሽ ጀመር። ድኝ ልትጠጪ ነው? ሌሎቹ ዘሮች ደግሞ የምን ዘር እንደሆኑ አይታወቁም። አባክሽን እራስሽ ይህንን አታድርጊ። አይሻ ከልክያት!»

ሳልዋ ጮኸችብኝ «አፍሽን ያዢ። አትነጂሽኝ።

አንደኛዋ አይነ ጥላዬ አንቺ ነሽ።»

ሳቅኩኝና «ታዲያ እኔ አይነ ጥላሽ ከሆንኩ እኔ ልሂድ ከፊትሽ ልጥፋ። ይህንን መርዝ ግን አትጠጪ»

አይሻ መርዝ በማለቴ ተቆጣች።

«ቡዳ! ስለማታውቂው ነገር አታውሪ።» አለችኝ። ዛራም ቀይ ብልጭልጭ ስስ ልብስ እንደለበሰች ከባድ አጣናማ ቡናዋን አዘጋጅታለች።

እራሴን ከእነርሱ አንዷ አድርጌ ብቆጥርም ይህ እምነታቸው ያስፈራኛል። ያች የቻድ ጠንቋይም እንደማትወደኝ አውቃለሁ። በጣም ስላመኗት እነቂት ብትላቸው ሳያውቁት በመንፈስ ብቻ ያንቁኛል ብዬም አንዳንዴ አሰጋለሁ። እርሷም የኔን ብቻ ሳይቀር ሁሉንም ነገር ስለኛ ታውቃለች። ስለ እርሷ ያለኝ አመለካከት በየጊዜው ለሚፈጠረው ግጭት ዋናው መንስኤ ነው።

ለኪራይ ያዋጣሁት ገንዘብ ስላላለቀ ደስ ሳልላቸው አስቀምጠውኛል። እኔም የየቀኑ የቡና ዝግጅት የራስ ምታቴን እየጨመረው ስለመጣ አዲስ ቤት ለመከራየት የአፓርትማ ዘበኞችን አጠያይቂ በቅርቡ ሊያስረክበኝ ቃል የገባልኝ ስላለ ግንኙነታችን እንደሚያበቃ አውቃለሁ።

አይሻ ቀጠሮ የነበረባት ሌሊት ሳልዋ እርዳታዬን ጠየቀች።

«እምነታችንን ስለጠላሽ እውነቱን ነው የምልሽ በአባባልሽ እንጂ አንቺን ጠልቼ አላውቅም። እንደውም ታሳዝኚኛለሽ። ለምን እንደሆነ አኔንጂ። አመለካከታችን ስለማይመሳሰል አንድ ላይ መኖር ባንችልም በስደት ስለተገናኘን ለመደጋገፍ እህትማማቾች እንደሆንን አትርሺ። የሆነ ችግር ሲያጋጥምሽ ከጉንሽ ነኝ። አትቀየሚኝ። ቤት አገኘሽ አሉ!»

«አዎን . . . አዎን። ግን አንቺ ዛሬ ምን ሆነሻል ፊትሽ ላብ በላብ ሆኖአል።»

«ከነገርኩሽ ያው የተለመደ ጥላችን ላይ እንመጣለን። ነገሩ የቻድ . . . »

«አወቅኩት። ብቻ ያን ነገር ጠጣሁ እንዳትይኝ!»

ሳልዋ አይኗ በእንባ ግጥም አለ።

«ምን ላድርግ?! ሁሉም ወንዶች ይጠቀሙብኝና ሳንቲም አይሰጡኝም። መጀመሪያ ያጋጣሚ ጉዳይ መስሎኝ ነበር። በኋላ ግን ጉዴን የቻዲ አዋቂ ነገረችኝ። ታውቂያለሽ! ወንዶች ይወዱኛል። እንዳለችኝ ከሆነ የሌሊት ንግስታቸው ነኝ። እኔን በማየት ብቻ አካላቸው ይወራጫል። ይህ ዓይነ ጥላዬ ግን በነጋታው እንዲጠሉኝ ያደርጋቸዋል። ለሊቱን ደህና አሳልፈው ጠዋት ያለምንም ገንዘብ እንደውሻ ያባርሩኛል። ተሳስቶ እንኳን ለሁለተኛ

ግንኙነት የጠየቀኝ የለም። አይነጥላ መሆኑን ሳላውቅ በዕድሌ ብዙ አልቅሻለሁ። አሁን ግን በሚቀጥለው ሳምንት ያ ሁላ አብቅቶ እድሌ ይጠራል። ድፍርሱ እድሌ ሲጠራ ገንዘብ አፍሳለሁ። ይታየኛል ይህ ፈውስ አይነጥላዬን አንስቶ በምትኩ ስጢት የሚለውን ይተካልኛል። በትንሽ ጊዜ ውስጥ ሀብታም እሆናለሁ። ገንዘብ ሁሉም ነገር ነው። በገንዘቤ የፈለግኩትን ሁላ በእጄ አደርጋለሁ። ሀይለኛ እሆናለሁ።» በላብ የተጠመቀ እጇን ጨበጥ ፈታ እያደረገች።

« ሳልዋ . . . . መድሐኒቱ እየጐዳሽ ነው። ወተት ላምጣልሽ?»

«አይ ወተት አይወድም። መጀመሪያ አካባቢ እንዲህ እንደሚያደርግ ነግራኛለች። ትንሽ እየቆየ እየባሰ ይሄድና በሙሉ ሀይሉ ችግሬን ከፈነገለ በኋላ ደህና እሆናለሁ። መድሐኒቱና መጥፎው መንፈስ እየተጣሉ ነው።» ድምፅዋን አንሾካሽካ። በፈገግታ ስታየኝ ቆየችና «በጣም ጥሩ ነሽ።» አለችኝ በምስጋና አንገቴን ወዘወዝኩ።

«ዛሬ አይሻ ቀጠሮ ስላለባት ከአልጋ ጋር እንድታስሪኝ ነው የጠራሁሽ። በዚህ ገመድ ጥፍር አድርገሽ አሰሪኝ። በቀኝ ጉኔ እንድተኛ አይፈቀድልኝም።

ሳቅኩኝ። «ተይ እንጂ እኔ በጣም እንቅልፋም ነኝ ለሊቱን ሽንትሽ ቢወጥርሽ እንዴት ልታደርጊ ነው?»

እውነቱን ለመናገር ሁኔታዋ ደስ ስላላለኝ ሌሊቱን እየተነሳሁ ሳያት አደርኩ።

በነጋታው ሞቅ ባለ የቡና ጭስ ተነቃቃን። አይሻ በደማቅ ፈገግታ ተሞልታለች። ቀንቶአል ማለት ነው።

«አሻገረኝ! ቀላል ደማልኝ? በጣም ሙዲ እያለ አጋጠመኝ ዋው . . . » ሳልዋን አቀፈቻት።

ወደ እኔ ዞር አለችና «ይቅርታ የኔ ቡዳ! ያኮረፍሽ ትመስያለሽ ላቅፍሽ እችላለሁ?

ሁለት እጀን ዘረጋሁላት . . . . በሙሉ ሀይሏ ተጠመጠመችብኝ።

«ልንግባባ እንጣር። እኔ ዛሬ ደህና ክፍያ አግኝቻለሁ። ግማሹን ለቤተሰቦቼ እልክና በግማሹ የቤት ክራይ ልንቀጥል እንችላለን። ለምግባችንም አናጣም እባክሽ አትለይን! እንወድሻለን እ . . . ይቅርታ አድርጊልኝ»

በሚቀጥለው ሌሊት ሳልዋ እንደታሰረች በጣም ታቃስት ጀመር። ነቅቼ ፈታኋት። አይሻ የትናንትና ድካሟ ስላለቀቃት ሞቅ ያለ እንቅልፍ ላይ ነበረች።

«ሳልዋ ዛሬም ያን ጠጣሽ ደግመሽ?»

«ሁለት ቀናት ይቀሩኛል።»

«ወይኔ! ብሶብሻል እኮ ፊትሽ ተለውጧል።

በጣም ፈራሁልሽ አይሻን ልቀስቅሳት።»

አይሻ በፍርሀት አይኗ እንደፈጠጠ

«ደም እየፈሰሳት ነው ምን እናድርግ . . .» አለች።

ጉልበቴ ተብረከረከ። መተንፈስ ተስኗት የምትንቀጠቀጠዋን አበባ/ሳልዋ/ ልረዳት እችል እንደሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም። ይህ በኔ አዕምሮ የሚመላለሰው ፍርሀት አይሻን አድርቋታል። ሌሊት ነው እንዴት እንውጣ! የመኖሪያ ፍቃድ የለን።

በግራና በቀኝዋ እጆቿን እንደጨበጥን በፅኑ ፀለይን። አበባ ግን አሁንም «ፈውሴን አታርክሱብኝ ፀሎታችሁን አቁሙ» አለች።

«እባክሽ ስለገንዘብ ማሰብሽን አቁመሽ ስለ ህይወትሽ አስቢ ብዙ ደም እየፈሰሰሽ ነው።»

ጠዋት ሲሆን እንደ ህፃን ላስቲክ እና ጨርቅ አስታጥቀናት በታክሲ ሆስፒታል አደረስናትና «ለኛ ስትይ ጠንክረሽ አንድ አስር እርምጃ ተራመጂ» አልናት

ተስፋ በመቁረጥ እያየችን

«የአዲስ አበባ አድራሻዬን ታውቁት የለ . . .» አነጋገሯ ዘመዶቼን በሞቴ አርዱልኝ የሚል አይነት ነው። አይሻ እንባዋን እየጠረገች «አትቀጥይ ደህና ትሆኛለሽ» ብላ ላመቻት።

እኔም አቀፍኳትና «ነገ እንጠይቅሻለን» አልኳት። አይሻ የአበባን የአስልምና ስም ዓፈችና ኢትዮጵያዊት የሚል አድራሻ አድርጋ ቦርሳዋ ውስጥ ከተተችላት።

በሩቁ ተደብቀን እየተውተረተረች ስትራመድ የሆስፒታሉ በራፍ እስክትደርስ እየናት። የሆስፒታሉ በር ላይ ሂ ብላ ስትወድቅ ክውስጥ ነርሶች ተሯርጠው ሲያነሷትም እያለቀስን አይተናት ወደቤታችን ተመለስን።

በነጋታው ልናያት ሾርባ ቢጤ አዘጋጅተን ሄድን። የእንግዳ መቀበያው ውስጥ የቆመው አስተናጋጅ ጉና ስሟንና ዜግነቷን ስንነግረው በቁራኛ እያየን ስልክ ሲያነጋግር አባያችንን ሰብስበን ረጅሙን አስፋልት ሮጠን ታጠፍን። በአይሻ ሀሳብ ፊታችንን ሸፍነን በታክሲ ሆስፒታሉ አካባቢ ዞርን። ብዙ ፖሊሶች ፍስስ ብለዋል።

«የገመትክት ነገር ነው ፖሊሶቹ እኛን እየፈለጉ ነው» አለችኝ በጆሮዬ

«ምን . . . . አበ . . ባ ምን ሆና ነው» ታክሲውን አስቁሜ ልወርድ ስል አይሻ አጥብቃ ያዘችኝ።

«ምን እያረግሽ ነው አበባን ማየት አለብኝ። ምንም ያድርጉኝ እንጂ . . . .» ከልብ አለቀስኩ።

እራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም። «ልቀቂኝ እወርዳለሁ» አልኳት አይሻን

አይሻ በጣም ታለቅሳለች። «ሁለታችንም ተይዘን እንቀጠቀጣለን።» እራሷ ሳትረጋጋ እኔን ደጋግማ ልታረጋጋኝ ሞከረች። ቆርጬ ከታክሲው ልወርድ ስል ሀይለኛ ምት እራሴ ላይ በያዘችው ፔርሙዝ መታችኝ። ዞረብኝ።

ባለታክሲው በመገረም ዞሮ ካየን በኋላ መንገዱን ቀጠለ። አይሻ በጣም እየተጠነቀቀች በሦስት አራት ታክሲ እቤታችን ገባን።

ሆዴን እንደጨመቅኩ ሳለቅስ ነጋልኝ።

«ሞት መጥቶ ሊያስፈራራት እንዳታመልጥ እስር ያደረግኳት እኔ ነኝ። አስራአት ደሟ ፈሶ አለቀ። አስራአት . . . ያችን ቻድ ማነቅ አለብኝ» ብዬ ደጋግሜ ዛትኩ።

«ሞኝ አትሁኚ። ሞትን በሩጫ የሚያመልጥ የለም። ደግሞም መሞቷን በምን አወቅሽ? ፖሊሶቹ ያንዣበቡት ለሌላ ጉዳይ ከሆነስ? ለማንኛውም ኤንባሲ እንሂድና ጓደኛችን ጠፋች ብለን እናመልክት»

ኤንባሲ ለማመልከቱ አበባ ጊዜ አልሰጠችንም። የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ከባዱ ድባብ እንደሸፈናት ፎቶግራፏ በአሳዛኝ ሁኔታ ተለጥፏል።

እኔና አይሻ መተንፈስ አቅቶን በጣም አየናት። አይሻ ቦርሳዋ ውስጥ የተወችላት አድራሻ ተፅፏል።

አይሻን ጨምድጀ እንደያዝኩ «ጮክ ብለሽ አንብቢልኝ ጮክ በይ የሚለው አልገባኝም። አንብቢ . . . አንብቢው እያት አ - በባን አየሻ - ት ወይስ እኔ ብቻ ነኝ የማያት . . . »

አይሻ እንዳልኳት ጮክ ብላ ሰው ሁሉ እንዲሰማ አድርጋ አነበበችልኝ።

«እህታችን ሳልዋ መሀመድ ሆስፒታል ውስጥ ሞታ ስለምትገኝ ፎቶግራፏን አይታችሁ የምታውቋት ካላችሁ ለቤተሰቦቿ የምንነግርበትን መንገድ ታሳዩን ዘንድ እባካችሁ ተባበሩን»

ጉሮሮዬን ምርር እያለኝ «አ . . .ህ . . የሚል ቃል አወጣሁ።

ከኤንባሲው ስንወጣ ጀምራ ግራ ክንዴን የጨመደደች የበራችንን ቁልፍ ለመክፈት ለቀቀችኝ። ገፍትራ አስገባችኝና በማስጠንቀቅ «እውነቱን ለማንም እንዳትናገሪ! ከተናገርሽ የናፈቅሻትን እናትሽን አታይም ገባሽ?» ድምፅዋ እንደትዕዛዝ ጠብቆ አይኖቿ ያለማቋረጥ እንባ ያፈሳሉ። የፍርሃት አልነበረም በርግጥ አበባ ለእርሷ ምን ያህል እንደሆነች አውቃለሁ።

ንግግሯን ቀጠለች «እኛ አላጠፋንም። የምትጠጣው ነገር መርዝ እንደሆነ እኔ በምን አውቃለሁ እ!» ራስ ወዳድነቷ በቃላቶቿ ውስጥ ጉልቶ ታየኝ። አፈጠጥኩባት።

«እና ምን ይጠበስልሽ አሁን? ስለራስሽ ብቻ ነው የምታስቢው? እንዲህ እንሆናለን እንዲህ ሆንን ከምትይ መጀመሪያውኑ በዛች ጠንቋይ ሀተታ የሞላሻት አንቺው ነሽ . . . አይደለሽ?! ሆስፒታል በር ትተናት እንድንሄድ ያደረግሽ እራስሽ ነሽ። ለራሳችን አስበን በችግሯ ጊዜ በሀመሟ ጊዜ ብቻዋን ትተናት ባንሄድ ከጉኗ ስታየን በተስፋ ትጠነክር ነበር። ይህን የትኛው መፅሐፍ ላይ

እንደሆነ እኔንጃ እንጂ አንብቤአለሁ። ጆሮዋ ስር ሆነን አይዞሽ ብንላት ልትድን ትችል ነበር . . . ምናልባት። እኛ ግን እንደማያውቃት ሰው ሁሉ የሆስፒታል በር ላይ ያለ ደጋፊ ጣልናት። ምንም ነገር ቢደርስብኝ እመርጥ ነበር ካሁኑ ስሜቴ ይልቅ። ሀሊናዬ ጨቅጭቆ ሊገድለኝ ነው። የሞቷ ምክንያት አንቺው ነሽ ይለኛል። ከሁሉም የቆጨኝ እንዳትነቃነቅ እንደ አስረኛ ማሰሬ ነው። ይህንን ስህተታችንን ማካካሻ ያቺን ቻድ መበቀል አለብን። እውነቱን የአበባ ቤተሰቦች ማወቅ አለባቸው። ፖሊስ ማወቅ አለበት። ይህችን ቻድ ከምታደርገው ወንጀል ካላቆምናት ሌሎችንም መጉዳቷን አታቆምም።»

«እኔ የቻዲን ትዕዛዝ ነግሬአት ነበር። አበባ በቀን አንዴ ብቻ የሚጠጣውን መድኃኒት እየነገርኳት ሁለቴ ጠጣች። ያቺ አዋቂ ያለችው አንዴ ብቻ ነበር።»

«አዋቂ? ገና ለዚያች ወንጀለኛ ጠንቋይ ትከራከሪያለሽ?»

ውሃ ቀድታ አመጣችልኝ። በእጇ ዝግ በይ! የሚል ምልክት ከፊቴ ሆና ደጋገመችልኝና ከኮኔ ቁጭ ብላ አቀፈችኝ።

«ማንም አያምነንም! እራሷ ያንን መርዝ መድኃኒት ብላ ጠጣች የሚል የሞኝ አባባል ምክንያት ብሎ ማንም አይቀበለንም። እርግጠኛ ነኝ ገዳዮች ተብለን ጀሀነብ እንላካለን። ስለዚያች ቻድ ደግሞ . . . የእርሷ አምልኮት ተከታዮች ውስጥ የሚበዙት የንጉስ ዘር ሴቶች

ናቸው። የጓደኞችን ህይወት ለእነርሱ ተራ ነው። ጫፏን የሚነካት የለም። እናም አፋችንን ብንከፍት የምንጐዳው እራሳችንን ነው። አበባ እንደሆን አትሰማም ተነስታም አትመሰክርም» ምርጫ አልነበረኝም። በዝምታው በደንብ አሰላሰልኩ። ራስ ወዳድ ሰው የነገሮችን ተቃራኒ ያስባል . . . እንደ አይሻ አይነቱ።

በዛው ብስል አስተሳሰቧ ሌሊቱን በአበባ ህዘን ላይሆን ከሰዎች ጥያቄ እራሳችንን የምንከላከልበትን ቃላት በፀሐፍ ስታስጠናኝ አደረች።

«የመጨረሻ ቀን ምን ምን እንደተባባልን»

«ለብሳ የወጣችውን ቀሚስ ከለር?»

«የት እንደሄድኩ?»

«መቼ እንደመጣሁ»

«ልናመለክት ኤንባሲ መሄዳችንን ጉዳዩን ከማስታወቂያ ማንበባችንን»

ንግግራችን አንድ አይነት እንዲሆን እንደራልም ተዋንያን በደንብ ሸመደድን።

በነጋታው ለነቅድስት ደወልን። ተሰባስበው ቅድስትን ያጀቡ ሴቶች ቤታችንን አጥለቀለቁት። ለቤተሰቧ ስለመንገር እነርሱው ተባበሩን። ሁላችንም ጥቁር ለብሰን ህዘን ተቀመጥን።

❋ ❋ ❋ ❋ ❋ ❋

ያልጠበቅናት ሀብታሚ ጓደኛችን ጀሚላ ብርቱካን መስላ ሀዘን ልትደርስ መጣች። የአበባ የዘወትር ምሳሌ ነበረች። ላለመዋሸትም እኔም አንዳንዴ እሷን መሆን ተመኝቻለሁ። ነፍሷን ይማረውና አበባ ከመሞቷ በፊት «እንደ ጀሚላ ጥሩ ሰው ቢያጋጥመኝ እኮ እንደርሳ ሰማይ እነካ ነበር በአንዴ!» እያለች ትል ነበር።

ግን ይህች የጅዳ ሀበሻ ሴቶች አፍ ውስጥ ሎተሪ እንደደረሳት እድለኛ ሆና የእርሷ አድባር ይለመነን እስከመባል የደረሰችዋ ጀሚላ ከኋላው እንባ ያቀፈ ፊቷን በእኔ በአይሻና በቅድስት ፊት ገለጠችው። ልቧን የሰበረውን የሀብቷን መነሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ተነፈሰች።

ባለጥቁር ሽንጣም መኪና ውስጥ ስገባ ልቤ አላመነልኝም። የማላውቀው ስሜት «ተይ አትግቢ!» እንደሚለኝ አይነት። ግን ደግሞ ይህ ሰውዬ ብዙ ተከትሎኛል።

«አምስት መቶ . . .?»

«ላ . . . . ላ»

«አንድ ሺ ለጥቂት ደቂቃ?»

እንግዲህ እግዜር ያውቃል ብዬ ዘው አልኩኝ። ሰውዬው ግማሽ ፊቱን የሚሸፍን ሰው ሰራሽ ጢም አድርጉአል። በዚያ ጨለማ በአንፀባራቂ መነፅር የተቀረውን ፊቱን ለመሸፈን ሞክሮአል። የመንገድ ሴት

ፈላጊዎች ብዙ ጊዜ ፊታቸውን መለወጪያ የተለያየ ዘዴ ቢጠቀሙም የዚህ ሰው ጉዳይ ከበደኝ።

ወዲያው የመኪናው የኋላ መስታወት ዝቅ አለና አይኖቼን የጨፈኑ ባለሰፋፊ መዳፍ እጆች ተከተሉ። የመኪናው በር ተከፈተና ክንዱ ላይ እንደክትባት ያለ መርፌ ጠቅ ሲያደርገኝ ተሰማኝ። ወዲያው አውቶው ያቀጠኑት ድምፅ እያባበለ አስተኛኝ።

«አይዞሽ አንጐዳሽም የሚያስተኛ መድሐኒት ብቻ ነው» የነቃሁ ጊዜ አነስተኛ የሆስፒታል ክፍል ውስጥ ጉኔ ተጀቡኖ ተጋድሜአለሁ። ሀይለኛ ቁስል ጉኔን ጠፍንቶ ይዞታል። መንቀሳቀስ አቅቶኛል።

ሀኪሜ በፈገግታ «ሀምደላ አሰላማ» ብሎ የእንኳን ለመሻል አበቃሽ ደስታውን ገለፀ።

«ምን ሆኜአለሁ? መኪና ተጋጨ፣ በፍፁም የሆነውን አላስታውስም።» አልኩት

በመሀል ተሰቅ ያለች ሴት ገባች። በጣም በፈገግታ። ክፍሉን አበቦች ወርሰውታል። ቀብሬን ለማሳመር የቆሙ መላእክት መሰሉኝ . . . ደክተሩ፣ ነርሷ።

«ረጋ በይ ስለሆነው ሲሻልሽ እናስታውቅሻለን

ለማንኛውም እኛ በግልጋሎትሽ ስር ነን»

«በግልጋሎትሽ? ቆይ አስረዱኝ!» ጩኸቴን አንጥሮ የሚመልስ ፈገግታ ፍልቅ አድርገው ወጡ።

ስለሆነው ጉዳይ እራሴን ልመረምር ወሰንኩ። ቀኑን ሙሉ የሰራሁትን አስታወስኩ። አዎን በደንብ ትዝ ይለኛል ገንዘብ ፍለጋ . . . ስተታጠብ . . . ገንዘብ ፍለጋ . . . ስለባብስ . . . ስኳኋል ገንዘብ ፍለጋ . . . ስራመድ . . . መኪናና ወንድ ስመርጥ። ቀፋፊዋ መኪና . . . መርፈዉ በደንብ ቁጭ አለልኝ።

በጣቴ ከጭንቅላቴ ጀምሮ ጠቅ ጠቅ እያደረግሁ ሰውነቴ ልክ መሆኑንና አለመሆኑን ላውቅ ሞከርኩ። ሰውነቴ ምንም ልክ አይደለም። በግራ ጐኔ አላስነካ ያለ ጥልቅ ሀመም አለ ከፋሻው ስር። ምን እንደሆንኩ ለማወቅ ሳቂታዎቹን ዶክተርና ነርስ መጠበቅ ነበረብኝ።

ሌሊቱን ስለ እናቴ፣ እህቶቼ፣ ዘመድ ጐረቤት አሰብኩ። ብቸኝነት ገንኖ ሆድ ባሰኝ። አለቀስኩ። ጠያቂ የለኝ የሆንኩትን አላውቅ . . .። ስለገንዘብም አሰላሰልኩ . . . ገንዘብን ከራሴ ማብለጤ ቆጨኝ. . . ለምን ሰርቼ አላገኘሁትም? ለምን ይህ ሁሉ ደረሰብኝ? ብሞትም እኮ ያው የትም ቀረሁ ማለት ነው። ሁኔታዬ አሰጋኝ።

በነጋታው ነርሴ ካርቶን ቸኮላት ይዛልኝ መጣች። የዶክተሩ እንክብካቤ የነርሷ ሁኔታ አበቦቹ . . . እኔ ማን ነኝና ይህ ሁላ ይደረግልኛል። ሰብአዊነትም ቢሆን ገደብ አለው። ጥርጣሬዬ የመኪና አደጋ ደርሶብኝ ካሳ እንዳይከፍሉን የሚያደርጉት ሙከራ ይሆናል የሚል ነበር

እንጂ የደረሰብኝ በደል ይደርስብኛል ብዬ ፈፅሜ አልጠረጠርኩም።

«ቸኮላት ትወጂአለሽ?»

«ማን ይጠላል!» አልኩ በፊታ የሚርመሰመሰውን ፈገግታ አልወደድኩትም።

«ታውቂያለሽ?! ቆንጆ ወጣትና ጠንካራ እንደሆንሽ?!» ነገሯን ደምድሚ ቶሎ ወደ ጥያቄዬ ለመግባት እራሴን በአምንታ ነቀነቅኩ።

«አሁን ተሽሎኛል ምን እንደሆንኩ ንገሪኝ»

«ዶክተር ሲመጣ ለሁለት እንነግርሻለን» በር በሩን አየች።

«እንዴት ነሽ በሽተኛዬ?» አለ ዶክተሩ

«በሽታዬን ለማወቅ ጓጉቻለሁ እባካችሁ . . .»

«ነገር ከመስማትሽ በፊት ጥሩ ትንፋሽ ሳቢ። ይህ ሆስፒታል የግል ነው። በሁኔታው ብትጮኺ ወይ ብትፈርጪ ፋይዳ የለውም። ነገሩን ረጋ ብለሽ ከተቀበልሽ ግን ቀስልሽን ከምርቀዛ አድነሽ ህይወትሽን ታቀያለሽ። የሚጠብቅሽን ድሎት አትርሺ እ!»

ያለኝን ሀይል ሁላ ተጠቅሜ ጮህኩ

«ምን ሆኜአለሁ?»

«ኩላሊትሽን ሸጠሻል» ፈገግታማ ፊቱ ወደ ቁጡነት ሲቀየር ሌላ ሰው መሰለ።

«ኩላሊቴን? እንዴት . . . መቼ?» ተንተባተብኩ።

«በደንብ አዳምጪ!» ጣቱን አወዛወዘ። «ሀሙስ ለት ገላሽን ለመሸጥ ስትንጐራደጂ አስታወስሽ? እኛ ታዲያ ከገላሽ ክፍል ኩላሊትሽን መረጥን።»

አለም ጨልማ ታየችኝ። ጠላኋት። ግን ደግሞ በጣም ስወዳት ስመኛት ተሰማኝ።

«እሞታለሁ?» ሁለነገሬ ባንዴ ሲደክም ተሰማኝ ተስፋ በመቁረጥ ጥያቄዬን ደገምኩ «እሞታለሁ?»

«ላ . . . ላ . . . አንቺ ወጣትና ጠንካራ ነሽ። በአንድ ኩላሊት መኖር ትችያለሽ። ብቻ ተናደሽ በማንወደው መንገድ ከቆምሽ . . .ፖሊስ ሀግ ምናምን . . . ጥሩ አይሆንም። ለኛ በጥቂቱ . . . ላንቺ ግን በትልቁ። እኛ ከዚች ወንጀል ምንም ሳንነካ እንወጣለን። አንቺ ግን ሁሉን ነገር ትከስሪአለሽ። ኩላሊትሽን . . . የምንከፍልሽን ገንዘብ . . . ብሎም አዕምሮሽን»

«ኩላሊትሽን የሰጠሻት ሴት በገንዘቡ ብዙ ነገር የሚያናጋ የእድግ ሀብታምና ታዋቂ ሰው ሚስት ናት። ብዙ ደምም ሰጥተሻታል። ህይወት ሰጠሻት ማለት ነው። ታዲያ ለዚህ ውለታሽ ባሏ የተቀረ ህይወትሽን ሊቀይርልሽ ቃል ገብቷል። ስለሄደው የአካል ክፍልሽ እርሺ። አይመለስም። ስለሚመጣው ህይወትሽ አስቢ። አንቺ

ካሁን ወዲያ የሚያደክም ስራ እና አድካሚ የህይወት ውጣ ውረድ መሸከሙ ቀላል ላይሆንልሽ ይችላል። ጤንነትሽን ለመጠበቅ የተደላደለ ገንዘብ ያስፈልግሻል። ጥሩ ልጅ ሆነሽ የተወሰኑ ወረቀቶች ላይ መፈረም ብቻ ችግርሽን ይወጣልሻል። እንዳልኩሽ ጥሩ ልጅ ሁኚ» ትተውኝ ወጡ።

ስለምን ላልቅስ? ስለተቀደደው ቆዳዬ ወይስ ሳላውቀው ስለተቀዳው ደሜ? ወይስ ሳልፈቅድ ስለተሰረቀው ኩላሊቴ? ወይስ ስለመብቴ . . . ለማን እሮሀለሁ። ለሁሉም ደክመኝ . . . ሀይል አነሰኝ . . . ተበሳጨሁ . . . የአለም መጥፎ ስሜቶች ሁሉ አላዬ ላይ ሰፈሩ።

ሌባው ዶክተር እንዳለው በሰላም ወረቀቶች ላይ ፈረምኩ። በተለያየ መልኩ የተደረገልኝ የኩላሊቴ ክፍያ ሀብታም አሰኘኝ።

* * * * * *

አይሻንም እንደቀላል ተሰናበትኩ። ለዚያውም አልጋዬ ላይ በተወችልኝ ማስታወሻ፡-

መርህባ! ይህንን ስታነቢ እኔ እርቄ እገኛለሁ። ለስንብትሽ አልቅሺ አዝኜአለሁ። በእንደዚህ ሁኔታ ትቼሽ

ለመሄድ የራስ ወዳድነት ስሜት ስለተሰማኝ ፊት ለፊት ልጋፈጥሽ እና ቻው ልልሽ አልቻልኩም።

ግን ከዚህ በፊት ያላልኩሽን ምክር ልምከርሽ። ገንዘብ እኛ ባመጣነው መልኩ ከተገኘ ደስታን አያስገኝም። እራሴን አይሸጡ መሸጥ ሽጨ ገንዘብ አግኝቻለሁ። ግን ይህ እዚህ አልፈው የምሄደው ምስቅልቅል ህይወት እድሜ ልኬን ይከተለኛል ብዬ ሰግቼአለሁ። ካሁኑ የለበስኩት ልብስ ይቀፈኝ ጀምሮአል። በዚህ ከቀጠለ ባገኘሁት ገንዘብ የማደርገው የኑሮ መሻሻል የድሮ ጥላሸት ህይወቴን በየደቂቃው የሚያስታውሰኝ ከሆነ ምኑን ኖርኩት?! ማን እንደሚያስቀናኝ ታውቂያለሽ? ያች ፅኑ ሌት ቅድስት። ምክሬም እንደበፊትሽ ከሷው ጋር እንድትጠጊ ነው። ያሁኑ መንገድሽ እንደሳልዋ ወይ እንደ ጀሚላ ወይ ደግሞ እንደ እኔ አይነት ዕድል ላይ ነው የሚጥልሽ። የሳልዋን እና የጀሚላን የሕይወት ሰቆቃ አይተሽዋል። የተሻለ የመሰለሽ የኔ ሕይወት ደግሞ ውስጡ ለቁስ ነው። ማድረግ የነበረብን እንደቅድስት እራሳችንን ጠብቆ ደረጃ በደረጃ የፈለግንበት መድረስ ነበር። እኛ ግን እራሳችንን ሰውተን ገንዘብ በላያችን ላይ እንዲጫወት ፈቀድን።

ለማንኛውም በድንገት አዲስ አበባ ከተገናኘን ዘመናይ ብለሽ በእውነተኛ ስሜ ጥሪኝ አይሽ።

* * * * * *

ምዕራፍ አስር

እራሴን ፍለጋ በሄድኩ ቁጥር ራሴን ሌላ ውሽት ሌላ ማስመሰል ውስጥ አገኘዋለሁ። ለምዶብኛል። በጣም የሚቀፈውን ኮሳሳ ሽማግሌ አረብ «ለኔ ልጅ ሆነህ ትታየኛለህ ወንዳ ወንድነትህ እንዳለ ነው» ብዬ ውሸቴን አቀልጣለሁ። ለሊቱንም ሽማግሌው ሲያንኮራፉ እንቅልፍ አይወስደኝም። በተነፈሰ ቁጥር የሚያወጣውን ደስ የማይል ትንፋሽ ልሸሽ ፊቴን ሳዞር ይነቃና እንደነበርኩ አዙሮ ይባስ ጥብቅ አድርጐ አቅፎኝ ይተኛል። ብቻውን መተኛት ይፈራል። እኔም በየቀኑ እርጅናን ከአይኑ እያነበብኩ ወደፊት የሚጠብቀኝን ህይወት ፈራሁት። ኡፍ! ማርጀት ሲያስጠላ . . . ወጣት እያለን የተሰጠንን ውበት ተስፋ ሀይል ብዙ ብዙ ነገር መቀማት . . . ሲያስፈራ። ከጐኑ ተኝቼ ብዙ አሰላስላለሁ። እንደዛ እንዳልኮራሁ ለውበት እንዳልተንበረከኩ አሁን እንዴት እራሴን ከሽማግሌ ጋር አስተኛለሁ። ውበት በጣም እወድ የለ!። ታዲያ ሽማግሌ ላይ የነበረ ውበት ብቻ ነው ያለው . . .። ሽማግሌውስ ለምን ሚስቴን አያቅፍም? በርግጥ እንደርሱ አርጅታ ይሆናል። ሙቀት እንደሚፈልግ ደጋግሞ አስጠግቶ ሲያቅፈኝ ተረድቼአለሁ። እርሱ ሙቀት ሳይሰጠኝ ከእኔ ብቻ ለሚወስደው ሙቀት የሚሰጠኝ ክፍያ በቂ ነውን? አንዳንዴ ከእንቅልፌ ስነቃ

ሽብሽብ አካላቱ ይቀዘቅዘኛል። ያ ሀይለኛ ማንከራፋቱ ቀጥ ይልና ምንም ድምፅ አያሰማም። ጠጋ እልና ትንፋሹን አዳምጣለሁ። እፈራለሁ ሞቶ ይሆን እንዴ?! እያልኩ። የዛኑ ጊዜ እምላለሁ ዛሬ የመጨረሻ ሌሊት ይሆናል ከርሱ ጋር የማድረው . . . እልና፤ ቀን ሲሆን በስልክ የሚያወራው ወሬ እግሬን ይጉተተዋል። ሁሌ የሚያወራው ትልቅ ስለሆነው ድርጅቱ ነው። ታዲያ ስለዚህ ድርጅቱ ሲያወራ እርጅናው ከላዩ ላይ የጠፋ ይመስላል። እርጅናው የሚሰፍርበት ምሽት ላይ ነው። መነፅሩን ሲያወልቅ አይኖቹ ደጋፊ ያሻሉ። ልብሱን ሲያወልቅ ገላው ከሌላ ሰው ሙቀት ይፈልጋል። በጣም ይተኛል ሰውዬው . . . ደክሞታል።

ግንኮ ማስመስሌን አውቆታል። ሽማግሌው ካንድ ጓደኛው ጋር ሲያወራ «'አነ አንድ ከዛባ' /ውሽታሚ ጋ ነኝ/» ብሎ ሲለው ሰማሁ። «ሁሌ ስትዋሸኝ ውሸቷ ይጥመኛል። ደግሞ ውሸቷ ያልበሰለ ነው። ሽምግዬ እያለሁ ገና ነህ ትለኛለች። ውሸቷ እስኪሰለቸኝ ልያትና ውሸታም ብዬ አባርራታለሁ»። የገረመኝ ግን ታወቀብኝ ብዬ አለማፈሬ ነው። አንዳንዴ ሙልጭ እድርጉ ሰድቦኝ ገፍቶ ከቤቱ አስካላወጣኝ አልሄድም ብዬ እቀመጣለሁ። ክብር የለ ስሜት የለ ሌላው ቢቀር ንዴት የለ። አጥንት የሚሰብር ስድብ ሰምቼም . . . ውርደት የለም። ምንም አይመስለኝም። የሰውነት ስሜቶቼ ድብን ብለው ሞተዋል።

ለዚህ ሕይወቴ የከሰር ዝርዝር ቢሰጠው ከለሩ ያለመወላወል ጥቁር ነው። ህይወቴ ከለሩ ጠቁሯል። ለዚያውም ሙሉ አዕምሮዬን ካበላሸ ጥላሸት ጋር!።

ስናገር ስሄድ ስራመድ ስቀመጥ በስልት ሆኖአል። ስስቅም በስልት ስለምስቅ አስካለሁ። በሲጋራ እየጠቆረ ያለውን ከንፈሬን ለመሸፈን ደማቅ ሊፕስቲክ እጠቀማለሁ። የሲጋራ ጭስ መንስኤው የአረቦቹ ግፊት ነበር። እነርሱ እንደሆነ ለኔ ባልተፈጠረ አለም ውስጥ ከትተውኝ ከውጭ ሆነው ይስቁብኛል። ከከተቱኝ አለም ስወጣ እራሴን እጅግ ረክሶ አገኘዋለሁ። ያን ለመርሳት ጭስ ማየት ፈለግኩ። ውስጤ ያጨሰው ነገር በሲጋራ ትነት ሲወጣ የማየው መሰለኝ። ሲጋራ ማጨስ በዚህ መልኩ ለመድኩ። ከንፈሬን የምሸፍንበት ደማቁ ሊፕስቲክ አያምርብኝም። አይኖቼም ያዘሉትን ሀዘን ለማጥፋት በወፍራሙ አኩላቸዋለሁ። ለራሴም ይታወቀኛል . . . ጭራቅ እንደመሰልኩ፤ ከማማር ይልቅ። በዚህ ሦስት ዓመት ውስጥ ልጅነቱ ጥሎኝ የሄደ ይመስላል። ካንዱ ከሌላው ጋር ስጓዝ አነርሱም ምጥጥ እያረጉ ሲያባርሩኝ . . . ተሰፋ ቆረጥኩ።

እነዛ ትልልቅ ሕልሞቼ፤ ቪላ ቤትና መኪና ልይዛቸው በሮጥኩ ቁጥር እያላገጡ ይሸሹኛል። በርግጥ እንደ አጐቴ ልጅ እጀን በወርቅ አንጣሮች ሞልቼአለሁ። ለእነዚህ ሕይወተ-ቢስ ብልጭልጮች ሕይወቴን ከፍያለሁ። በእነሱ ሰበብ እራሴን ፍለጋ አባክናለሁ። ኩራቴ ልሳላሴዬ ልጅነቴ አስተላሰቤ . . . ወይ ነዶ!።

ምዕራፍ አስራ አንድ

እመለስ ይሆናል። ምናልባት እራሴን ፈልጌ ማግኘት ከቻልኩ . . . ካልቻልኩ ግን እዚሁ በስደት መቅረቱን እመርጣለሁ። የምመለሰው ያጠፋሁትን እኔነቴን ካገኘሁ ብቻ ነው። ወዜን ትዕግስቴን አደቤን ስነ ስርዓቴን ሀልሜን ተስፋዬን እንደነበር ማግኘቱ ቀላል አይመስለኝም። ግን እሞክራለሁ . . . እኔነቴን ካገኘሁ እመለሳለሁ። እመጣለሁ ምናልባት . . .።

ግን ደግሞ ይህ አገር እኔነቴን የማይመልስልኝ ከሆነ ምናልባት አንድ ቀን፦

«'አልባብ ይጅለክ ሚኑ ሪህ ዚቱ ወእስተያህ' /ሽታ የሚያመጣልህን በር ዝጋውና እረፍ/ የሚለው ተረታቸው የገባኝ እለት የስደትን በር ለመዝጋት አገሬ እገባለሁ።»

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ትህትና ከፊቷ የተዝረከረኩትን ከደርዘን በላይ የሚሆኑ የፖስታ ኪሶች ወደ መሳቢያ ከተተችና በሀሳቧ አብሮ አደግ ጓደኛዋን «አይ መሲ! እንዳልሽው ቶሎ እራስሽን አግኝተሽ በመጣሽ። በጣም ናፍቀሽኛል። መጨረሻሽ ምን ይሆን?» ብላ «የህይወቱ ከለር ጥቁር ነው» በሚል ለዓፈችላት የልብ ጓደኛዋ ተከዘች። ለደብዳቤዋም አመስግናታለች . . . . ትህትና። የስደትን ችግር ሳይረዳ ልሂድ ልሰደድ የሚላትን ፍላጐቷን የመሲ ደብዳቤ አብርዶላታል።

ደግማ «ምስኪን መሲ! ምስኪን . . .» እያለች በጣም አጫጭር የሰላምታ አንቀፆች የያዙትን እጅግ ረጃጅም ደብዳቤዎችን በቅደም ተከተላቸው በወረቀት ማያያዣ አንድ ላይ አያያዘቻቸውና በትልቁ ይድረስ ለአዲስ ህትመት ድርጅት የሚል ዕሁፍ አሰፈረችበት።□

ተፈፀመ